አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት


# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY



በ

ሊያ መዝገቡ


በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ለኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ


አዲስ አበባ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ

በ

ሊያ መዝገቡ

በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ለኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አማካሪ
ስርግው ገላው (ዶ/ር)

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ
የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

አዲስ አበባ
ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ

በ

ሊያ መዝገቡ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት

ሥርግው ገላው ________________ [signature] ________

አማካሪ ፊርማ

[illegible] ________________ [signature] ________

ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና


- ትህትናና አክብሮት ሳይለያቸው አስፈላጊውን ምክርና መረጃ ለሰጡኝ፣ጊዜያቸውን ሰውተው የጥናቱን ረቂቅ ፈጥነው በማረምና ሂሳዊ አስተያየታቸውን በመለገስ ከእኔ ጋር አብረው ለደከሙ አማካሪየ ዶ/ር ስርግው ገላው ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

- ጋሽየና ታለምየ (አለሙ አኖ እና የባህር መዝገቡ) ትምህርትን አስተምሮ ለጥሩ ደረጃ ከማብቃት ባሻገር የጥናቱን ስራ ጀምሬ እስከማጠናቅቅ ድረስ አስፈላጊውን ምክርና እገዛ ስላደረጋችሁልኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡
- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአንድ አመት ነፃ የትምህርት እድል በመስጠት ትምህርቴን እከታተል ዘንድ ስለፈቀደልኝ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡
- የአዲስ አበባ ሃገረ ስብከት ሊቀጳጳስ፣ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብጹእ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ረዳት እና የሲኖዶስ አባል የሆኑት ብጹእ አቡነ ቀውስጦስ እንዲሁም የበአታ ለማርያም መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መምህር መጋቢ.ጥበብ የማነብርሃን ጌታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እችል ዘንድ ስላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡
- የሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የዜና አበው መምህር ሃይማኖት ኃይለማርያም ፣በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የማህበረ ቅዱሳን ጽህፈት ቤት፣ ከመጽሄት አዘጋጅ ክፍል ጌታቸው በቀለ፣ ከኦዲዮ ቪዥዋል የትናየት ይፍሩ፣እና ከቤተመጻህፍት ዳዊት ደስታ የጥናቱን መረጃዎች እንዳገኝ ስላደረጋችሁልኝ ትብብር በጣም አመሰግናለሁ፡፡

- መምህሮቼ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው፣ አብርሃም አለሙ፣ወንድወሰን አዳነ እና መሐመድ አሊ ለጥናቱ የሚነበቡ መጽሐፎችን በመስጠት ስለተባበራችሁኝ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡
- ይበይን መዝገቡ፣ሐፍታይ ገብረ እግዚአብሄር ፣ መጋቢ ምስጢር ሰናይ ባያብል ፣ቅድስት መለሰ፣ ተስፋዬ ሞላ፣ ሄለን ኤፍሬም፣ሙሉቀን ንጋቱ፣ ከሁሉም በላይ፣ ታደለ ብርሃኑ፣ወንድወሰን ጽጌ፣ ይታገሱ ሽምዬ፣ምህረት ሞላ እና መቅደስ ተሾመ ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን መጽሐፎች፣ ማቴሪያሎችና መረጃዎች በመስጠት ስለተባበራችሁኝ፣ እንዲሁም ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ተገንዝባችሁ ገንቢ ሃሳባችሁን በመለገስ ብርታት ስለሰጣችሁኝ አመሰግናችኋለሁ፡፡
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኬኔዲ ቤተመጻሕፍት ኃላፊ አቶ በኃይሉ ጀማነህ፣የኢትዮጵያን ኮሌክሽን ክፍል ሰራተኞች እና የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ መጻሕፍት ሰራተኞች ሳትታክቱና ሳትሰለቹ መጽሐፎችን በቅንነትና በፍጥነት ፈልጎ በማቅረብ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ እንዳገኝ አድርጋችኋል፡፡ ይህም የጊዜ መስተጓጎል እንዳይገጥመኝ ረድቶኛልና በጣም አመሰግናለሁ፡፡


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# የምህፃረ ቃላት መፍቻ

ዮሐ. - የዮሐንስ ወንጌል

ሉቃ. - የሉቃስ ወንጌል

ማቴ. - የማቴዎስ ወንጌል

ሐዋ. - የሐዋርያት ሥራ

1ኛ ጢሞ. - የመጀመርያይቱ የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች

1ኛ ጴጥ. - የመጀመርያይቱ የሐዋርያው የጴጥሮስ መልዕክት

ገላ. - የሐዋርያው የጳውሎስ መልዕክት ወደ ገላትያ ሰዎች

ምሳ. - መጽሐፈ ምሳሌ

ዘፀ. - ኦሪት ዘጸአት

መዝ. - መዝሙረ ዳዊት

ዘፍ. - ኦሪት ዘፍጥረት

ኢሳ. - ትንቢተ ኢሳይያስ

# አጠቃሎ

በዚህ ጥናት የቀረበው ርዕስ ጉዳይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደበት ምክንያትም የሥርዓተ ክዋኔውን ሃገረሰባዊ ልማድ ገጽታ ለማመልከት ነው፡፡

የጥናቱን መረጃዎች ማግኘት ይቻል ዘንድ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሆነው አገልግሎት ላይ የዋሉት ምልከታ ፣ ቃለመጠይቅ እና የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭ የአጠናን ስልት ቀርበዋል ፡፡ ጥናቱ የሥልጣነ ክህነትን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ በትኩረት የሚመለከት በመሆኑ መረጃዎችን ተንትኖ ለመተርጎምና ሃገረሰባዊ ልማዱን ለማሳየት የክዋኔ(Performance) የቲዎሪ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡በዚህ የቲዎሪ አቅጣጫ መሠረትም በሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ላይ የሚታዩ ትዕምርቶች ተተርጉመዋል፤ የሥርዓተ ክዋኔው ፋይዳም ተጠቁሟል፡፡

በጥናቱ የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎች ፣ ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ፣ ካህናት የሚሰጡት መንፈሳዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲሁም የአኗኗር ልማዳቸው ምን እንደሚመስል ተጠቁሟል ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክንዋኔው ለምን? መቼ ?እንዴት ? የት ? እንደሚፈፀም በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ መልስ ይሰጣል፡፡

ጥናቱ ተጠንቶ ከተጠናቀቀ በኂላ የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎች ዲቁና ፣ ቅስና እና ኤጲስ ቆጶስና መሆናቸው ፣ አሁን ያለው የክህነት አሰጣጥ መሰረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ሥልጣንን የሰጠበት ሥርዓት መሆኑ ፣ ካህናት ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ የአኗኗር ልማድ እንዳላቸው እና ማህበረሰቡን የመቆጣጠር ፣ የመግራት ፣ ከሃጢያት የመመለስ ተግባር እንደሚፈፅሙ፣ የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ፋይዳ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንንና ሥርዓተ አምልኮን ለመፈፀም የሚያስችል ኃይል ማጎናፀፍ እንደሆነ እና የስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔው ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ በሃገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተት መሆኑ በጥናቱ ግኝት ላይ ተጠቁሟል ፡፡

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና ......................................................................................i
የምህፃረ ቃላት መፍቻ ....................................................................ii
አጠቃሎ......................................................................................iii
የአርዕስት ማውጫ .........................................................................iv

**ምእራፍ አንድ**

1. መግቢያ ....................................................................................1
   1.1. የጥናቱ አላማዎች .................................................................3
   1.2. የምርምር ጥያቄዎች.................................................................4
   1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት .................................................................4
   1.4. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ...........................................................5
   1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................................................6
   1.6. በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ........................... 6
   1.7. የጥናቱ ዘዴ (Theory) ..............................................................7
   1.8. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች .......................................................8
   1.9. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..............................................................9

**ምእራፍ ሁለት**

2. የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት.............................................................10
   2.1. ያልታተሙ የጥናት ፅሑፎች ......................................................11
      2.2 የታተሙ ፅሑፎች ..............................................................18

**ምእራፍ ሶስት**

3.የጽሑፎች ዳራ
   3.1 በኢትዮጵያ የክርስትና ሐይማኖት እና የክህነት አጀማመር ታሪካዊ ዳራ.........26
      3.1.1 የክርስትና ሐይማኖት አጀማመር.............................................26
      3.1.2. የክህነት አጀማመር...........................................................33
         3.1.2.1 በብሉይ ኪዳን................................................................ 33
         3.1.2.2 በሐዲስ ኪዳን................................................................36

3.2 የስልጣነ ክህነት ምንነት ........................................................40
3.2.1 የስልጣን ምንነት ........................................................40
3.2.2 የክህነት ምንነት ........................................................40
3.3 የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎችና ምንነታቸው ........................................43
3.3.1 ዲቁና ........................................................44
3.3.2 ቅስና ........................................................45
3.3.3 ጵጵስና (ኤጲስ ቆጶስነት) ........................................................46
3.4 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት ተዋረድ.....47

## ምዕራፍ አራት

4. የንድፈ ሐሳባዊ ዳራዎች ትንታኔ........................................................50
4.1 ወግ ማዕረግ (Rite of passage)........................................................50
4.2 ሥርዓተ ክዋኔ ........................................................54
4.2.1 የሥርዓት ምንነት ........................................................54
4.2.2 ሃይማኖታዊ ሥርዓት ........................................................55
4.2.3 የሥርዓት አስፈላጊነት ........................................................57
4.3 ክዋኔ (performance)........................................................58
4.3.1 የክዋኔ ምንነት ........................................................58
4.3.2 የክዋኔ አላባውያን /Elements of performance/........................59
4.3.3 የክዋኔ መገለጫ ባህርያት ........................................................61
4.3.4 የክዋኔ ገጽታዎች........................................................62
4.3.5. ትእምርት ፣ ትርጉም እና ተግባር........................................................66

## ምዕራፍ አምስት

5. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣን
አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ........................................................69
5.1 የዲቁና ሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ........................................69
5.1.1 ቅድመ ሥርዓተ ክዋኔ ........................................................69
5.1.1.1 ሥርዓተ ጥምቀት........................................................69
5.1.1.2 የቤተክህነት ወይም የአብነትን ትምህርት መማር........................71
5.1.1.3 ንፅሕናና መልካም ስነ ምግባር ........................................75

5.1.2 ሥርዓተ ክዋኔ ....................................................................75
5.1.3. ድህረ ሥርዓተ ክዋኔ ....................................................................87
5.2 የቅስና ሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ..................................................90
5.2.1 ቅድመ ሥርዓተ ክዋኔ ....................................................................90
5.2.2 ሥርዓተ ክዋኔ ....................................................................91
5.2.3 ድህረ ሥርዓተ ክዋኔ ....................................................................93
5.3 የኤጲስ ቆጶስና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ..........................................96
5.3.1 ቅድመ ሥርዓተ ክዋኔ ....................................................................96
5.3.2 ሥርዓተ ክዋኔ ....................................................................98
5.3.3 ድህረ ሥርዓተ ክዋኔ ....................................................................107
ምዕራፍ ስድስት
6.1 ማጠቃለያ ....................................................................109
6.2 የጥናቱ ግኝቶች ....................................................................110
6.3 ከቀረቡት ግኝቶች በመነሳት በጥናቱ የተደረሰበት ማጠቃለያ (Conclusion) ......113
ዋቢ መጻሕፍት ....................................................................115
አባሪዎች
የመረጃ ሰጪዎች አጭር መግለጫ
የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች
ፎቶግራፎች

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

የሰው ልጅ በተፈጥሯዊም ሆነ በማህበራዊ ሥርአቶች ውስጥ የሚያልፍባቸው አዳዲስ የህይወት ገጽታዎች አሉት። እነዚህ ገጽታዎች አንድን ማህበረሰብም ሆነ ግለሰብ ቀደምት ይኖርበት የነበረውን የህይወት አቅጣጫ ቀይረው ወደ አዲስ (ሌላ) የአኗኗር ዘይቤ የሚያሻግሩ ናቸው።

እነዚህ ሽግግሮች በማህበረሰባችን ዘንድ ወግ ማዕረግ (*Rite of passage*) ተብለው ይጠራሉ። አንድ ግለሰብ ወግ ማዕረጉን ከሚያይባቸው ገጽታዎች መካከል አንዱ ሹመት (advancement to a higher class) ወይም ስልጣንን መቀበል ነው። ሹመትን ለመስጠትም ሆነ ለመቀበል የተለያዩ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይፈጸማሉ። ሥርዓተ ክዋኔዎቹ እንደ ማህበረሰቡ ወግ እና ልማድ የሚለያዩ ሲሆን የሹመቱ ዓይነት ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ መሆኑ ደግሞ በክዋኔው ዓውድ ላይ ልዩነት ይፈጥራል።

ይህ ጥናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔ ገጽታ ምን እንደሚመስል ያሳያል ። በሥርዓተ ክዋኔው ላይ የሚታየው የፎክሎር ዘርፍ ሃገረሰባዊ ልማድ ነው። ስርዓተ ክዋኔው ሃይማኖታዊ ስርአት ሆኖ ግለሰቦች የክህነትን ስልጣን ለመቀበል የሚፈጸምላቸውን ክንውኖች ያሳያል። ሥልጣነ ክህነትን በመስጠት እና በመቀበል ላይ ያለውን ገጽታ ለማሳየት ጥናቱ በስድስት ምዕራፎች ተጠቃሎ ቀርቧል።

ምዕራፍ አንድ የጥናቱን መግቢያ የያዘ ነው። በውስጡም የክዋኔን የጥናት ዘዴ በመጠቀም የጥናቱ አቢይ አላማ የፎክሎር ገጽታዎችን ለማሳየት መሆኑ የተጠቆመበት እና ሌሎች በመግቢያ ውስጥ የሚካተቱ ዋና ዋና ነጥቦችንም ይዟል ።

በምዕራፍ ሁለት የታተሙና የልታተሙ የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት ቀርቧል። የታተሙ ፅሁፎች ለንባብ የበቁ እና በገበያ ላይ የዋሉ መፃህፍቶች ሲሆኑ ያልታተሙት ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለኤም.ኤ እና ቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ሆነው የቀረቡ የጥናት ሥራዎች ናቸው።

በምዕራፍ ሦስት የጽሁፎች ዳራ ቀርቧል። ትኩረት ያደረገውም የጥናቱን ርዕስ ጉዳይ የተመለከቱ ጽንስ ሃሣቦችን ሲሆን እነሱም የክርስትናና የክህነት አጀማመር በኢትዮጵያ፣ የሥልጣነ ክህነት ምንነት፣ደረጃዎችና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነትን ተዋረድ የሚያሳዩ ናቸው።

በምዕራፍ አራት ላይ የጥናቱን ርዕስ ከፎክሎር "ዲሲፕሊን" አንፃር በመመልከት ጥናቱ በተጠናባቸው የቲዎሪ አቅጣጫዎች ላይ ትንታኔ ቀርቧል። በዚህ ክፍል ትኩረት ተሰጥቶት ንድፈ ሃሳባዊ ብያኔ የቀረበበት "ሥርዓተ ክዋኔ" ሲሆን ሥርዓት ምንድን ነው ? ክዋኔስ ምን ምን ገጽታዎች አሉት? የክዋኔ አገልግሎትስ ምንድነው? የሚሉ እና ሌሎችም ጉዳዮች ቀርበውበታል ። ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ ርዕስ ጉዳይ የሚያመራው ሹመትን በተመለከተ ሲሆን ይህ አቅጣጫ ደግሞ በሃገረሰባዊ ልማድ ውስጥ በወግ ማዕረግ ሥር የሚመደብ ነው። ስለሆነም በወግ ማዕረግ ላይ የቀረበው የጌኔፕ ንድፈ ሃሳብ ቀርቧል።

በምዕራፍ አምስት የመረጃ ትንታኔ ቀርቧል። ስልጣነ ክህነትን የተቀበለ ግለሰብ ማስታረቅ፣ ማማለድ፣ ችግር መፍታት፣ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን መምራትና ማደራጀት በአጠቃላይ ስጋዊም ሆነ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን መስጠት ይጠበቅበታል። የክህነት ህይወት ከከፍተኛው የመንፈሳዊ አገልግሎት ጎን ለጎን ማህበራዊ እና ግለሰባዊ የሆኑ ተግባሮችም የሚከናወኑበት ነው።

በመሆኑም ግለሰቦቹ እነዚህን የመሳሰሉ ከባድ ኃላፊነትን የሚጠይቁ ስርዓቶች ሲቀበሉ ያለው ገጽታ በዚህ ምዕራፍ ቀርቧል። እነዚህን ገጽታዎች ለማሳየት ለእያንዳንዱ የስልጣን ዓይነቶች ሶስት አበይት ጉዳዮች ቀርበዋል። የመጀመሪያው "ቅድመ ስርዓተ ክዋኔ" ሲሆን ይህም ካህናትን ለስልጣነ ክህነት የሚያበቋቸው መስፈርቶች ምን ምን እንደሆኑ በመስክ የተደገፈ መረጃ የቀረበበት ነው። ይህ ገጽታ የሚያመለክተው ክህነትን የሚቀበሉ ግለሰቦች ከማህበረሰቡ ተለይተው (separation)አዲስ ህይወትን የሚጀምሩበት ነው። ይህ ርዕስ ጉዳይ አስፈላጊ ሆኖ የቀረበበትም ምክንያት ክህነቱን ለመስጠት መስፈርቶቹ ተግባራዊ በመሆናቸው እና የአሰጣጡ አካሄድ (ቅደም ተከተል) ከእነዚህ መስፈርቶች ጀምሮ እየተጣራና እየተለየ መምጣት ስላለበት ነው።

ሁለተኛው ክፍል የስልጣን አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔውን የሚያሳይ ነው፡፡በዚህ ውስጥ የተነሳው ጉዳይ ከነበሩበት ማህበራዊ ቦታ ወደ ቀጣዩ ሲሻገሩ (transition rite) የተፈጸምላቸውን ስርአተ ክዋኔ የሚያሳይ ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ "ድህረ ስርዓተ ክዋኔ" ማለትም ከስልጣን አሰጣጥ ስርዓቱ በኂላ ካህናት በማህበረሰቡ ውስጥ በመቀላቀል (reincorporation)እንዲፈጽሟቸው የሚጠበቅባቸው ጉዳዮችን(ትእዛዞችን) የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ትዕዛዛት ከፊሎቹ ስርአቱን ፈጽሞ ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ተልዕኳቸውን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ይህ ክፍል በስርአተ ክዋኔው የተፈጸመው ድርጊት ምን ያህል የሰዎችን ህይወት መለወጥ እንደቻለ የሚያሳይ ነው፡፡ የመጨረሻው ክፍል ምዕራፍ ስድስት ሲሆን በውስጡ ማጠቃለያና የጥናቱ ግኝቶች ቀርበዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ የሆነውን ሃገረሰባዊ ልማድ ማሳየት ሲሆን በተጨማሪም ቀጥሎ የቀረቡ ንዑስ ዓላማዎችም አሉት እነሱም፡-

- የስርአተ ክዋኔው አፈጻጸም መነሻ ከየት እንደሆነና ለምን እንደሚፈጸም ገልጾ ማሳየት፤
- ለስልጣነ ክህነት የሚመረጡ ግለሰቦች የሚያልፉባቸውን ዓበይት የህይወት እርከኖች ገልፆ ማሳየት፤
- ስልጣነ ክህነትን የሚቀበሉ ግለሰቦች ማሟላት የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች እና የክህነትን ደረጃዎች መግለጽ፤
- ስርአተ ክዋኔው ለየትኞቹ የስልጣን አይነቶች ብቻ እንደሚፈጸም መግለጽ፤
- በስርአተ ክዋኔው ምን በማን፣እንዴት፣የትና መቼ፣ለምን፣ እንደሚፈጸም መግለጽ ፤
- ስርአተ ክዋኔው በተፈጸመላቸው ሰዎች ላይ የታየውን የህይወት ለውጥ መግለጽና ግለሰቦቹ በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚሰጡትን መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ እና ግለሰባዊ ፋይዳ /አገልግሎት/ መጠቆም እና
- ፎክሎር ተለዋዋጭ (dynamic) በመሆኑ የሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማህበረሰቡ እንደደረሰበት የአስተሳሰብ ደረጃ ሊለወጥ ይችላል፡፡ በአሁን ሰዓት



ADDIS ABABA UNIVERSITY ... ILS LIBRARY

ያለው የሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓት ማህበረሰቡ ያለበትን ደረጃ ያመለክታልና በምስል ቀርጾ በማስቀመጥ መሰነድ(ዶክመንት ማድረግ) ናቸው፡፡

## 1.2 የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በሂደት ይመልሳል፡፡ እነዚህም ጥያቄዎች፡

1. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓት እንዴት፣መቼና የት ይካሄዳል? በክዋኔው የሚኖረው ፎክሎራዊ ገጽታስ ምንድነው?
2. በስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶች ወይም ክዋኔዎች ምን ምን ናቸው? የክዋኔዎች ትዕምርታዊ ፋይዳስ ምንድነው?
3. የስልጣነ ክህነት አይነቶች ምን ምን ናቸው?
4. የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ ለምን ይጠቅማል ?
5. ስልጣነ ክህነትን ለማግኘት መፈጸም ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?
6. ግለሰቦች ስልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኋላ የሚሰጡት መንፈሳዊ እና ማህበራዊ አገልግሎትስ ምንድነው?
7. ስልጣነ ክህነትን የተቀበሉ ግለሰቦች የአለባበስ ስርአትና የአኗኗር ልማድ ከሌላው ማህበረሰብ ለምን ተቀየረ ? የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

1. የቤተክህነት ስልጣን ሥርዓተ ሹመትን በተመለከተ ለሚካሄድ የፎክሎር ጥናት ዘርፍ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይሰጣል፤
2. ስልጣነ ክህነትን በመቀበል ሂደት ውስጥ ያሉ ትውፊቶችን፣ ሃገረሰባዊ ልማዶችንና ስርዓቶችን ይጠቁማል፤
3. የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርአተ ክዋኔ ስልጣኑን ለሚቀበሉት ግለሰቦች የሚሰጠውን ፋይዳ ይገልጻል፡፡

4. የአንድ አገር መንፈሳዊ እና ባህላዊ እሴቶች ተጠብቀው የማህበረሰቡ ህይወት፣ አኗኗር ፣ፍልስፍና ፣ አስተሳሰብና ሌሎችም ይታወቁ ዘንድ የካህናት ድርሻ የት ላይ እንዳለ ይጠቁማል፤
5. በቤተክህነት የስልጣን አቀባበል ስርአት ላይ ግለሰቦች የሚልፉባቸውን የህይወት ሽግግሮች ወይም ደረጃዎች ያመለክታል።
6. በቤተክህነት ውስጥ የሚሰጡ የሹመት( የማእረግ) ዓይነቶችን፣ ሥርዓተ ክዋኔውን፣ ማህበረሰቡ ለካህናት ካህናት ደግሞ ለማህበረሰቡ ያላቸውን አመለካከት እንዲሁም ሹመትን ከተቀበሉ በኋላ የሚኖራቸውን ማህበራዊ ቦታ /Status / ማወቅ ለሚፈልግ አካል መረጃ ይሰጣል።

## 1.4 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በየሳምንቱ እሑድ እሑድ እና በየበዓላቱ ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ስርአተ ቤተክርስቲያንን የሚከታተሉ ሰዎችን ቁጥር ስመለከት በርካታ ከመሆናቸው የተነሳ ምን አይነት የእምነት ስርአት እንዳላቸው ለማወቅ ጉጉቱ ነበረኝ። ከዚህም የተነሳ ወደ ቤተክርስቲያን ቀረብ ብዬ ካህናቱ የሚሰጡትን አገልግሎት ለማወቅ ጣርኩ።

ከዚያም ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ የሚፈጽሙትን ስርአተ ቅዳሴ ተመለከትኩ። በስርአተ ቅዳሴው ላይም ምዕመናኑ የቄሶቹን ተሰጥኦ ሲመልሱ የሚፈጽሙት ድርጊት ምስጢራዊ ፍቺ ምን እንደሆነ ለማወቅ ፈለግሁ።በተጨማሪም ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ የሚፈፅሙት የአከዋወን ስልት፣ የሚናገሩት ንግግር እና የሚጠቀሙትን ቁስ ስመለከት የምን ተምሳሌት?ለምን ዓላማ? የሚሉ ጥያቄዎች ይፈጠሩብኝ ነበር። እንዲሁም ምዕመናኑ ቅዳሴን አስቀድሰው ሲመለሱ እንደነፁ፣ እንደተፈወሱ፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ተገናኝተው የሚፈልጉት ነገር እንደተፈፀመላቸው አምነው ሲመሰክሩ ስሰማ እንዴት ይህ ሊሆን ቻለ? በማለት እጠይቅ ነበር።

ይህም ብቻ ሳይሆን በቤተክህነት ሹመት የተሰጣቸው ግለሰቦች ማህበረሰቡን ከበሽታ የመፈወስ፣ ከሰይጣን እስራት የመፍታት፣ ከኃጢያት መመለስና ማንፃት እንዲሁም በጥሩ ስነምግባር መግራትና ባህላዊ እሴቶችን የማስጠበቅ ስልጣን እንዳላቸው ይታመናል። በመሆኑም ከሰው አቅምና አእምሮ በላይ የሆነን ተግባር የማከናወን ብቃት የሚያስገኝን ሃይል እንዴት አገኙት? በምን አይነት ስርዓትስ ተቀበሉት? ስልጣኑንስ ማን ሰጣቸው?

እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ይህን አይነት ተግባር የሚፈፅሙት ምን አይነት ቃል ኪዳን ቢገቡ ነው? እነዚህ ግለሰቦች በምን አይነት ህይወት አልፈው ለዚህ ስልጣን በቁ? የሚሉ ጥያቄዎች በውስጤ ተፈጠሩ። እነዚህን ለማወቅ በመጓጓቴና ይህ ጉዳይ ደግሞ ትውፊታዊ ስርአትን የያዘ በመሆኑ በክዋኔው ወቅት ያሉ ድርጊቶች ( ስርአቶች) ያላቸው ፎክሎራዊ ገጽታ የጎላ ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ። ከዚያም የእነዚህን ፋይዳ ለመግለጽ ስለፈለግሁ ጥናቱን ለማጥናት ተነሳሳሁ።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ትኩረት ያደረገበት ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ ላይ ብቻ ሲሆን ከስልጣን አሰጣጡ ባሻገር ቅድመ ክዋኔ እና ድህረ ክዋኔ ያሉት ገጽታዎች ከስርአተ ክዋኔው ጋር ተደጋጋፊነት (ተያያዥነት) ያላቸው በመሆናቸው በጥናቱ ቀርበዋል።

አዲስ አበባ የመንበረ ፓትርያርክ መቀመጫ በመሆኗ ስልጣነ ክህነትን የሚሰጡ ጳጳሳት በብዛት ይገኙባታል።ስለሆነም መረጃዎችን በቀላሉና በአግባቡ ለማግኘት ሲባል የጥናቱ ክልል የተወሰነው በአዲስ አበባ ከተማ ነው።በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ጥናቱ የተካሄደባቸው ውስን ቦታዎች በአታ ለማርያም ቤተክርስቲያን፣ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን እና ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ናቸው።ምክንያቱም በበአታ ለማርያም ቤተክርስቲያን የአብነት ትምህርት የሚሰጥበት በመሆኑ ፣ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የጳጳሳት መኖርያ የሚገኝበት እና የዲቁናን ስልጣን በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ሊሰጥ የታቀደ በመሆኑ እና ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ደግሞ የኤጲስ ቆጶስነት ስልጣን የሚሰጥበት በመሆኑ ነው።

## 1.6 በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

የኤጲስ ቆጶስና ስልጣን በሃገራችን በአራት ወይም በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ስርዓት ነው። ከዚህ በፊት የተፈጸመው የሹመት ስርዓት በ 1997 ዓ/ም ከስድስት ዓመት በፊት ነበር። በዘንድሮው ዓመት ይህ ስርዓት ተፈፃሚነቱን ለማረጋገጥ የሚመለከታቸውን ሰዎች ስጠይቅ ከሲኖዶስ ስብሰባ በኋላ እንደሚታወቅ ገለፁልኝ። የሲኖዶስ

ስብሰባው አልቆ በቀጣዩ ቀን (ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም) ጉዳዩን ሳጣራ በዚህ ዓመት ለጵጵስና ሹመት የተመረጡ ቆሞሳት እንደሌሉና ስልጣነ ክህነቱም እንደማይሰጥ ተነገረኝ፡፡

በአርቲፊሻል እና ተፈጥሮ ቅንብር መቼት እንዲከወን ለማድረግ ስሞክር " ስርዓቱ መንፈስ ቅዱስ የሚወርድበት፣የእግዚአብሔርን ፀጋ የሚቀበሉበት ሃይማኖታዊ ስርዓት በመሆኑ ትክክለኛውና ዕውነተኛው ስርዓት ይፈፀማል እንጂ አስመስሎ መከወን አይቻልም" በማለት ገለፁልኝ፡፡ይህም ሁኔታ ጥናቱን ለማጥናት ይገኙቸው ከተነሳኒቸው አላማዎች ውስጥ አንዱ የሆነውንና "ፎክሎር ተለዋዋጭ በመሆኑ ,አሁን ያለውን ስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ በምስል ቀርጾ ማስቀመጥ" የሚለው ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋት ፈጥሮብኛል፡፡

በፎክሎር ጥናት ጊዜ ይህ አይነት ችግር ሲያጋጥም በቦታው ተገኝተው ስርዓተ ክዋኔውን የተከታተሉትን ሰዎች በመጠየቅ መረጃውን ማግኘት እንደሚቻል ጎልድስቲን (1964 ÷83) በገለጸው መሰረት ችግሩን ለመፍታት ሁለት መንገዶችን ተጠቅሚያለሁ፡፡ የመጀመሪያው በቃለመጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በማህበረ ቅዱሳን ኦዲዮ ቪዥዋል ክፍል በቪድዮ ተቀርጾ የተቀመጠ የጵጵስና ስርዓተ ሲመት በመመልከት እና ትንታኔ በመስጠት ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

የጥናት ዘዴ አንድ የምርምር ስራ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ሲሆን የሚገኘውም ከጥናቱ ቲዎሪ ውስጥ መሆኑን ዊሊያም ቶምስ( 1967፡63) ገልጻል፡፡ዘዴዎች በጥናቱ ቲዎሪዎች መሰረት ዳታዎችን ለማግኘትና ቅርጽ ለማስያዝ የሚያስችሉ መንገዶች ናቸው፡፡የጥናት ዘዴ እያደገ ሲመጣ ቲዎሪን ለመቅረጽ የሚያስችል በመሆኑ ዘዴ እና ቲዎሪ ተደጋጋፊ ናቸው፡፡ይህጥናት የስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔን የሚያሳይ በመሆኑ በዋናነት የክዋኔ (performance) የጥናት ዘዴን ( ቲዎሪን) ተከትያለሁ፡፡ይህንን ቲዎሪ ከቀረጹት ውስጥ ሪቻርድ ቦውማን (1983) እና ዳን ቤን አሞጽ (1982) ይገኙበታል፡፡ ይህ ቲዎሪ ተቀርጾ ስያሜውን ከማግኘቱ በፊት አውዳዊ ( contextual) ቲዎሪ ይባል ነበር፡፡ አውዳዊ ቲዎሪ እያደገ ሲመጣ ክዋኔ( performance) ቲዎሪ ተብሏል፡፡ የክዋኔ ቲዎሪ በውስጡ ባህላዊ እና ማህበራዊ አውዶችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ አውዶች ትእምርታዊ ፍቺዎችን ፣ባህላዊ ተቋሞችንና ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚያሳዩ ናቸው፡፡የአንድ ማህበረሰብ ባህል መኖሩ የሚታወቀው ሲከወን (perform ሲደረግ )ብቻ ነው፡፡ክዋኔ በህግ የሚመራ፣ የማኅበረሰብን ልማድ የሚያሳይ እና ትውፊት እንዲቀጥል የሚያስችል ነው ፡፡ ህልውናው የተመሰረተውም በአንድ ማህበረሰብ ትውፊት ወይም ባህል ላይ ሲሆን የሚቀርበውም በድርጊት እና በገለጻ ነው፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ጉዳዮች ተፈጻሚነት ኖሯቸው በቅደም ተከተል እና በድግግሞሽ መከወን ሲችሉ ሥርዓት ይባላሉ፡፡ ሥርዓቶች የማህበረሰቦችን ደንብ፣መመርያ

ትውፊት፣ባህል እና ሌሎችንም ጉዳዮች ገልጸው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህ የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ የሆኑ እሴቶችን ገልጾ ለማሳየት ክዋኔ መሰረታዊ እና ቁልፍ የሆነ መሳርያ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሃሳብ በውስጡ በክዋኔ ጊዜ ሊኖሩ የሚችሉ ባህላዊ፣ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ትእምርቶችን የመተርጎሚያ መንገድ የሆኑ ቲዎሪዎችንም ያካተተ ነው፡፡ እነሱም ተግባራዊ (functional) ፣መዋቅራዊ (structural) እና ትርጉም (Interpritative) ናቸው፡፡ ተግባራዊ ቲዎሪን የቀረጸው ማሊኖዊስኪ (1942) ነው፡፡የዚህ ቲዎሪ አላማ ባህል፣ ማህበራዊ አገልግሎትን ይሰጣል፡፡በባህል ውስጥ ለማህበረሰቡ የማይጠቅምና ዋጋ የሌለው ነገር የለም የሚል ሃሳብ አለው፡፡መዋቅራዊ ቲዎሪ በራድክሊፍ ብራውን (1952 ) የተቀረጸ ሲሆን ዋና ሃሳቡም የአንድ ማህበረሰብ ስርአት ከሌሎች የእምነት እና የባህል አይነቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ወይም ተዛምዶና ቅንጅት መመልከት እና ያለውን ፋይዳ ማመልከት ነው፡፡የትርጉም ቲዎሪ በ1973 በክሊፎርድ ጊርቲዝ የተቀረጸ ሲሆን ይዞት የተነሳው ዓላማ የአንድ ማህበረሰብ እሴት፣ስርዓት እና የአኗኗር ደንብ በምሳሌዎች የተበጁ ናቸውና መተርጎም አለባቸው የሚል ነው፡፡

ክዋኔ አውድን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ምክንያቱም በሥርዓተ ክዋኔው ወቅት ያሉት ነገሮች ሁሉ (ጊዜው፣ቀኑ፣ ቦታው፣ ለክዋኔው የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣የሰዎች ሁኔታ ፣አለባበስ……) ለአንድ አላማ ተብለው የሚቀርቡ እንጂ ያለምክንያት የሚፈጸሙ ነገሮች ስለማይኖሩ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ቲዎሪ አውዳዊ( contextual approach) በመባልም ይጠራል፡፡ስለዚህ በስርአተ ክዋኔው ወቅት ትእምርታዊ ፋይዳ ያላቸው ድርጊቶችን ለመተርጎም፣የክዋኔን ፋይዳ ለመግለጽ፣ ስርአተ ክዋኔው የሚፈጸምበትን መቼት ለመተንተን፣የስርአት አሰጣጡን ቅደም ተከተልና የስልጣነ ክህነትን መዋቅራዊ ሂደት ለማሳየት እነዚህን ቲዎሪዎች ተጠቅሜያለሁ፡፡

## 1.8 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ቀዳማይ እና ካልአይ የመረጃ ምንጮች አገልግሎት ላይ ውለዋል፤ በቤተመጻሕፍት ውስጥ ያሉ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጽሑፎች፣ ቲዎሪዎች እና ተዛማጅ የጥናት ሥራዎች በስፋት ተቃኝተዋል፡፡

በስልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ወቅት ምን ለምንና እንዴት እንደሚባልና ምን እንዴት እንደሚደረግ በትኩረት መመልከት እና መገንዘብ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ በውል

ለማስረዳት ያስችላል። ስለሆነም ምልከታ ለዚህ ጥናት ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ተፈጥሯዊ አውድን በመጠቀም ነው።ምልከታውን ምሉዕ ማድረግ ይቻል ዘንድ የመረጃ ስብሰባው በቪዲዮ እና በቴፕሪከርደር መሣሪያዎች ታግዟል።

በምልከታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያልተቻለውንና ከምልከታ አምልጦ የቀረውን እንዲሁም አጥኚው ከዕይታው በተጨማሪ ለመረዳት የፈለገውን ጉዳይ የሚመለከተውን ክፍል መጠየቅ ይኖርበታል። በዚህ ጥናትም በሥርዓተ ክዋኔው ወቅት ምን ለምን እንደሚደረግ፣የትእምርቶች ተምሳሌት እና ትርጉም ምን እንደሆነ ለመረዳት ፣ በቪዲዮ ተቀርጸው የተቀመጡትን በመመልከት እና በቃለመጠይቅ መረጃዎችን ለማግኘትና ለመሰብሰብ ተችሏል።

## 1.9. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በቡድን ውይይት ከተሰሰቡ በኋላ ትንታኔውንና ትርጓሜውን ለማቅረብ የሚከተለውን የአተናተን ዘዴ ተጠቅሜያለሁ።

በቅድሚያ ከመስክ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በአይነት በአይነት ለየኋላቸው። እነዚህ በአይነት የተለዩት መረጃዎች ሦስት ሲሆኑ እነሱም ቅድመ ክዋኔ፣ ክዋኔ እና ድህረ ክዋኔ ያሉ ገጽታዎች ናቸው። በእያንዳንዱ ደረጃዎች ውስጥ የተፈፀመውን ሥርዓት ለመተንተን በቅድሚያ በምልከታ ከዚያም በቃለ መጠይቅ ያገኘኋቸውን መረጃዎች በዝርዝር በወረቀት ላይ አሰፈርኩ። ለጥናቱ የመረጥኩትን የአጠናን ዘዴ እና የቲዎሪ አቅጣጫ መሠረት በማድረግም የተፈፀሙትን ክዋኔዎች አንድ በአንድ ገለፅኩ። በቃለ መጠይቅ ያገኘኋቸውንም እንዲሁ የአከዋወን ቅደም ተከተላቸውን በመጠበቅ ዘረዘርኩ። የመረጥኩት ገላጭ የመረጃ ማቅረቢያ ስልት ሥርዓተ ክዋኔው ቅደም ተከተሉን ጠብቆ እንዴት እንደተፈፀመ ለመግለፅ የረዳኝ ሲሆን የክዋኔ የቲዎሪ ዘዴ መሠረት በሚያደርጋቸው ነጥቦች ማለትም ማን? ምን? እንዴት? መቼ? የት? ለምን? በሚሉ ጥያቄዎች ላይ ተመርኩዤ በትንታኔው ላይ የሚገኙትን ትእምርቶች በመመርመርም የያዙትን ተምሳሌት ተረጐምኩ። እንዲሁም በሥርዓተ ክዋኔው ውስጥ የሚታዩትን የፎክሎር ዘርፎች በመለየት ሃገረሰባዊ ልማዱ እንዴት እንደተገለፀ አስረዳሁ። ከዚያም ሥርዓተ ክዋኔው የሚያስገኘው ፋይዳ ምን እንደሆነ በመመርመር የክዋኔን ሙያ( function) ገለፅኩ።

# ምእራፍ ሁለት

## 2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ላይ ጥናት ለማድረግ በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉ  የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች፣ መጻህፍት እና በመጽሄት ላይ የወጡ መጣጥፎች ተቃኝተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የተጻፉና ከዚሁ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስራዎች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የፍሬሕይወት ባዩ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሀይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ" በሚል ርዕስ በ 2000 ዓ.ም. የቀረበው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ታደሰ አይችሉህም" በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ሥርዓት እና የገዳማውያን የዕለት ከዕለት ህይወት ከትዕምርታዊነቱ አንፃር በዝቋላ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳማት" በሚል ርዕስ በ 1999 ዓ.ም. የቀረበ ነው፡፡

ለቢ.ኤ. ዲግሪ ማሟያና በተዛማጅ ጥናት ፅሁፍነት የተቃኘው የሙላው አለበል" በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክህነት የሹመት ስሞች" በሚል ርዕስ በ1981 ዓ.ም. የቀረበ ነው፡፡

እንደዚሁም በመጽሄት ላይ የቀረቡ መጣጥፎች ሲፈተሹ የኤፍሬም ይስሃቅ በ "Journal of Ethiopian Observer" መጽሄት ላይ vol xiv No 4 "Social Structure of the Ethiopian Church" በሚል በ 1971 ዓ.ም. ያቀረቡት ጥናት ይገኛል፡፡

ሌሎች በተዛማጅ ጽሑፍነት የተቃኙት በመፅሐፍ መልክ ታትመው የወጡ ናቸው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት በርካታ ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል ከማስተዋወቅ ይልቅ በቅኝቱ ውስጥ መግለጽ የተሻለ ይሆናል፡

### 2.1. ያልታተሙ ጥናት ጽሑፎች

በፍሬህይወት ባዩ (2000)" በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅዱሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ" በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ሁለት ጉዳዮችን ይዟል፡፡ እነሱም የንዋያተ ቅድሳት ሀይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ገፅታዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ሁለት ገጽታዎች ማሳየት የጥናቱ አቢይ ዓላማ ነው፡፡

ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ተግባራዊ አድርጓል ለማለት የሚያስችሉ ነጥቦች አሉ፡፡ ይህም የጥናቱ ዓላማ በዋናነት ትኩረት ያደረገው የንዋየ ቅድሳትን ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ገጽታቸውን ገልፆ ለማሳየት መቻሉ ነው፡፡ ይህንን ማሳየት በምዕራፍ አራት የንዋየ ቅዱሳት ሀይማኖታዊ ገጽታ በሚለው ውስጥ ስለንዋየ ቅድሳት ምንነት፣ ስለንዋየ ቅድሳት አሰራር አገልግሎና ተምሳሌታዊነታቸው እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ አምስት ላይ የንዋየ ቅዱሳት ፎክሎራዊ ገጽታ መቅረቡ በዓላማው ላይ “ፎክሎራዊ ገጽታን ለማሳየት” የሚለው ተግባራዊ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ በዚህ ውስጥ ስለ ንዋያተ ቅድሳት ቁሳዊ ባህል በተመለከተ ሀገረሰባዊ እጅ ሥራ፣ ሀገረሰባዊ ሥዕል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና እና ሀገረሰባዊ ልብስ በማለት ተከፍለው መቅረባቸው ዓላማው በዋናው የጥናቱ ክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባር ላይ እንደዋለ የሚያሳይ ነው፡፡

ፍሬህይወት የጥናት ሥራዋን ስታከናውን የንዋያተ ቅድሳቱን አሰራር፣ አጠቃቀም፣ አያያዝና የት እንደሚገኙ ገልፃለች፡፡ የንዋያተ ቅድሳቱን ሀይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ መርምሮ ለማሳየት ያስችላት ዘንድም አሰሳና ገላጭ ዘዴዎችን ተጠቅማለች፡፡ መረጃዎችን በቃለመጠይቅ በምልከታ እና በሰነድ ምርመራ ሰብስባለች፡፡ እነዚህን መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መጠቀሟ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳዮች በጥልቀት መመልከቷን ያሳያል፡፡ፍሬህይወት የተጠቀመችበትን የቲዎሪ አቅጣጫ ሳትጠቅስ ብታልፍም የንዋየ ቅድሳቱን ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ ለማሳየት አውዳዊ መቼት መጠቀሟን እንዲሁም ስለንዋየ ቅዱሳቱ ተምሳሌት ምንነት መግለጿን ከጽሁፉ መረዳት ይቻላል፡፡ ጥናቱ በመስክ መረጃ ላይ ስለተደገፈ ክዋኔ (Performance) ተግባራዊ (functional) እና ትርጉም (interpretative) የቲዎሪ አቅጣጫዎችን ተከትላለች ማለትም ያስችላል፡፡ የእኔ ጥናት እነዚህን የፎክሎር ማጥኛ አቅጣጫዎች የተከተለ በመሆኑም ከፍሬህይወት ጥናት ጋር ተመሳሳይ አካሄድ (ቲዎሪ)አለው፡፡

ፍሬህይወት ከጥናት ርዕሷ ጋር ዝምድና ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎችን በተመለከተ በሁለተኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ የቀረቡ አለመኖራቸውን ገልፃ በቢኤ ደረጃ የተሰሩ የሁለት ሰዎችን የጥናት ጽሑፎች አቅርባለች፡፡

በመጀመሪያ ያቀረበችው ዐቢይ ብርሃኑ (1963) " የህንፃ ቤተክርስቲያን የንዋየ ቅድሳትንና የአልባሳት ስሞች" በሚል ያቀረበውን ጥናት ሲሆን በውስጡም የጥናቱን ዓላማ፣ ስለንዋየ ቅድሳት ማብራርያ ማቅረቡንና የጥናት አቀራረብ መንገዱን ገልፃለች፡፡ ነገር ግን ከእርሷ ጥናት ጋር በምን መልኩ እንደሚመሳሰል እና እንደሚለያይ ማብራሪያ አላቀረበችም፡፡ ስለሆነም አንባቢ በዐብይ እና በእሷ ጥናት መካከል ያለውን ክፍተት በቀላሉ እንዳይረዳ ያደርጋል፡፡ የእሷ ጥናት ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ገጽታን ከመግለፅ አንፃር ያለውን ሁኔታ ብትጠቁም አንባቢ ለፎክሎር የሚኖረውን ጽንሰ ሀሳብ ይበልጥ እያዳበረ እና በአብይ ጥናት ደግሞ የቀረበው ከስነልሳንም ይሁን ከሌላ ጉዳይ መዳሰሱን በማየት በአንድ ነገር ላይ የተለያዩ ጥናቶች ሊካሄድ እንደሚችል ጎራ እየለየ የሚገነዘብበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻል ነበር፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ላይ ያቀረበችው የብርሀኑ "Debre Tsige St. marry church" (945-2000) በሚል ርዕስ በ 1993 ዓ.ም. ለታሪክ ክፍል ያቀረበውን ነው፡፡ በዚህ የጥናት ርዕስ ውስጥ ስለ ደብረ ፅጌ ማርያም ቤተክርስቲያን አመሰራረት እንዲሁም ስለቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ አስተዳደር መግለፁን በመጠቆም ከጥናቷ ጋር ያላቸውን ተመሳስሎ እና ልዩነት ገልፃለች፡፡

"የጽሁፎች ዳራ" በሚል ርዕስ ስለሃይማኖትና ፎክሎር፣ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ ስለንዋየ ቅድሳትና አልባሳት እና ስለተምሳሌት በሀይማኖት ውስጥ የሚሉ ፅንሰሀሳቦችን በሰፊው ዳሰሳለች፡፡ እነዚህም ሀይማኖትና ፎክሎር እንዴትና ከምን አንፃር መታየት እንደሚገባቸው የሚጠቀሙ በመሆናቸው ለጥናቱ አስፈላጊ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የንዋያተ ቅድሳት ሀይማኖታዊ ገጽታ ከተለያየ አቅጣጫ በተለያዩ ጸሃፊዎች ቀርቧል፡፡ በጥናቱ የሃይማኖትን እና ፎክሎርን ፅንሰሀሳብ በማገናኘት ንዋየ ቅድሳት የሚባሉት ቁሶች ከሀይማኖታዊና ከፎክሎራዊ ፋይዳ አንፃር የሚይዙትን ቁሳዊና መንፈሳዊ ሃብት በመለየት መጠቆም መቻሉ የጥናቱ ጠንካራ ክፍል ነው፡፡ በተለይ ስለንዋየ ቅድሳት ፎክሎራዊ ገጽታ ሲተነተን ቁሳዊ ባህሉን፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ገጽታውን፣ ሀገረሰባዊ ልማዱን እና ተለዋዋጭነቱን ማሳየቱ የፎክሎርን ገፅታ እና ህልውና በንዋየ ቅዱሳቱ ላይ ለመግለፅ አስችሏል፡፡

ፍሬህይወት በጥናቷ የስልጣነ ክህነትን ምንነት እና አይነቶች እንዲሁም የካህናትን ተግባር ገልፃለች። የንዋየ ቅድሳት ምንነትም፣ ተምሳሌታዊ ፋይዳቸውና ሌሎችም ጉዳዮች ተዳሰዋል። የዚህ ጥናት ዋና ጉዳይ ስልጣነ ክህነት በመሆኑ እና በውስጡም ስለ ካህናት ምንነት፣ ስለክህነት ደረጃዎች፣ ስለካህናት ተልዕኮ /አገልግሎት/ እንዲሁም በስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ወቅት አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት ተምሳሌታዊ ፋይዳ የሚገልጽ ስለሚሆን የተጠቀሱት ጉዳዮች ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ የፈጠሩ ናቸው።

ይህ ጥናት የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔውን፣ ስልጣነ ክህነቱን በሚቀበሉ ግለሰቦች ቅድመ እና ድህረ ሥልጣን የሚኖራቸውን የህይወት ገጽታ፣ ወግ ማድረግ (rite of passage) የሚገልጽ በመሆኑና ፍሬህይወት ግን የተጠቀሱትን ባለመዳሰሷ የተለየ ያደርገዋል።

ታደሰ አይችሉህም (1999) "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ሥርዓት እና የገዳማውያን የዕለት ከዕለት ህይወት ከትዕምርታዊነቱ አንፃር" በሚል ርዕስ ጥናቱን ሲያቀርብ የጥናቱ ዓላማዎች በማለት ያመለከታቸው በገዳማት ውስጥ የሚኖሩ መነኮሳትን የየዕለት ህይወት መመልከት፣ ገዳማውያኑ የሚጠሙባቸውን መገልገያ ዕቃዎች፣ የፀሎት ሥርዓታቸውን፣ የአስተዳደርና የሥራ መዋቅሩን ተምሳሌት መመርመር እና የገዳማውያኑን የዕረፍት፣ የግንዘት እና የፀሎት ፍትሀት ምሳሌነቱን መመርመር የሚሉ ናቸው። በእነዚህ ዓላማዎች እና በጥናቱ ርዕስ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር በቅድሚያ ጥናቱ ሁለት ርዕሰጉዳዮችን እንደሚያመለክት መገንዘብ ይቻላል። የመጀመሪያው "የምንኩስና ሥርዓት" የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "የገዳማውያኑ የዕለት ከዕለት ህይወት ከትዕምርታዊነቱ አንፃር" የሚለው ነው።

በጽሁፉ የጥናቱ አላማዎች ሆነው የቀረቡት የገዳማውያኑን የዕለት ከዕለት ህይወት ከትዕምርታዊነቱ አንጻር ሚለውን የጥናቱ ክፍል የሚያመለክቱ ሲሆን። የምንኩስናን ሥርዓት በተመለከተ የቀረበ ዓላማ ባለመኖሩ በጥናቱ አንድ አቢይ ጉዳይ የተዘነጋ ይመስላል።

ታደሰ የጥናት ስራውን ለማከናወን የተከተለው አቅጣጫ Symbolic interaction Theory (ትዕምርታዊ መስተጋብራዊ ቲዎሪ) ነው። ይህን የቲዎሪ አቅጣጫ መከተሉ በምንኩስና ሥርዓት እና በገዳም ህይወት ውስጥ የሚታዩ ተምሳሌታዊ ጉዳዮች ምን ከምን ጋር ውክልና

እንዳላቸው ዘርዝሮ ሊያመለክትበት ይችላል አመልክቶበታልም፡፡ እንዲሁም ታደሰ የክዋኔ (performance) ቲዎሪ መጠቀሙን ሳይገልጽ ቢያልፍም በጥናቱ የሥርዓተ ምንኩስና አሰጣጥ የተካተተበት በመሆኑ ይህ የቲዎሪ አቅጣጫ ተግባራዊ መደረጉን መጠቆም ይቻላል፡፡ በእኔ ጥናት የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ ሲጠና እነዚህ የቲዎሪ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡በመሆኑም ከታደሰ የጥናት አቅጣጫዎች ጋር ተዛማጅ ናቸው፡፡

ታደሰ የጥናቱን ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ በተመለከተ የክርስትና ሀይማኖት ታሪካዊ መነሻ በኢትዮጵያ፣ የገዳምና የምንኩስና ህይወት በአለም አቀፍ እና በኢትዮጵያ የተጀመረበትን ታሪካዊ ዳራ የተለያዩ ምሁራን የሰጡት ሀሳብ በማስፈር ማብራሪያ አቅርቧል፡፡

የተዛማጅ ጥናቶችን ቅኝት ሲያደርግ የተመለከታቸውንም የውጪ ዜጎች እና በኢትዮጵያ የተጠኑ ጥናቶች በማለት በሁለት ክፍሎ አቅርቧል፡፡ በውጪ ዜጎች ከተጠኑት ጥናቶች በመጀመሪያ ቅኝት ያደረገው የካፕላን (1982) “The Monastic Holy Man and the Christianization of Early Solomonic Ethiopia” በሚል ርዕስ የቀረበውን ሲሆን በሁለተኛ ላይ የተመለከተው የስፔንስሮ (1993) “The Monastery of Abeya Fogy Qysqwam in Wollo” በሚል ርዕስ ያቀረበውን ጥናት ነው፡፡ ታደሰ በኢትዮጵያውያን የተጠኑ ጥናቶችን መቃኘቱን ገልጾ እነሱም የሚከተሉት መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡ ሀጎስ (1964) "ገዳማዊ ህይወት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን" መንግስቱ (1999) "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የደብረሊባስ ገዳም ሚና" መዝገቡ (2001) "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልማዳዊ አውድ የገዳማዊ ህይወት መንፈሳዊ ልማድ"፣ ሚካኤል (2002) "በ20ኛው መቶ ክፍለዘመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ገዳማዊ ህይወት እና ተዛማጅ ችግሮች"፣ ኃይለማርያም (1991) " የአዲስ አበባ ገነተ ኢየሱስ ገዳም"፣ ሃብታሙ(1998) "የመርጡለማርያም ገዳም " እና ጌቱ (1999) “የወለተ ጴጥሮስ ገዳም” መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡

በእነዚህ አጥኚዎች ሥራ የየገዳማቱ ታሪክ የቀረቡባቸው፣ ስለክርስትና አመጣጥ እና የገዳማት አጀማመር እንዴት እንደሆነ መግለጻቸውን እንደዚሁም የመነኮሳትን ጸሎትና አለባበስ፣ ሥራ እና ሌሎችን በተመለከተ ማብራሪያ ማቅረባቸውን በዚህም ከእሱ ጥናት ጋር እንደሚዛመዱ ጠቁሟል፡፡

ታደሰ በጥናቱ በኢትዮጵያ የሚገኘውን የምንኩስና እና የገዳም ህይወት በመግለፅ በዘመኑ ያለውን የገዳም ውስጥ አኗኗር፣ ፍልስፍና፣ ህይማኖታዊና ማህበራዊ ገፅታውን እንዲሁም ትእምርታዊ ውክልናውን ገልጿል፡፡ ይህም በገዳም ህይወት ያለውን መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብት፣ ዕውቀት፣ ፍልስፍና እንዲሁም ለህይወት ያላቸውን ትርጉም ገልጾ ማሳየቱ ጠንካራ ጎኑ ነው፡፡

ከዚህ በፊት ለመግለፅ እንደተሞከረው በጥናቱ ውስጥ የምንኩስና አሠጣጥ ሥርዓት እንደ አቢይ ጉዳይ በመታየት በጥናቱ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ራሱን ችሎ መቅረብ ነበረበት፡፡ ሥርዓቱ የምንኩስናን ህይወት የሚመራ፣ በፊት ከነበሩበት ወደሌላ የህይወት አቅጣጫ የሚያሻግር በመሆኑ የሥርዓቱ ክፍል በዝርዝር መጠናት ይገባዋል፡፡ ሁልጊዜ በምንኩስና ህይወት ሲኖሩ እንደመርህ ሊጓዙበት የሚያስችላቸው በሥርዓቱ ላይ የተፈፀመው ክዋኔ ነው፡፡ በክዋኔው የሚፈፀመው ማንኛውም ድርጊት በቀጣይ ህይወታቸው ውስጥ ይዘውት ወይም ጠብቀውት የሚጓዙበት አቅጣጫ የሚያመለክታቸው ነው፡፡ ይህ ዋና ጉዳይ በጥናቱ ለመጠቀስ ቢሞከርም እንኳ ራሱን ችሎና ቀጥተኛ መስመር ይዞ አይደለም፡፡ ይህም በጥናቱ ውስጥ አንባቢ በጥልቀት ማወቅ የሚፈልገውን ጉዳይ እንዳያገኝ ስለሚያደርግ ክፍተት ይፈጥራል፡፡

በጥናቱ ውስጥ የምንኩስና ስርዓት እና የገዳማውያንን የዕለት ከዕለት ህይወት ሲገለፅ ስለምንኩስና ሥርዓት አቀባበል፣ ስለመነኮሳት ገዳማዊ ህይወት፣ ስለፀሎት እና የአመጋገብ ሥርዓታቸው፣ ስለገዳማውያ አለባበስ እና ሌሎችም ጉዳዮች ተገልጿል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች መገለጻቸው ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ የሚያመሳስላቸውም ነገር ሥልጣነ ክህነት ሥልጠና የሚባሉት ዲቁና፣ ቅስና እና ጵጵስና በመሆናቸው እና የጵጵስና ስልጣን ለመቀበል የሥርዓት ሂደቱ ከምንኩስና ጋር የሚያያዝ በመሆኑ ነው፡፡ የጵጵስና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓት ክዋኔውን በምመለከትበት ጊዜ ቅድመ ጵጵስናን (ስርዓተ ምንኩስና) መመልከት አንዱ የጥናቱ ክፍል በመሆኑ የታደሰ ጥናት በዚህ መልኩ ተዛምዶ አለው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ታደሰ በጥናት ዳራው የምንኩስናን አጀማመር ፣ ጳጳሳት ወደሀገራች መምጣትና መሾም እንዴት እንደቻሉ ገልጿል፡፡ ይህም የስልጣነ ክህነት አጀማመርን በተመለከተ ከሚነሳው ርዕሰ-ጉዳይ ጋር ግንኙነት አለው፡፡

የእኔ ጥናት ከታደሰ ጥናት የሚለየው የቤተክህነት ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ ላይ ትኩረት የሚያደርግ እንዲሁም የቅድመ እና ድህረ ክህነት ገጽታዎችን የሚመለከት በመሆኑ ሲሆን የታደሰ ጥናት እነዚህን ገጽታዎች ባለመመልከቱ ነው።

ሙላው አለበል (1982) "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክህነት የሹመት ስሞች" በሚል ርዕስ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፉን አቅርቧል። ጥናቱ ዓላማዎችም የቤተክህነት የሹመት አሰጣጥ ከማህበረሰቡ፣ ከቋንቋውና ከሃይማኖቱ ጋር ያለው ግንኙነት በምን ደረጃ ላይ እንደሆነ ማሳወቅ፣ የቤተክህነት የሹመት ስሞችን በፅሁፍ መዝግቦ ማስቀመጥ፣ የቤተክህነት ሹመት ስሞች አሰጣጥ ራሱን ችሎ ተጠንቶ ሲቀርብ የአገራችን ታሪክ ለማሳወቅ የበኩሉን እገዛ እንደሚያደርግ መጠቆም፣ በዚህ ጥናት ዙርያ ምርምር ለማድረግ ለሚነሱ ወገኖች ይህ ጥናት እንደመነሻ ሆኖ እገዛ እንደሚያደርግ መግለጽ የሚሉ ሲሆኑ ተግባራዊነታቸውም በጥናቱ ዋና ክፍል ታይቷል።

አጥኚው የጥናቱ ዓላማ ያደረገው የኢትዮጵያ ቤተክህነት የሹመት ስሞችን ምንነት፣ አይነት እና ያላቸውን ፋይዳ አብራርቶ መግለጽ በመሆኑ የተከተለው ገላጭ እና ተንታኝ የአጠናን ዘዴዎችን ነው።
ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ሁለት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተጠቅሟል። የመጀመሪያው በፅሁፍ ያሉ ሰነዶችን መመርመር ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ቃለ መጠይቅ ነው።

ሙላው በጥናቱ ውስጥ ይህንን አይነት የቲዎሪ አቅጣጫ ተከትያለሁ በማለት የገለጸው ነገር የለም። ጥናቱን በመመልከት ግን መዋቅራዊ ቲዎሪ (structural theory) አቅጣጫን እንደተከተለ መገመት ይቻላል። ይኸውም ጥናቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን የስልጣን ተዋረድ ያመለከተ እና በእያንዳንዱ የስልጣን እርከን ያለውን ስምና ተግባር ከማህበራዊ ስነልሳን አኳያ የሚያሳይ በመሆኑ እና መዋቅራዊ ቲዎሪ (Structural theory)ደግሞ የአንድን ህብረተሰብ አደረጃጀትና አገነባብ ሁኔታ በሚመለከት ትንታኔ የሚሰጥበት በመሆኑ ነው።

ሙላው የቤተክህነት ስሞች ከሥነማህበራዊና ሥነልሳን አኳያ ጥናት ሲያደርግ በጥናቱ ርዕስ ዙርያ የተሰሩ ሦስት ተዛማጅ ጥናቶችን ለመቃኘት ሞክሯል። ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ

ጥናታዊ ፅሑፎች ሲሆኑ አንዱ በመፅሃፍ መልክ ታትሞ የወጣ ነው። ሁለቱ ጥናታዊ ጽሑፎች የአረጋ ኃ/ሚካኤል (1960) "የማዕረግ ስሞች" እና (1984 እ.ኤ.አ.) "The social basic and social change up on official titles in Amharic" በሚል ርዕስ ከማህበራዊ ሥነ ልሳን አኳያ በመጣጥፍ መልክ ያቀረቧቸው ናቸው። እንዲሁም በመጽሐፍ መልክ የቀረበው የሃብተማርያም ወርቅነህ (1963) "ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት" በሚል ርዕስ የታተመው መጽሃፍ ነው።

ሙላው እነዚህ ሦስት ተዛማጅ ጽሑፎች ርዕሳቸውን፣ አጥኚውን እና ዓመተምህረቱን ከመግለፅ ውጪ በውስጣቸው የቀረበውን ጉዳይ ጠቅለል አድርጎ አላቀረበም። (የአጥኚዎቹ ትኩረት ምን እንደሆነ አልጠቆመም።) እነዚህ ጥናቶች ከራሱ ጥናት ጋር ያላቸውን ልዩነት በተመለከተ ግን የሹመት አጀማመርና መስፋፋት መረጃ በማቅረቡ፣ የሹመት ስሞች አሰያየም ከማህበራዊ ሥነልሳን አኳያ መመርመሩን፣ የጥምቀት ስሞችን መግለፁ፣ የጳጳሳትን የተፀውዖ ስሞች እንዲሁም ማህበረሰቡ ለሹመት የሚሰጠውን ክብርና እምነት በመግለፁ ከሌሎች እንደሚለይ ገልጿል።

ንድፈሃሳባዊ ዳራዎችን በተመለከተ ሁለት ርዕስ ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ"የሹመት ምንነት" እና "ሹመት ከማህበራዊ ሥነልሳን አኳያ" በማለት ማብራሪያ አቅርቧል። በጥናቱ ውስጥ ለመግለፅ ከተፈለጉት በርካታ ጉዳዮች አንፃር የሁለት ፅንሰ ሃሳቦችን ዳራ ብቻ ማቅረቡ እንደደካማ ጎን ሊታይ ይችላል።

ከስነልሳን ጥናት አኳያ ስሞች በማህበረሰቡ የሚሰጡትን ፋይዳ ለመግለጽ የአንድን ተቋም ገፅታ በመምረጥ ያለውን ዕውነታ በተጨባጭ ማሳየት መቻሉ ጠንካራ ጎኑ ነው። ስሞች በተለይ የሹመት ስሞች ተሿሚውን በተሾመበት የሥራ ዘርፍ ጠንክሮ እንዲሰራ የሚያደርጉ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ እና በተሿሚዎች መካከል ያለውን ደረጃ ወይም እርከን የሚያመለክቱ ናቸው። ይህንን ለማመልከት አጥኚው የተጠቀመው አካሄድም አንድ ተሿሚ የሚያልፍባቸውን የህይወት እርከኖች በመዳሰስ ነው። በመሆኑም ስራው ጠንካራ ነው ማለት ይቻላል።

ሙላው በጥናቱ ውስጥ ስለሹመት ስሞች ሲገልፅ የሹመት አይነቶችን እና ሹመት ከመሰጠቱ በፊት ማሟላት የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች እንዲሁም እነዚህ የሹመት ስሞች የሚሰጡትን ፋይዳ በመግለፁ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። የሙላው ጥናት በዋናነት ሰው በቋንቋ አማካይነት ምኞቱን፣ ፍላጎቱንና ተስፋውን ከሚገልፅበት አንዱ ስያሜ መሆኑ

ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ ይህ በሁለታችን ጥናት መከካከል የሚታዩ ልዩነቶች ናቸው።

## 2.2. የታተሙ ጽሑፎች

**ኤፍሬም ይስሃቅ** (1971) "Social structure of the Ethiopian church" በሚል ርዕስ በ Journal of Ethiopian observer" vol xiv No 4 መጽሄት ላይ ያቀረቡት መጣጥፍ በአምስት ክፍሎች ተከፍሎ የቀረበ ነው። በመጽሄቱ ውስጥ የቀረቡት ዋና ዋና ጉዳዮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አመሰራረት፣ ታሪክ፣ ዘመናዊ ትምህርት፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንና ባህሏ፣ ቤተክርስቲያንና መንግስት ያላቸው ግንኙነት፣ ቤተክርስቲያን የሥልጣን እና የትውፊት (ባህል) አርአያ መሆኗ፣ ቤተክርስቲያን ማህበረሰቡን ከማስተማርና በስነምግባር ከማነፅ ጋር ያለው ሁኔታ፣ የቤተሰብ አመሰራረት፣ ሃይማታዊና ባህላዊ ልማዶች (ወጎች) የሚሉ ናቸው።

የጥናቱ ዓላማ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሰለጠነች፣ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ እሴቷ ጉልቶ የሚታይ ነው ብለው ለሚያስቡ እና ለሚያምኑ ሰዎች እውነታውን ገልጦ ማሳየት ነው። የጥናቱ ዋና ክፍልም የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳይ በመሆኑ የጥናቱ ርዕስ፣ ዓላማና በጥናቱ የቀረበው ዋና ጉዳይ የተዛመዱ ናቸው።

ጥናቱ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከማህበረሰቡ፣ ከመንግስት፣ ከሌሎች ሃይማኖቶች፣ ከዘመናዊ ትምህርት እና ሌሎችን ጉዳዮች ገልፆ የሚያሳይ በመሆኑ ገላጭ እና ተንታኝ የጥናት ዘዴን ተጠቅሟል።

ኤፍሬም ይስሃቅ ይህንን ጥናት ሲያቀርቡ ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ማህበረሰብ አደረጃጀትና የአደረጃጀቱንም ፋይዳ መግለጽ በሚል ለሃቫርድ ዩኒቨርሲቲ ያቀረቡትን ጥናት ለዚህ ሥራ መቃኘታቸውን ገልጸዋል።

በዚህ ጥናት በርካታ ጉዳዮች ቀርበዋል።በተለይ የኢትዮጵያ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ገጽታዎች በጥሩ ሁኔታ የቀረቡበት በመሆኑ ጥናቱን ለሚያነብ ግለሰብ ኢትዮጵያ የነበራትን ገጽታ በሚገባ መመልከት ይችላል።

ጽሑፉ የቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ ጉዳዮች፣ የማህበረሰቡን ወግ እና እሴት ከሃይማኖት እና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር አዛምዶ ያቀርባል። በመሆኑም ለታሪክ ተመራማሪዎች፣ ለተለያዩ

አብያተክርስቲያናት፣ ተቋማት እንዲሁም የኢትዮጵያን ሃይማኖት ጥንተ ነገር ማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ በቂ መረጃ ይሰጣል ማለት ይቻላል።

ይህ ጥናት የቀረበበትን የቲዎሪ አቅጣጫ አጥኚው ይህ ነው በማለት ሊገልፁት ባይችሉም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን፣ የመንግሥት፣ አስተዳደርን፣ ሌሎች ሃይማኖቶችን፣ ማህበረሰባዊ ገጽታዎችን፣ ልማድን፣ ዘመናዊ ትምህርትን እና ሌሎችንም ጉዳዮች ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጋር እያገናኘ ማቅረብ በመቻሉ የrelative፣ structural እና comparaticve theory አቅጣጫን የተከተለ ነው ማለት ይቻላል።

ይህ ጥናት በዋናነት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያዛምደው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ያለውን የአስተዳደር ሁኔታ በሚገልጹበት ክፍል ስለዲያቆናት፣ ቀሳውስት ጳጳሳት እና ፓትሪያርክ ምንነት፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ቦታ እና ተግባር መግለፅ መቻሉ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ የሹመት አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ በጥናቱ አለመካተቱ ነው።

ፒ.ኬ. ማቲው (1970) “The church of Ethiopia a panaroma of history and spiritual life” በሚል መጽሐፍ ውስጥ The Hierarchy የሚል ጽሁፍ አቅርቧል ። ስርግው ሃብለስላሴ፣ ታደሰ ታምራት፣ ሃይለገብርኤል ዳኜ፣ ቪ.ሲ. ሳሙኤል እና አዳሙ አማረ በመጽሃፉ ውስጥ የተለያዩ ፅሁፎችን አቅርበዋል። እነዚህ አጥኚዎች በፅሁፋቸው ለማቅረብ የሞከሩት ስለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ እና መንፈሳዊ ህይወት ነው።

ከአጥኚዎቹ መካከል የፒ.ኬ. ማቲው ጽሑፍ ለዚህ ጥናት ጽሑፍ በተዛማጅነት የቀረበበት ምክንያት ጥናቱ ስለቤተክርስቲያን የሥልጣን ተዋረድ የሚገልፅ በመሆኑ ነው።

ፒ.ኬ. ማቲው ጽሑፉን ሲያቀርብ በውስጡ ያካተታቸው ዋና ዋና ጉዳዮች “Hierarchy” /የሥልጣን ተዋረድ/ ምንነት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የስልጣን ተዋረድ/የስልጣን ክፍፍል አይነት/፣ ስለ ምዕመናንና ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ናቸው።

ማቲው ይህንን ፅሑፍ ሲያቀርብ አላማው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ያለውን የሥልጣን ተዋረድ ለማሳየት ነው። በመሆኑም የሥልጣን አይነቶቹ ኤጲስ ቆጶስ፣ ቄስ እና ዲያቆን መሆናቸውን ተግባራቸው ጋር ገልጿል። ፒ.ኬ. ማቲው ጥናቱን ሲያቀርብ የተከተለው አካሄድ ግልፅና ቀጥተኛ ቅደም ተከተላዊነቱን የጠበቀ በመሆኑ አንባቢ የጥናቱን ዋና ጉዳይ በቀላሉ ለመረዳት ይችላል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የስልጣን ተዋረድ አካሄድ እንዴት እንደሆነ በማብራራት ያቀረበ በመሆኑ ጥናቱ ገላጭ እና ተንታኝ ስልትን የተከተለ ነው፡፡ የፒ.ኬ. ማቲው ጽሑፍ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት የሥልጣነ ክህነት አይነቶችን ከተግባራቸው ጋር መግለጽ መቻሉ ሲሆን የሚለይበት ደግሞ ቅድመ እና ድህረ ሥልጣነ ክህነት እንዲሁም የሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔው ያልቀረበበት በመሆኑ ነው፡፡

አዕምሮ ወንድማገኘሁ እና ጆኪም (1970) “The Ethiopian Orthodox Church” በሚል ርዕስ አስር ዋና ዋና ጉዳዮችን የሚገልፁ ጽሑፎችን አቅርበዋል፡፡ ከእነዚህም ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል ሰባቱን ምስጢራት የሚገልፅ ፅሑፍ በመኖሩ እና ከሰባቱ ምስጢራት ውስጥ ደግሞ አንዱ ምስጢረ ክህነት በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር በከፊልም ቢሆን ተዛምዶ አለው፡፡

የአፅምሮ እና ጆኪም መጽሐፍ ዓላማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አስተዳደር፣ ታሪክና እምነት፣ አምልኮ፣ ልማድ እና ሃይማኖታዊ ህይወት ገልፆ ማሳየት ነው፡፡

ጸሃፊዎቹ በጽሑፋቸው ውስጥ የሥልጣነ ክህነትን ምንነት ገልፀዋል፡፡ ሥልጣነ ክህነት የሚባሉት የተለያዩ መሆናቸውን እና እነሱም ጳጳስ፣ ቄስ እና ዲያቆን እንደሚባሉ ጠቁመዋል እነዚህ የሥልጣን አይነቶችን ግለሰቦች ሲቀበሉ ሥርዓቱ በተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚታጀብና እንደሚከበር አስረድተዋል፡፡ እንዲሁም ግለሰቦች ስልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኋላ የሚኖራቸውን የሥራ ድርሻ (አገልግሎት) እና ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነት ገልጸዋል፡፡

በመጽሐፉ ከቀረቡት ጉዳዮች ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በተለይም ስለ ክህነት የሚገልፅ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ በክህነት አሰጣጥ ሥርዓት ላይ ግን የሚከወኑ የተለያዩ ክዋኔዎችን የሚያሳይ ባለመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚለይበት ነው፡፡

መልአኩ አስማማው “ሀብታችንና ሥርዓቱ” በሚል ርዕስ በ1993 ዓ.ም ስለ ቤተክርስቲያን፣ ስለ ህግ፣ ስለ ሥርዓት፣ ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ስለ ጸሎት፣ ስለ ቅዳሴ እና ስለ ሰባቱ ምስጢራተ ቤ/ክርስቲያን የሚገልጽ መጽሐፍ አሳትሟል፡፡

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩ ጉዳዮች ተመልክተን አጠቃላይ የመጽሐፉን ይዘት ስንመረምር በሦስት ሊከፈል ይችላል፡፡ እነሱም ህግ (ድንጋጌ ወይም ውሳኔ)፣ ሥርዓት (ማንኛውም

ሊከወን ለሚችል ነገር ቅደም ተከተል፣ መጀመሪያና መጨረሻ ልክና መጠን ወይም ገደብ ማዘጋጀት) እና ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡

ይህ መጽሐፍ ለዚህ ጥናት በተዛማጅ ጽሑፍነት የቀረበው ስለክህነት ምስጢር ፣ ስለሥርዓት ምንነት እና አይነቶች የሚገልጽ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች የተጠቀሱት ጉዳዮች በጥናቱ ውስጥ መጠቀስ ለሚገባቸው መረጃዎች ልዩ ልዩ ማብራሪያዎችን እና ሀሳቦችን የሚሰጥ በመሆኑ የመጽሐፉ በተዛማጅ ጽሑፍነት መቅረቡ አስፈላጊ ነው፡፡

መልአኩ ስለክህነት ምስጢር ሲያስረዳ አምስት ዋና ዋና ገጽታዎችን አንስቷል፡፡ እነዚህም የክህነት አጀማመር፣ ለክህነት የሚያበቁ መመዘኛዎች፣ የሹመት አሰጣጥ ሥርዓት፣ ከስልጣን የሚሻሩባቸው ነጥቦች እና የክህነት አገልግሎት ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ስለሚፈፀመው የክህነት አሰጣጥ በቅደም ተከተል ሲያሳይ በመጀመሪያ ፓትያርክ ቀጥሎም ጳጳስ፣ ቄስ እና ዲያቆን የሚል የስልጣን ተዋረድን ተከትሏል፡፡ በእነዚህ የክህነት አይነቶች ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ገጽታዎችንም አሳይቷል፡፡ ይህ በመሆኑም በዚህ ጥናት ትኩረት ከሚሰጥባቸው ነጥቦች ጋር ይዛመዳል፡፡

በመጽሐፉ ስርዓት ለሚለው ጽንሰ ሐሳብ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡እንዲሁም ስለ ሥርዓት አይነቶች፣ እና በአሁኑ ወቅት ያለውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ገጽታ አስረድቷል፡፡ በተለይ መንፈሳዊ ሥርዓትን በተመለከተ ስለ አመጣጡ፣ ስለክህነት ስልጣን አሰጣጥ የነበረውን ሁኔታ ያገኘውን መረጃ በመግለጽ ማስረዳቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ ከእኔ ጥናት የሚለየው ስለምስጢረ ክህነት ሲገልፅ የሹመት ሥርዓቱን በተመለከተ እኔ ከምመለከትበት አቅጣጫ እና ከማጠናበት ሥርዓተ ሂደት የተለየ መሆኑ ነው፡፡ ዲያቆን መልአኩ የሹመት ሥርዓቱን ሲገልፅ አውድ፣ ክዋኔ፣ ትዕምርት እና ትርጉም የሚባሉ የፎክሎር ማጥኛ፣ መተንተኛ ዘዴዎችን አልተጠቀመም፡፡ በክዋኔው ወቅት የሚፈፀሙ ሥርዓቶች ሃይማኖታዊ ገጽታዎች በጥቂቱ ተገለፀው እንጂ ፎክሎራዊ ገጽታቸው አልታየም፡፡

ሄኖክ ኃይሌ(1998) "ክብረ ክህነት" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥ ስለስልጣነ ክህነት በሰፊው ተገልል።

ይህ ክብረ ክህነት የተሰኘ መጽሐፍ የክህነትን አጠቃላይ ገጽታ የሚጠቁም ነው። በውስጡ ስለካህናት አጠቃላይ ነገር ለመግለጽ በሰባት ዋና ዋና ጉዳዮች ተደራጅቶ ቀርቧል። እነዚህ ጉዳዮች የመጽሐፉን ይዘት የሚጠቁሙ ሲሆን እነሱም ስልጣነ ክህነት በሐዲስ ኪዳን፣ የካህናት ሥልጣን፣ የካህናት ፈተና፣ በካህናት የሚጠበቁ ሥርዓቶች (ደንቦች) የካህናትና የምዕመናን ግንኙነት፣ ለካህናት የሚገባ አክብሮትና አገልግሎት እንዲሁም ካህናትን መገሰጽና መንቀፍ እንደማይገባ የሚገልፁ ናቸው።

በመጽሐፉ ውስጥ በተለይ ስለካህናትና ምዕመናን ግንኙነት ፣ ለካህናት የሚገባ አክብሮትና አገልግሎት በሚሉ ነጥቦች የተዳሰሰ በመሆኑ በመጽሐፉ እና በዚህ ጥናት መካከል ያለውን ተዛምዶ ያመለክታል።

በሌሎች ተዛማጅ ጽሑፎች ላይ እንደተገለፀው ሁሉ ይህ መጽሐፍ ከዚህ ጥናት የሚለይበት የሥርዓተ ክዋኔው ሂደት መገለፅ ባለመቻሉ እና በሥርዓተ ክዋኔው ወቅት የሚኖሩ ፎክሎራዊ ገጽታዎች ምን ምን እንደሆኑ የማያመለክት በመሆኑ ነው።

አክሊሉ ታደሰ (1999)"ክህነትና ካህን በቤቱ በዕሥራ ምዕት " በሚል ርእስ መጽሐፍ አሳትሟል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ ዋና ዋና ነጥቦች ሁለት ሲሆኑ እነሱም ክህነት እና ካህን ናቸው። ክህነትን በተመለከተ አጀማመሩን በህገ ልቡና፣ በህገ ኦሪት እና ወንጌል እንዲሁም ክህነት በኢትዮጵያ የነበረው ገጽታ የተገለፀ ሲሆን ስለካህን ደግሞ በህይወት ዘመኑ ሊኖረው የሚገባው የአኗኗር ዘይቤ የተጠቆመበት ነው።

ይህ መጽሐፍ ዋና ትኩረቱ ካህንን እና ካህናትን የተመለከተ በመሆኑ ከክህነት አጀማመር ጀምሮ ያለውን ሁኔታ በዝርዝር ያስረዳል። በተለይ የክህነት አጀማመር በሕገ ወንጌል ያለውን ገጽታ ሲያስረዳ ካህን ለመሆን ወይም ላለመሆን የሚያስችሉ መስፈርቶች፣ ስለካህን መብት፣ ስለክህነት ስልጣን አቀባበል ሥርዓት፣ እና ስለካህናት ተግባር ተገልፃል። ስለክህነት ስልጣን አቀባበል ስርአት ለመግለጽ ሲሞከር በፍትሃነገሥት ውስጥ የተጠቀሱትን ለክህነት የሚያበቁ እና የማያበቁ፣ እንዲሁም በሥርዓተ ሹመቱ ላይ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ተገልፀዋል። በእነዚህ ዋና ዋና ነጥቦች ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ሲኖረው ልዩነቱ

በሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔው ወቅት የክዋኔው አውድ አንድ በአንድ ማቅረብ አለቻሉ ነው፡፡ በመጽሐፉ የቀረበው አጠቃላይ ስርዓት እንጂ በክዋኔ ወቅት ሊታዩ የሚገባቸው አለባዎች /Elements/ አልቀረቡም፤ አልተገለፁም፡፡ እንዲሁም በክዋኔው ወቅት ያለው ሥርዓት ተምሳሌታዊ ትርጉም /interpretation/ አልቀረበም፡፡ ፀሐፊው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በአጠቃላይ ለማሳየት የፈለጉት ስለ ክህነትና ካህን ሃይማኖታዊ ገጽታ እንጂ ፎክሎራዊ ገጽታ አለመሆኑ ከዚህ ጥናት የሚለይበት ነጥብ ነው፡፡

**ሃብተማርያም ወርቅነህ** (1953) "ትምህርተ አበነፍስ" በሚል ርዕስ መጽሐፍ አሳትመዋል፡፡ ይህ መጽሐፍ በውስጡ ስለቤተክርስቲያን፣ አበ ነፍስ (የነፍስ አባት) አንድ ግለሰብ ወደ ክህነት ከመግባቱ በፊት የሚያልፍባቸው ሂደቶች፣ ካህናት ሊኖራቸው ስለሚገባ ፀባይ፣ ካህን ሥልጣነ ክህነትን ከተቀበለ በኋላ የሚፈፅማቸው ተግባሮችና የካህኑ የማንፃት ሥራ ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር የሚያስረዱ ዋና ዋና ጉዳዮችን ይዟል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ይዘት ስንመረምር ከዚህ ጥናት ጋር የተዛመዱ የተለያዩ ነጥቦችን አንስቷል፡፡ በተለይ ካህናት ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል ክህነታዊ ዝግጅት እንዴት እንደሚያደርጉ፣ ክህነት እንዴት እንደሚሰጥ የካህናት ተግባር እና ካህናት በማህበረሰቡ ውስጥ ምን አይነት ገጽታ ሊኖራቸው እንደሚገባ ሲያስረዳ ከዚህ ጥናት ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ልዩነታቸው ደግሞ ክህነት እንዴት እንደሚሰጥ ለመግለፅ ሲሞክር የአሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔው አልተገለፀም፡፡ የሹመት አሰጣጥ ህጉ ብቻ ተጠቆመ እንጂ ፎክሎራዊ ገጽታው አልታየበትም፡፡

ለዚህ ጥናት በተዛማጅ ጽሁፍነት የተመለከትኩት ሌላው መጽሃፍ ፍትሐ ነገሥት ነው፡፡ይህ መጽሃፍ የህግ እና የሥርዓት መጽሐፍ ነው፡፡ ከ1444 እስከ 1668 ዓ.ም በነበረው ጊዜ ውስጥ ከአረብኛ ወደ ግዕዝ እንደተተረጎመ እና በሥራ ላይ እንደዋለ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ተገልጿል፡፡

ፍትሐ ነገሥት ፍትህ መንፈሳዊ እና ፍትህ ሥጋዊ የተሰኙ ሁለት ክፍሎች አሉት ፡፡ ኢትዮጵያ ህገመንግስት በ1948 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ይህ መጽሐፍ የህግ መጽሐፍ ሆኖ ያገለግል እንደነበር ተጠቁሟል፡፡ በአሁን ሰዓትም መንፈሳዊ ህግና ሥርዓቱ እየተሰራበት እንደሆነ መጽሐፉን ያሳተው ድርጅት መግለጫ ሰጥቷል፡፡

ይህ መጽሐፍ በዚህች ምድር ስንኖር በመንፈሳዊ እና ሥጋዊ ህይወት እንዴት መመላለስ እንደምንችል ለማስረዳት ሃምሳ አንድ የሥጋዊና መንፈሳዊ ህይወት ገጽታዎች በማቅረብ ህግና ሥርዓቱን ጠቅልሎ ያሳያል፡፡ ስለሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ ንፍቀዲያቆናት፣ አናጉንስጢስ፣ አንባቢ፣ በረኛና መዘምር፣ ስለዲያቆናዊት፣ ስለካህናትና ተከታዮቻቸው ሁሉ ይናገራል፡፡

ስለእነዚህ የክህነት አይነቶች ህግና ሥርዓት ሲገልፅ ካህናት ስልጣነ ክህነትን ከመቀበላቸው በፊት፣ ሥልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኋላ ስለሚኖራቸው የህይወት አቅጣጫ፣ ከምን ከምን መጠበቅ እንዳለባቸው የሚያመለክት ሃይማኖታዊና (መንፈሳዊ) ማህበራዊ ገጽታዎች፣ ከማዕግ የሚያስሽራቸው ምክንያቶች ሁሉ አንድ በአንድ ዘርዝሮ ያሳያል፡፡ ሥርዓተ ሹመት በሚሰጥበት ጊዜ ለሲመቱ የሚያገለግሉ ህጎችም ቀርበውበታል፡፡ መጽሐፉ እነዚህን ሁሉ ጉዳዮች የሚያስረዳ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ዳሩ ግን ይህ ጥናት ከሚመለከትበት አቅጣጫ አንጻር ፎክሎራዊ ገጽታዎች ያለተገለጹበት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ጽሐፊዎች በተጨማሪ በርካታ የሃይማኖትና የቤተክርስቲያን ጸሐፊዎች ስለ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ጽፈዋል፡፡ ክህነት ከሰባቱ ሚስጥራት መካከል አንዱ በመሆኑም በጽሁፋቸው መጠነኛ ዳሰሳ አድርገዋል፡፡ ለዚህ ጥናት በተዛማጅ ጽሁፍነት ለማቅረብ ቅኝት ሲደረግ የሚከተሉት ጽሁፎች መጠነኛ ተዛምዶ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እነዚህም፡-

- አባ በትረ ሃይማኖት እና ዮሃንስ መኮንን (1998) " ሰባቱ ሚስጥራተ ቤተክርስቲያን" በሚል ርዕስ ስለ ሰባቱ ሚስጥራት ገልፀዋል፡፡ ስለ ምስጢረ ክህነት ምንነት እና ደረጃዎቹም አስረድተዋል፡፡

- "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙት" በሚል ርዕስ አስራ ስምንት የሚያህሉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በ1988 ዓ.ም አዘጋጅተው ያሳተሙት መጽሐፍ የሚስጢረ ክህነትን ምንነት አብራርቷል፡፡

* አበራ በቀለ (1996) "ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ህይወት" በሚል ርዕስ ስለምስጢረ ክህነትና ሌሎች ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ገልጿል፡፡

* የማህበረ ቅዱስን ትምህርት ክፍል በሰንበት ት/ቤቶች ለሚማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማስተማሪያነት ተዘጋጅቶ በ1993 ዓ.ም የታተመና "ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት" በሚል ርዕስ የቀረበ መጽሐፍ ስለምስጢረ ክህነት፣ስለክህነት አሰጣጥ ክህነትን ለመቀበል የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እና የካህናት ተልዕኮ ምን ምን እንደሆኑ ያስረዳል፡፡

* አባ ኤጲፋንዮስ (1998) "ፍኖተ ሃይማኖት" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ ስለምስጢረ ክህነት ፣የሥልጣነ ክህነት አመሠራረት ፣ በአዲስ ኪዳን ስለክህነት ማዕረጋትና የክህነት አሰጣጥ ሥርዓት ገልፀዋል፡፡

* አባ ገብርኤል (1990) "ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክስ" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ ስለክህነት ምንነት የስልጣን ደረጃዎች ፣ተግባራቸውና በአዲስ ኪዳን ዘመን የክህነትን ገጽታ አብራርተዋል፡፡

* ብርሃኑ ጎበና (1990) "መራሄ ድህነት" በሚል ርዕስ ስለክህነት አሰጣጥ ሥርዓትና ሃጢያትን ለካህን መናገር ማዕድን (ምግብን) በካህን እጅ ማስባረክ ስለሚገባና ሃዋርያት ሥልጣነ ክህነትን የሚያስሸሩ ምክንያቶች ምንምን እነደሆኑ ገልጿል፡፡

የተጠቀሱት ስራዎች ያነሱት ርእሰ ጉዳዮች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ሲሆን የሚለዩት ምስጢረ ክህነትን በተመለከተ ሃይማኖታዊ ገጽታውን አሳዩ እንጂ ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርግባቸውን ፎክሎራዊ ገጽታች ያልዳሰሱ በመሆናቸው ነው ፡፡

# ምእራፍ ሶስት

## 3.የጽሑፎች ዳራ

### 3.1.በኢትዮጵያ የክርስትና እና የክህነት አጀማመር ታሪካዊ ዳራ

#### 3.1.1 የክርስትና ሐይማኖት አጀማመር

አሁን ላለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ለስልጣነ ክህነት መሰረት ክርስትና ነው፡፡ ስልጣነ ክህነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት የሚሰጥበት ምክንያት ሥርአተ ቤተክርስቲያንን እና ስርአተ አምልኮን ለማስፈጸም ከመሆኑ ባሻገር የክርስትናን እምነት ጠብቆ ለማቆየት እና ለማስፋፋትም ጭምር ነው፡፡ ይህንን ሃይማኖት ጠብቆ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚፈልጉበት ዋና ምክንያት ጥንት የነበረ፣ ሃዋርያት የመሰረቱት፣ የጥንት አባቶች እውቀት፣እምነት፣አስተሳሰብ፣ነገረ ተፈጥሮንና ነገረ አማልእክትን የተገነዘቡበት ከዚያም ተነስተው የሚኖሩበትን አለም የተረጎሙበት ፣የሰዎች የአኗኗር ዘይቤ እንዴት መሆን እንዳለበት ያመለከቱበት ወይም የአኗኗር መርሃቸውን የደነገጉበት ቀጥተኛ፣ ትክክለኛና የጽድቅ መንገድ የሆነ፣ለወደፊቱም መቀጠል ያለበት ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ክርስትና በኢትዮጵያ እንዴት እንደተጀመረና ጥንታዊነቱን ለማሳየት የተለያዩ የሃይማኖትና የታሪክ ጸሐፊዎች ሁለት ገጽታዎችን በዋናነት ይጠቁማሉ፡፡ የመጀመሪያው በ34ኛው ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግስት በነበረችው ጃንደረባ አማካኝነት ገብቶ መስፋፋቱን የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ) የኢትዮጵያ ጳጳስ በመሆኑ ምክንያትና መጽሐፍ ቅዱስን በሰፊው በማስተማር ሃይማኖቱ እንዲሰራጭ በማድረጉ ነው የሚል ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ገጽታዎች የሚነገርባቸው ዘመን የጥንታዊ ኢትዮጵያ ክርስትና (Ancient christianity) በሚል የሚጠራ ነው፡፡ ሉሌ (1986፤123፣ መንግስቱና አሳምነው 2000፣9)

የክርስትና ሃይማኖት በ34ኛው ዓ.ም በኢትዮጵያ ለመስፋፋቱ ምክንያት የንግስት ህንደኬ ጃንደረባ የኦሪትን ስርዓተ አምልኮ ለመፈጸም ኢየሩሳሌም ደርሶ ሲመለስ ፊልጶስን ጋዛ (ሰለሞን ለንግስተ ሳባ በርስትነት የሰጣት ምድር) በምትባል አገር በማግኘቱ ነው፡፡ የንግስት ህንደኬ ጃንደረባ እንደ ኦሪት ህግ የእምነቱን ሥርዓት ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም የሄደበት ምክንያት (ዘዳ 16፡16 )ላይ “ወንዶች ሁሉ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት እርሱ

በመረጠው ስፍራ ይታዩ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ባዶ እጃቸውን አይታዩ። አምላክህ እግዚአብሔር በረከት እንደሰጠህ መጠን እያንዳንዱ ሰው እንደችሎታው ይስጥ" ተብሎ የተጻፈውን ህግ ለማክበር እንደነበር ክንፈ ገብርኤል (2000፣16)ይገልጻሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ (ሐዋ 8÷25-40) እንደተገለፀው ጀንደረባው በሰረገላው ላይ ተቀምጦ የኢሳያስን መጽሐፍ (ኢሳ÷53) ያነብ ነበርና ፊልጶስ በእግዚአብሔር መልአክ አዛዥነት ወደዚህ ሰው በመቅረብ ሊያነጋግረው ችሏል። የኢሳያስ መጽሐፍ የሚያስረዳው ስለክርስቶስ ነበርና ፊልጶስ ለጃንደረባው መጽሐፉ በክርስቶስ ማመን እንደሚገባ ማስረዳቱን ገልያስታል። ጃንደረባው የክርስትናን እምነት የተቀበለበትም ዋናው ምክንያት በጉዞው ላይ ፊልጶስ ስለ ኢሳያስ መጽሐፍ ካስረዳው በኋላ ስለትንሳኤ እና ጥምቀት እንዲገነዘብ እና በእነዚህ የክርስትና እምነት መሠረቶች እንዲያምን በማድረጉ ነው።ጃንደረባው ይህንን የተቀበለውን የክርስትና እምነትም በኢትዮጵያ ላሉ ህዝቦች አሰራጭቷል።

አቡነ ሳሙኤል (2000፣14) ጃንደረባው የኢሳያስን መጽሐፍ ማንበቡ አረማዊ ሳይሆን የኦሪት እምነት ተከታይነቱን እንደሚያሳይ ጠቁመዋል። እንዲሁም በዚህ ዘመን በበዓለ ሃምሳ ጊዜ ሃዋርያት የተለያዩ ቋንቋዎችን የመናገር ጸጋ ተሰጥቷቸው ስለነበር ፊልጶስ የግዕዝን ቋንቋ መናገር ይችል እንደነበር ተገልጻል። ከዚህ በመነሳትም ፍሊጶስና ጃንደረባው የተግባቡበት ቋንቋ ግዕዝ መሆኑን አስረድተዋል።

ሉሌ መልአኩ የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ የነበረው ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት መሆኑን ሲያስረዱ የሚከተለውን ብለዋል።

> *ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላ ክርስትና የተቀበለ በ4ኛው መቶ ዘመን ቢሆንም ቀደም ሲል በ[ከ35] ዓ.ም የክርስትናን እምነት ኢትዮጵያ ተቀብላ ነበር። ይኸውም [በ35] ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግሥት የህንደኬ በጅሮንድ (ጃንደረባ) ኢየሩሳሌም ደርሶ በኦሪት ልማድ በዓለ ፋሲካን አክብሮ ወደ ጋዛ በምትወስደው መንገድ በኩል አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ፊልጶስ አግኝቶ ስለ ጌታ ወደዚህ አለም መምጣት፣ ስለሞቱ፣ ስለትንሳኤውና ስለሥርዓተ ጥምቀት አስረድቶና በክርስቶስ አሳምኖ አጠመቀው። ጀንደረባውም ከፊልጶስ የተማረውን የክርስትና ትምህርት ዜና ለኢትዮጵያ ህዝብ አሰማ ስለዚህ [ከ35] ዓ.ም እስከ 330 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኦሪት እምነቱ ጋር ጥምቀትን ተቀብለሎ ቆየ። (1986፣123)*

ኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ወደ ሀገሩ ተመልሶ የክርስትና ሃይማኖትን በቅድሚያ ለንግስቲቱ አስተዋውቆ እምነቱን እንድትቀበል ማድረጉ ሌሎች ዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍሎች የንግስቲቱን ትዕዛዝ ለመፈፀም ሲሉ እምነቱን በፍጥነት እንደተቀበሉት መንግስቱና አሳምነው (2000፤53)፤ ስርግው (1970:5) ገልፀዋል፡፡

የታሪክ እና የሃይማኖት ጸሐፊዎች ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በተጨማሪ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ክርስትናን ለኢትዮጵያ እንዳስተዋወቁ ይገልፃሉ፡፡ ስርግው (1970:3)፤ መንግስቱና አሳምነው (2000፤52) ኢትዮጵያውያን የበዓለ ሃምሳን ከአይሁድ ጋር ማክበር አንዱ ልማዳቸው መሆኑን አስረድተው በዓሉን አክብረው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ እምነቱን ለኢትዮጵያውያን ማስተዋወቅ ችለዋል ሲሉ ኤፍሬም (1971:241) ደግሞ ኢትዮጵያውያን ለስርአተ አምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ሳለ በበአለ ሃምሳ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የተለያዩ ቋንቋዎችን መስማት ችለው እንደነበርና በወቅቱ ጴጥሮስ ሲሰብክ የአርማይክን ቋንቋ ሰምተው ሃሳቡን ተረድተው እንደነበር ከዚያም ለኢትዮጵያውያን እምነቱን ማስራጨታቸውን አስረድቷል፡፡

እንዲሁም ክንፈገብርኤል (2000፤15)፤ ኤፍሬም (1971:241)፤ አባ ጎርጎርዮስ (1991:18) እና መንግስቱና አሳምነው (2000፤52-53) ሩፊኖስና ሶቅራጥስ የተባሉ የታሪክ ጸሐፊዎችን በመጥቀስ ከቅዱሳን ሐዋርያት መካከል ቅዱስ ማቴዎስ፣ ቅዱስ ናትናኤል፣ ቅዱስ በርተሎሜዎስና ቅዱስ ቶማስ በኖብያና በኢትዮጵያ ባሉ አውራጃዎች በመዘዋወር ወንጌል መስበካቸውን ገልጸዋል፡፡

ክንፈገብርኤል በጽሑፋቸው ስለ ቅዱስ ማቴዎስ ሲገልጹ በህንድ በኩል አድርጎ ኢትዮጵያ ገብቶ እንዳስተማረ እና በዚያው በሰማዕትነት እንዳረፈ፣ በዚህ ምክንያትም ኢትዮጵያ መንበረ ማቴዎስ በመባል እንደምትጠራ ሲገለጹ አባ ጀሮም የተባሉ ፀሐፊ ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ በኢትዮጵያ የክርስትናን እምነት እንዳስተማረ መንግስቱ እና አሳምነው በጽሑፋቸው ጠቁመዋል፡፡ እንዲሁም ታደሰ (1972:23) ጉዊዲን (1922:124) ጠቅሶ በአክሱም ያሉ ኢትዮጵያውያን በንግድ ልውውጥ አማካይነት የክርስትና እንምነት ከተቀበሉ የውጪ ዜጎች ዘንድ ሊያውቁ (ሊማሩ) መቻላቸውን አስረድቷል፡፡

የተለያዩ የሃይማኖት እና የታሪክ ፀሐፊዎች ክርስትና በትክክል የተጀመረው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው በማለት የሚገልፁት ታሪኩን ከፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ) ታሪክ ጋር

በማያያዝ ነው።ማርቆስ (Marcus(1994:7) ፣ ስርግው (1970፣3)፣ ኤፍሬም (1971፣241)፣ ባህሩ (1989፣3)፣ ቻሎት( 2002፣17)፣ ጌታቸው(1981:25-35)፤ ሉሌ (1986፣123)፣ታደሰ (1972:51)፣ አዕምሮ (1970:4)፣ አቡነ ሳሙኤል (2000:12)፣ ክንፈገብርኤል( 2000:16) አባ ገርጎርዮስ (1991:21) እንደገለፁት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያን ይገዙ በነበሩ ኢዛና እና ሳይዛና የአክሱም ነገስታት ዘመን ፍሬምናጦስ የተባለ ግሪካዊ ከህፃንነቱ ጀምሮ ወንጌልን እየተማረ ያድግ ነበር። ይህ ሰው ከአጎቱ ጋር ህንድን ሊጎበኝ በመርከብ ሲሄድ አጋጣሚ መርከቧ ብትሰምጥም እሱና ወንድሙ ጉዳት አልደረሰባቸውም ነበር።

ፍሬምናጦስ ወደ ሃገሩ ሳይመለስ በምፅዋ አካባቢ ቆይቶ ከአክሱም ነገስታት ጋር ሊገናኝ ችሏል። ይህ ሰው ከልጅነቱ ጀምሮ ክርስትናን ያወቀ በመሆኑ በኢትዮጵያም እምነቱ እንዲስፋፋ ጥረት አድርጎ ነበር። ይኸውም የአክሱም ነገስታት የነበሩትን ኢዛናን እና ሳይዛናን በማስፈቀድ ወንጌልን የሚያስተምር፣ የሚያጠምቅ እና የሚያቆርብ ጳጳስ ለማስመጣት ወደ እስክንድሪያ በመሄድ ጉዳዩን ለቅዱስ አትናቴዎስ ማስረዳቱ ነው። ቅዱስ አትናቴዎስ ግን ፍሬምናጦስ የኢትዮጵያን ባህል ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆኑን ስለተረዳ ራሱን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ አድርጎ ሾመው። ‹‹አባ ሰላማ ››የሚል የማዕረግ ጵጵስና ስምም ሰጥቶት ወደ ኢትዮጵያ መልሶ ላከው።በኢትዮጵያም ወንጌልን በሚገባ ይሰብክ ስለነበር ‹‹ከሳቴ ብርሃን›› በመባል እንደተጠራ ተገልጿል።

ቻሎት (2002፣17) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጥንታዊ እንደሆነች እና የተመሰረተችውም በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአሌክሳንድሪያ ቅዱስ አትናቴዎስ የመጀመሪያውን ጳጳስ ከሾሙ በኋላ መሆኑን ገልፃለች። ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ስለነበረው የክርስትና እምነት ታሪካዊ ዕድገት ለመግለጽ አስቸጋሪ መሆኑን በመጠቆም ለኢትዮጵያውያን ግን በሐዋ (8÷26-40) ላይ የተጠቀሰውን (የኢትዮጵያው ጃንደረባ በፊሊጶስ መጠመቅ) መግለጽ አስፈላጊ መሆኑን የሚከተለውን ጽሑፍ በማስፈር ታስረዳለች።

> *The Ethopian orthodox Tewahedo church is one of the most ancient churches, found in the 4th century, after the consecration of its first Bishop by saint Athnnaasius of Alexandria. It is difficult to find sources about any earlier historical stage of Christianity in Ethiopia. For Ethiopians, in any case it is important to mention the Baptism*

*of the Ethiopian eunch by philipon his way back of his pilgrimage to Jerusalem (Acts 8:26-40). (Chailot 2002፣ 17)*

ባህሩ (1998፣34) በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ሊስፋፋ የቻለው በአክሱም ንጉስ በኢዛና መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ንጉስ ኢዛና ይህንን ሃይማኖት ሊቀበል የቻለበት ምክንያትም በፍሬምናጦስ አማካይነት መሆኑን የተለያዩ መዛግብት እና የአርኪዎሎጂ መረጃዎች መጠቀማቸውን ያስረዳል፡፡ ባህሩ በጽሑፉ እንዳመለከተው በዘመኑ ንጉስ ኢዛና ብቻ ሳይሆን ሌሎች ንጉሳዊ ቤተሰቦች ሁሉ የክርስትና ሃይማኖት የተቀበሉ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ የፃፉ (ሰሙ እና ቸሬ፡2000፡54-63፣ መንግስቱ እና አሳምነው፣ 2000 ሰለሞን 2001፣ ኤፍሬም 1971፡241-245፣ ስርግው 1970፡1-43፣ አፅምሮ 1970፡22-30 ታደሰ 1972፡145 እና ሉሌ 1997፣21-40) በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ እምነት ተስፋፍቶ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንዲገኝ ያስቻሉ በርካታ ምክንያቶችን ሲጠቁሙ ከላይ የተጠቀሱትን የኢትዮጵያዊውን ጃንደረባና ቅዱስ ፍሬምናጦስ ያደረጉትን አስተዋጽኦ በቅድሚያ ያነሳሉ ፡፡ ከእነዚህም መካከል ለምሳሌ ቁንስጣ የተባለ የሮም ንጉሥ አባ ሰላማ ወደ እስክንድርያ ሄዶ የአርዮስን ትምህርት እንዲቀበል ነገስታቱ ኢዛናና ሳይዛና (አብርሃና አጽብሃ) ተጠይቀው ነበር፡፡ ወደኢትዮጵያ ተመልሶ ይህንን አርዮሳዊ ትምህርት እንዲያስተምር ነገስታቱ ሲለመኑ ፍሬምናጦስ የክርስትናን ምንነት በማስገንዘቡ ምክንያት ሀሳቡን አለመቀበላቸውና በኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸው ጸንተው መቀጠላቸው ሃይማኖቱ ህልውናውን ጠብቆ እንዲቆይ ካሰቻሉት መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ዘጠኙ ቅዱሳን በ 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ451 ዓ.ም የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ አንቀበልም በማለት ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ የሁለት ባህርይ ትምህርትን ማስተማር ነው፡፡ ዘጠኙ ቅዱሳን በዚሁ አዲስ ትምህርት ምክንያት ከሚኖሩበት ሀገር ተሰደዋል፡፡ ኢትዮጵያ እነዚህን ቅዱሳን በመቀበሏ ክርስትና ፣ የገዳማዊ ኑሮ እንዲሁም የምንኩስና ስርዓትን እንዲስፋፋ አስችሏታል፡፡ እነዚህ ቅዱሳን በርካታ ቅዱሳት መፃህፍትንም ወደግዕዝ ተርጉመዋል፡፡

አፄ ካሌብ፣ ቅዱስ ያሬድ እና አፄ ገብረመስቀል በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ስር እንዲሰድ ለዘመናት መሠረቱን ሳይለቅ እንዲቆይ ብዙ ደክመዋል፡፡ አፄ ካሌብ በርካታ

አብያተክርስቲያናትን ማሳነፁና ከአይሁዳውያን ጋር ተዋግቶ በየመን አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖችን ማዳኑ፣ አፄ ገብረመስቀል (የአፄ ካሌብ ልጅ) በአባቱ እግር ተተክቶ ገዳማትንና ቤተክርስቲያናትን ማሳነፁ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከሌሎች ሀገሮች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራት ማድረጉና ሌሎችንም ሥርዓቶች መመስረቱ መልካም ገጽታን አቆይቷል። እንዲሁም ቅዱስ ያሬድ ግዕዝ፣ ዕዝልና አራራይ የተባሉ የዜማ ስልቶችን መፍጠሩ፣ አምስት የዜማ መጽሐፍትን፣ እንዲሁም አንቀጸ ብርሃን የተሰኘ የፀሎት መጽሐፍ በመድረሱ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ከዚህም በተጨማሪ "የጨለማው ዘመን" ተብሎ የሚጠራውና ለክርስትና ሃይማኖት መጨናገፍ ምክንያት የነበሩት ጊዜያት ካለፉ በኋላ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በመካከለኛውና በዘመናዊ የታሪክ ዘመን የተለያዩ ክስተቶች ተፈጥረዋል። ከእነዚህም ውስጥ የግዕዝ ሥነጽሑፍ መዳበር፣ የስብከት ወንጌልና የትምህርተ ሃይማኖተ መጠናከር፣ የገዳማዊ ህይወት መስፋፋትና ሌሎችም የነበሩ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ቤተክርስቲያን በሌላ የእምነት አራማጆች ተጽዕኖ ስር ወድቃ ነበር። ቢሆንም ግን ከዚህ ቀደም እምነቱ እንዲጠነክር ያስቻሉ የተለያዩ ጉዳዮች ዘመን ተሻግሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ እንዲደርስ አስችለዋል።

ዘመናዊው የታሪክ ዘመን ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ያለው ሲሆን በዚህ ክፍለ ዘመን በንጉሳውያኑ የመንግሥት አገዛዝ ጊዜ የኦርቶዶክስ እምነት የቤተመንግስት ሃይማኖት በመሆኑ በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ነበረው። ሆኖም ግን በዚህ ዘመንም የሚሲዮናውያን መነሳት፣ የውጭ ወራሪ (የቅኝ አገዛዝ) ተከስቶ የነበረ በመሆኑ የቤተክርስቲያን እድገት ላይ እንቅፋት ፈጥሮ እንደነበር ተጠቁሟል።

በዚህ መልኩ የክርስትና ሃይማኖት ከመስፋፋቱ በፊት በብሉይ ኪዳን ዘመን አምልኮ ይፈጸምባቸው የነበሩ ትውፊቶች ዛሬም ድረስ ተጠብቀው ለትውልድ እየተላለፉ ያሉ በርካታ ናቸው። እነዚህም የፎክሎርን ገጽታዎች አጉልቶ የሚያመለክቱ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ የህንፃ ቤተክርስቲያን አሰራር፣ የቅዳሜ አከባበር፣ የታቦትና የበዓላት አከባበር፣ የተከለከሉ ምግቦችን አለመመገብ፣ ግዝረት፣ ልብሰ ተክህኖ፣ የመዝሙር መሳሪያዎች እና ሌሎችም ናቸው። እነዚህ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ከሃይማኖታዊ ገጽታቸው ባሻገር ፎክሎራዊ ገጽታዎቹ ሲመረመሩ የአንድን ማህበረሰብ እምነት አመሰራረት እንዲሁም የአምልኮ ስርዓት የሚያሳዩ፣ የተለያዩ ማህበረሰቦች መገለጫ የሆኑ እሴቶችን የሚያመለክቱ ናቸው።

የፎክሎር ዘርፍ የሆኑት ስነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ሀገረሰባዊ ልማድ የአንድን ማህበረሰብ ማንነት፣ እውቀት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ እምነትና አንድ ማህበረሰብ ተጠብቆ የሚኖርበትን የህልውና መሠረት የሆኑ ጉዳዮች የሚመለከቱ ናቸው (ዶርሰን 1972፡25)፡፡ በዚህ መሠረት ስርዓተ አምልኮውን ለመፈፀም እና ለማስፈፀም በቃል የሚባሉ ንግግሮች (sayings) ከትውልድ ወደ ትውልድ ቃላዊነታቸውን ይዘው የሚሻገሩ ናቸው፡፡ በቃል ከሚተላለፉት ውስጥ ትረካዎች የተለያዩ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች የሚነገርባቸው እና ሰዎች ስለተፈጥሮ እና ስለአማልክት የተለያዩ ግንዛቤዎችን የሚያገኙባቸው ናቸው፡፡ እንደዚሁም ስርዓተ አምልኮውን ለመፈፀም የሚያገለግሉ የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት የቁሳዊ ባህል መገለጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሶች ከምን አይነት ጥሬ እቃ እንደተሰሩ፣ በምን አይነት ቅርጽ እንደተዘጋጁ ሲመረመሩ ሃይማኖታዊና በህላዊ እሴቶችን አንፀው የያዙ ናቸው፡፡ በስርዓተ አምልኮው ጊዜ የሚከናወኑ የተለያዩ ድርጊቶች (የካህናት እና የምዕመናን እንቅስቃሴ፣ በመዝሙር ጊዜ የሚኖረው ሽብሸባ፣ እርገዳ… ሊሆን ይችላል) ሀገረሰባዊና ሐይማኖታዊ ትውን ጥበባትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ እንዲሁም በስርዓተ አምልኮ ጊዜ የሚኖሩ ልማዶች ለምሳሌ እጣን ማጤስ፣ ቤተክርስቲያን መሳለም፣ ማተብ ማሰር፣ እምነት መቀባት፣ ፀበል መጠጣት የተከለከሉ ምግቦችን አለመብላት፣ የበዓላት አከባበር እና ሌሎችም ሀገረሰባዊ ልማድ የሚገለፁባቸው ገጽታዎች ናቸው፡፡

## 3.1.2 የክህነት አጀማመር

### 3.1.2.1 በብሉይ ኪዳን ዘመን

በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበረው ክህነት በሁለት ተከፍሎ ይታያል። ይኸውም በህገ ልቡና እና በህገ ኦሪት ጊዜ የነበረውን ገጽታ የሚያመለክት ነው። አክሊሉ (1999፡2) "ህገ ልቡና የሚባለው ዘመን ከአዳም ጀምሮ በጽሑፍ የተቀመጠን ህግ ከእግዚአብሔር እጅ እስከተቀበለው እስከ ነብዩ ሙሴ ያለው ጊዜ ነው" በማለት የገለፀ ሲሆን ስለምንነቱ ዘርዝሮ ሲያብራራም የሰው ልጅ በተፃፈ ህግ ሳይሆን እግዚአብሔር በተፈጥሮ በሰጠው ጥበቡ ወይም በልቡ ውስጥ በተቀመጠ ህግ የሚመራበት ጊዜ የነበረ መሆኑን ጠቁሟል። ይህ ማለት እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው ሀብተ ክህነትን፣ ሀብተ ትንቢትንና ሀብተ መንግስትን አብሮ ሰጥቶታል። ይህ በመሆኑም ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያሉት ትውልዶች ሲወርድ ሲዋረድ የሚተላለፈውን የአባቶቻቸውን በረከት በመጠቀም እንደ ፀጋ ስጦታቸው መስዋዕትን ይሰውና ትንቢት ይናገሩ ነበር፣ ያስተምሩና በሀብተ መንግስታቸው ቤተሰቦቻቸውን ይመሩና ያስተዳድሩ ነበር።

መልአኩ በህገ ልቡና ጊዜ የነበረውን ክህነት በተመለከተ በ(ዘፍ. 4፡3፣ ኩፋሌ 5፡1. ዘፍ 8፣20፣ 12፣7 13፣18) ያሉትን ጥቅሶች በመጠቀም የሚከተለውን ሀሳብ አስፍሯል።

> *በህገ ኦሪትና በህገ ወንጌል ልዩ ሥርዓት እስኪሰጥ ድረስ ከአዳም እስከ ሙሴ የነበሩ አባቶች በረከት (ምርቃት) ከእግዚአብሔር እየተሾሙ ማለትም ለአዳም አባታቸው የተሰጠው ፀጋ እየተላለፈላቸው እንደ ሀብተ ክህነታቸው፣ መሥዋዕትን ሲሰው፣ እንደ ሀብተ ትንቢታቸው ቤተሰቦቻቸውን ሲመሩና ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል። ስለዚህ በብሉይ ታሪኩን እንደምናነበው ሰው ሁሉ በተሰጠው ተፈጥሮአዊ ክህነት ስለራሱ የራሱን መስዋዕት፣ የቤተሰብ ኃላፊው ስለቤተሰቡ መስዋዕት ያቀርብ ነበር። (1993፡118)*

ክህነቱ ለዘለአለም የማይሻር የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የሆነ መልከ ጼዴቅ በህገ ልቡና ጊዜ ካህን በመሆንና የክህነትን ሥርዓት በመፈጸም ረገድ ትልቅ ስፍራ የተሰጠው መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ፣በመጽሐፈ ቀለሚንጦስና (2000፡68) በሌሎች መጽሐፎች ላይ ተገልጿል።

የሃይማኖት አባቶች ፀሐፊዎች (አባ ገብርኤል 1993፡159) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (ዕብ.7፣2-4፣ መዝ. 109፣4፣ ዘፍ 14፣18-23 ዘሌ. 21፣10-12 ዘፀ 28፣1፣ ሉቃ. 24፣50)

ያሉ ጥቅሶችን በመመርመር መልከጼዴቅ እውነተኛ የሰላም፣ የጽድቅ ንጉሥ፣ የዘላለም ካህን የትውልድ ዘሩ ያልተቆጠረ (ያልተነገረ) በመሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጸበት ተምሳሌት አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ለዚህም ትርጓሜ ሲሰጡ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለና የነበረ ከዚህ ተነስቶ እዚህ ደረሰ የማይባል ወደፊትም የሚኖር መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡ ኃየሎም ግን (2002፡110-120፣ 143) ስንክሳር ዘጳጉሜ 3 ቀን፣ ቀለሚንጦስና ገድለ አዳምን በመጥቀስ መልከ ጼዴቅ የካምና የሴም ዘር እንዳለው መጠቆማቸውን ገልጿል፡፡ ማርቆስ ዮናናዊ የተባሉ የግብጽ መነኩሴ ደግሞ "መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ልጅ ነው" ብለው ለተነሱት መናፍቃን በመጽሐፈ ፊልክስዩስ መልስ ሲሰጡ የዘር ሀረጉን ተንትነው ማሳየታቸውን አስረድተዋል፡፡ ይህም የኢየሩሳሌምን ከተማ የመሠረተ ከካም ወገን ከሆኑት የነብያ ንጉስ የነበረው ሴዱ ሳሌምን ወለደ፤ ሳሌም ሚልኪንና መልከ ጼዴቅን ወለደ በማለት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በህገ ልቡና ጊዜ ክህነት መደበኛ ሥርዓትን ይዞ ለተመረጡ ሰዎች መሾም የተጀመረው መልከ ጼዴቅ አብርሃምን ከባረከበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ብርሃኑ (ዘፍ 14፣ 12-24) ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመመርኮዝ እንዲህ በማለት ያስረዳል፡፡

> *ሙሴ ለአሮንና ለአልአዛር፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነት ከመስጠታቸው በፊት ክህነትን በመምህራን ቡራኬ ከመንፈስ ቅዱስ ለማግኘትም ለመሾም መሠረቱና መጀመሪያው መልከጼዴቅ አብርሃምን የባረከበት÷አብርም ከመልከጼዴቅ የተባረከበት ያ ብሩህ ሰዓት ነው፡፡ (1990፣ 90-92)*

በህገ ኦሪት ጊዜ የነበረው ክህነት በህገ ልቡና እንደነበረው ሰዎች ከአባቶቻቸው የሚሰጣቸው ፀጋ እየተላለፈላቸው እስከ ትውልድ ድረስ የሚያገለግላቸው ሳይሆን እግዚአብሔር ሌላ ሥርዓትን እንዳዘጋጀ ተገልጿል፡፡ ይህም ሥርዓት ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ በዘር እየተላለፈ እንዲሰጥና ክህነቱም የሌዊ ወገን ለሆነው ለአሮን እንዲሆን እግዚአብሔር ለሙሴ "አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ፡፡… የተቀደሰውንም ልብስ ለክብርና ለጌጥ እንዲሆን ለወንድምህ ለአሮን ስራለት፡፡" በማለት አዝዞ ነበር፡፡ (ዘፀ. 28፣1)፡፡ ሙሴም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት አሮንንና ልጆቹን ሾሟል፡፡ካህናቱ ይሰጡት የነበረው አገልግሎቶችም ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ፣ በመቅደስ ውስጥ በምስጋና ማገልገል፣ ህገ ኦሪትን ለህዝበ እስራኤል ማስተማር፣ ህዝቡን ከህመማቸው መፈወስ፣ መስዋዕትን ማቅረብ እና ሌሎች የተቀደሱ ስራዎች ናቸው፡፡

በክብረ ነገስት እንደተነገረው በብሉይ ኪዳን ዘመን በኢትዮጵያ ክህነት የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት ዘጠኝ መቶ ዓመት ገደማ በንግስተ ሳባ አማካኝነት ነው፡፡ ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን መፃህፍት ባለቤት እና የሥርዓተ ኦሪት ፈፃሚ ነበረች፡፡ ይህም የሆነው ንግስተ ሳባ የኢየሩሳሌምን ንጉስ የሰሎሞንን ዝና እና ጥበብ ታምሪን ከተባለው ኢትዮጵያዊው ነጋዴ ሰምታ ልትጎበኘው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ ስትመለስ ከእርሱ ምኒሊክን ፀንሳና የአምልኮ ሥርዓቶች ይዛ በመምጣቷ ነው፡፡

መንግስቱ እና አሳምነው( 2000፡38) ክህነት በኢትዮጵያ የተጀመረው ንግስተ ሳባ ንጉሥ ሰሎሞንን ጎብኝታ ከተመሰለች በኋላ መሆኑን ሲገልጹ "ከዚህ ታሪካዊ የንግሥተ ሳባ ጉብኝትም በኋላ ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን መፃህፍት ባለቤት፣ የታቦተ ጽዮን መንበር፣ የሥርዓተ ኦሪት ፈፃሚና አስፈፃሚ ሀገርና የኦሪት ካህናት ተገልጋይ ሀገር ለመሆን በቅታለች፡፡" በማለት ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን (የህገ ኦሪት) ክህነት የተጀመረውም ከሰሎሞን የፀነሰችው ልጅ ምኒሊክ ተወልዶ 22 ዓመት ከሞላው በኋላ አባቱን ሊጠይቅ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ለሶስት ዓመታት ሥርዓተ ኦሪትን በሚገባ ተምሮ፣ በካህኑ ሳዶቅ ንግስናን ተቀብሎ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ነው፡፡ ወደ ሀገሩ ሲመለስም ካህናትና አስራ ሁለት ሺህ የእስራኤላውያን በኩር ወንድ ልጆች ታቦተ ጽዮንን ይዘው አብረው መጥተዋል፡፡

እነዚህ ካህናት ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ህገ ኦሪትን ይፈፅሙና ያስፈፅሙ ነበር፡፡

አንዳንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ፀሐፊዎች እና ተከታዮች ይህን በክብረ ነገስት ላይ ተጽፎ የሚገኘውን የንግሥት ሳባ ታሪክ በኢትዮጵያ የተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ የክብረ ነግሥት መጽሐፍ አዘጋጅ ስርግው ገላው (1994) እንደገለጹት የታሪኩን ተአማኒነት ለማስረዳት የሚያቀርቡት ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (2ሳሙ. 7፡12 -17) ፤ (መዝ 89፡ 40 እና 132፡11) ያሉትን ትረካዎች እና የታቦተ ጽዮን በኢትዮጵያ መገኘት ነው፡፡

በአንጻሩ ደግሞ በታሪክ አዋቂዎች እና ፀሐፊዎች ዘንድ ይህ ታሪክ ባህላዊ እና አፈታሪክ መሆኑ ይነገራል፡፡ በእነዚህ ተከራካሪዎች ዘንድ የሚቀርቡት ማስረጃዎች በሰለሞን ዘመን የተጻፈ አለመሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ተከራካሪዎቹ ሃሳባቸውን ሲገልጹ የክብረ ነገሥት ፀሃፊዎች በብሉይ ዘመን ላይ ሆነው የሐዲስ ኪዳኑን ታሪክ በምንጭነት መጠቀማቸው የዚያ

ዘመን ሰዎች አለመሆናቸውን የሚያሳይ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ዲማትዮስ ዘሮም ወይም ዘአንፆኪያ እንዲሁም 318 አባቶች የመጽሐፉ ገፀ ባሕሪያት ሆነው መጠቀሳቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የኖሩት በሐዲስ ኪዳን ዘመን ነው፡፡ ነገር ግን ታሪኩ በተፃፈበት ዘመን (በሰሎሞ ዘመን) እንደኖሩ ታስቦ መፃፉ ታሪኩን ተአማኒነት እንዳይኖረው አድርጓል፡፡ የክብረ ነገሥት ታሪክ ገጸባህሪያት ሆነው የተጻፉ እነዚህ ሰዎች በዘመናቸው ታላላቅ አባቶች እና በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት የነበራቸው በመሆናቸው ታሪኩ ተአማኒት እንዲኖረው በሚል የተካተቱ ናቸው ሲሉ ስርግው (1994) እና Budge Wallis (2001) ይገልጻሉ፡፡

### 3.1.2.2 በሐዲስ ኪዳን ዘመን

በሐዲስ ኪዳን ክህነትን የመሠረተው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ (አባ ገብርኤል 1993፡161)፡፡ክርስቶስ ክህነትን መሥርቶ የመረጣቸውን ሐዋርያት ሾመ፡፡ በሐዲስ ኪዳን ያለውን የክህነት አጀማመር ለማስረዳት የተለያዩ የሃይማኖት ፀሐፊዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት የሰጠባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በቅድሚያ ይጠቅሳሉ፡፡እነሱም ሉቃ (6÷12፣24÷40)፣ ዮሐ (20÷ 22)፣ በማቴ (19÷28)፣(16÷18-19)፤ (18÷18-19)፣ (28÷20 )ሐዋ (13÷2)፣ (6÷6)፣ 1ኛ ጢሞ( 4÷4) ናቸው፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ለምሳሌ ሉቃስ 6÷12 ላይ ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተራራ ወጥቶ ሌሊቱን በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ሲፀልይ እንዳደረ እና አስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት መርጦ ሐዋርያት እንዳደረጋቸው የሚያስረዳ ነው፡፡ እንዲሁም (ዮሐ 20÷22) ላይ ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ እንዲቀበሉ አድርጎ የማሰርና የመፍታት ሥልጣን እንደሰጣቸው ይገልፃል፡፡ ሌሎችም ጥቅሶች በአስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ላይ መፍረድ እንደሚችሉ እና ምዕመናንን ከኃጢያት መጠበቅ እንዲችሉ ሥልጣን እንደተሰጣቸው የሚገልፁ ናቸው ሄኖክ (1999፣ 12)፣ ብርሃኑ (1990፣95)፣አክሊሉ (1999፡3)፡፡

መልአኩ (1993፡126) በሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ሲያስረዳ በዘመንና በቦታ የማይወሰን፣ የማይሾሙት፣ የማይሽሩት፣ አድራጊ ፣ፈጣሪ፣ ዘላለማዊ የቤተክርስቲያን መሪ፣ ሊቀ ካህናት፣ ኤጲስ ቆጶስ፣ እንዲሁም የእርሱ ክህነት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ በመገለፁ ነው ይላል፡፡

በሐዲስ ኪዳን ያለው የክህነት አሰጣጥ በብሉይ ኪዳን እንደነበረው በዘር ሀረግ የሚመረጥ አይደለም። እግዚአብሔር የመረጣቸው እና መንፈሱ ያደረባቸው፣ ለዚህ ዓላማ የታጩ ሰዎች ብቻ ስልጣነ ክህነት ይሰጣቸዋል። ይህንን በተመለከተ አክሊሉ የሚከተለውን አስፍሯል።

> *በህገ ወንጌል የክህነት ሥልጣን እንደ ህገ ልቡና በተፈጥሮ ሐረግ እንደ ህገ ኦሪት በነገድ ሐረግ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ልዩ ጥሪና በቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ነው። ኦሪትና ነቢያትን የፈፀመው ክርስቶስ እርሱ ራሱ ሊቀ ካህናት በመሆን ምስጢረ ክህነትን በአዲስ ሥርዓትና በአዲስ ኪዳን መስርቶታል።* (1999፣3)

በሐዲስ ኪዳን ያሉ ካህናት በብሉይ ኪዳን ካሉት ይልቅ ወደ እግዚአብሔር የቀረቡ እና የከበሩ ናቸው። ምክንያቱም የማሠርና የመፍታት፣ የእግዚአብሔር ልጅነት የማሰጠት እና ልዩ ልዩ ተአምራትን የማድረግ ሥልጣን አላቸው። ከዚህም አልፎ የክርስቶስን ስጋና ደም መስዋዕት የሚያቀርቡ በመሆናቸው ኃይልና ሥልጣናቸው ከፍ ያለ ነው።

የሐዲስ ኪዳን ስልጣነ ክህነት አሠጣጥ እንደ ብሉይ ኪዳን በቡራኬ፣ በምርቃት በአንድ ነገድ ብቻ ተወስኖ የሚተላለፍ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ጥሪ የሚመረጥ ነው። ስልጣነ ክህነትን ለመቀበል የተለያዩ መስፈርቶች መሟላት ያለባቸው ሲሆን የአሰጣጥ ሥርዓቱ መሠረት ያደረገውም ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐዋ (13፣2፣ 6፡6)፣ ዮሐ(20፡22)፣ 1ኛ ጢሞ (4፡4) ነው። ይህም በፆም፣ በፀሎት፣ በተቀባዩ ራስ ላይ እጅን በመጫን፣ በፊቱ ላይ እፍ በማለት በጳጳሳት አማካይነት የሚሰጥ ነው። አባ ኤጲፋንዮስ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን ያለውን የክህነት ስልጣን ልዩነት ሲያስረዱ በብሉይ ዘመን የነበረው ክህነት ፍፁምና ምሉዕ ያልነበረ፣ በዘር የመጣውን የውርስ ሃጢአት ሊያስወግድ የማይችል ሲሆን በሐዲስ ኪዳን ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የዘር፣ የውርስ ሃጢአትን ማስወገድ እንደሚቻል፣ ፍፁም የሆነና ሕፀፅ የሌለበት ስልጣን ነው (1999፣123-124) በማለት ይገልጻሉ።

በሐዲስ ኪዳን የክህነት መሠረታዊ ዓላማ የሰው ልጅ ሁሉ በሃጢያት ምክንያት ሞትን እንዳይሞትና እግዚአብሔርን እንዲያመልክ ማድረግ ነው።ይህም ይሆን ዘንድ ካህናት ለዘለዓለም ህይወት የሚሆነውን መመሪያ ማሳወቅ፣ የሰው ልጅ ሁሉ በፍቅር ተስማምቶ፣ ተከባብሮ እየተረዳዳ በአንድነት እንዲኖር፣ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት እንዲሁም

ሃይማኖታዊ ሥነምግባርን ማስተማር እና ሥርዓተ አምልኮትን ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው ፍትሃነገስት ፣ዲስቅልያ እና ሌሎች የስርአት መጽሃፎች ያስረዳሉ።

በኢትዮጵያ የሥልጣነ ክህነት አጀማመሩን በተለይ መንበረ ጵጵስናን አግኝታ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ያለው የአደረጃጀት ሁኔታ ሉሌ (1986፡124) እና ሰሎሞን (2001፣71)እንደገለጹት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ከኖረ እና የአክሱምን ነገሥታት የክርስትና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ካደረገ በኋላ ወደ ግብፅ ሀገር በመሄድ ከአቡነ አትናቴዎስ የጵጵስና ማዕረግ ተቀብሎ የመጀመሪያው ጳጳስ ለመሆን በቅቷል። በወቅቱ በግብፅ የነበሩ የሃይማኖት ባለስልጣናት ፣ እለ እስክንድሮስና አትናቴዎስ የአርዮስን የክህደት ሀሳብ (ወልድ ፍጡር ነው ማለቱ) ለመቃወም ወደ ኒቅያ ሄደው ነበር። ፍሬምናጦስም የጵጵስናውን ማዕረግ ለመቀበል ከኒቅያ እስከሚመለሱ ድረስ ለጥቂት አመታት መጠበቅ ነበረበት። ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስም የጵጵስና ማዕረግን ብቻ ሳይሆን ወልድ ከአብ ጋር በመለኮቱ አንድ መሆኑን የሚያስረዳና የሚያጸድቅ መግለጫን ጭምር ይዞ መጥቷል።

በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ መንበረ ጵጵስናን ያገኘችው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ጳጳሳት ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን እየተሾሙ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት አገልግሎት ይሰጡ ነበር። እንደ አክሊሉ (1999፣38-39) አገላለፅ ኢትዮጵያ ክህነትን የመስጠት ስልጣን ሙሉ በሙሉ እስክትረከብ ድረስ ኢትዮጵያን ያገለግሉ የነበሩ ጳጳሳት ግብፃውያን ነበሩ። ማዕረገ ጵጵስናውም ይሰጥ የነበረው በዚያው በግብፅ ሀገር በመሆኑ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ለ1600 ዓመታት 111 ግብፃውያን ጳጳሳት ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አገልግሎት ሰጥተዋል።

ለ1600 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያ ጳጳሳትን ለማስመጣት የተለያዩ ገፀበረከቶችን ወደ ግብፅ ሀገር ትልክ ነበር። ይህም ገጽታ የሀገሪቱን ሀብት በማቆርቆዝ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳደረ ነበር። ከዚህም አልፎ ተልከው የሚመጡት ጳጳሳት የኢትዮጵያን ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ቋንቋ እና ሌሎች ማህበራዊ እሴቶች በቀላሉ የማይረዱ ስለነበሩ በሥርዓተ አምልኮው ላይ እና ከምዕመናን ጋር የነበራቸው ተግባቦት ችግር ላይ የወደቀ እንደነበር የተለያዩ የታሪክ እና የሃይማኖት መጻህፍት ገልፀዋል። ከዚህም በተጨማሪ ይላኩ የነበሩት ጳጳሳት አንድ አንድ ብቻ በመሆናቸው መላውን የኢትዮጵያ ክፍል ለማካለል እና አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት አስቸጋሪ ሁኔታ ነበር ። ኢትዮጵያ ከግብፅ ጳጳሳትን ታስመጣ የነበረበት ምክንያት

በፍትሃነገሥት አንቀጽ 4 ቁ.10 ላይ "የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቹ ወገን፣ በራሳቸው ፈቃድ ሊቀ ጳጳሳትን ለራሳቸው አይሹሙ። ጳጳሳቸው ከእስክንድርያው በዓለ መንበር ሥልጣን በታች ነውና። " የሚል ኃይለቃል በመገኘቱ ነው። ይህ ቃል ኢትዮጵያ ጳጳሳትን የመሾም ብቃት ሳይኖራት ቀርቶ ሳይሆን የግብፃውያን ሴራ እንደሆነ የተለያዩ ሊቃውንት ተረድተው ብርቱ ትግል ማድረጋቸውን አክሊሉ (1999፡40) አስረድቷል።

ለ1600 ዓመታት በዚህ ሁኔታ የቆዩት ኢትዮጵያውያን በ1921 ዓ.ም በንግስት ዘውዲቱ እና በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ጥረት ይህ ሥርዓት ተገርስሶ አምስት የኢትዮጵያ መነኮሳት ወደ ግብፅ ሀገር በመሄድ ማዕረገ ጵጵስናን እንዲያገኙ ተደርጓል። ከእነዚህ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ጋር ሊቀ ጳጳሱ (አቡነ ቄርሎስ) አብረው መጥተው ነበር። በኋላ ግን በኢጣልያ ወረራ ጊዜ በቤተክርስቲያን ላይ ከባድ ችግር ሲደርስ እኒህ ጳጳስ ኢትዮጵያን ጥለው ሸሽተው ሄደዋል። በዚህ ጉዳይ ላይም ሊቃውንት ተሰብስበው ከተወያዩ በኋላ ለጵጵስና ማዕረግ ከተሾሙት ጳጳሳት መካከል አንዱን ሊቀጳጳስ አድርጎ በመሾም ሌሎቹን የጵጵስና ማዕረግ እንዲጥ ማድረግ የሚል ውሳኔ አፅድቀዋል። በመሆኑም አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተመርጠው ሌሎች መነኮሳትን በጵጵስና ማዕረግ ሹመዋል።

አቡነ አብርሃም በ1931 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አቡነ ዮሐንስ ተሹመው እሳቸውም ሌሎች አምስት ጳጳሳትን ሹመዋል። የኢጣሊያ ወረራ ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ በ 1940 ዓ.ም አቡነ ዮሳብ በግብፅ ሀገር አምስት ጳጳሳትን ሾመው የላኩ ሲሆን ወደ ሮም ሀገር ሸሽተው ሄደው የነበሩት አቡነ ቄርሎስ በ1943 ዓ.ም ሲያርፉ በምትካቸው አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ በመሆን ተሹመው አምስት ጳጳሳትን ለመሾም በቅተዋል። ከዚያም በኋላ አቡነ ባስልዮስ በ1951 ዓ.ም የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ፓትሪያርክ በመሆን በመሾማቸው ኢትዮጵያ ከግብፅ ጥገኝነት ሥር ተላቃ የራሷን ዜጎች በራሷ ምድር ክህነት ለመስጠት በቅታለች። ቻሎት (2002:38-39)፣ መንግስቱ እና አሳምነው (2000፣ 148-157)፣ ፒ.ኬ ማቲው (1970፡55-56) እንደገለጹት አቡነ ባስልዮስን ጨምሮ በኢትዮጵያ የተሾሙት የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ አምስት ሲሆኑ እነሱም አቡነ ቴዎፍሎስ (1962)፣ አቡነ ተክለሃይማኖት (1968)፣ አቡነ መርቆርዮስ (1980) እና በአሁኑ ጊዜ ያሉት አቡነ ጳውሎስ (1984) ናቸው።

### 3.2 የሥልጣነ ክህነት ምንነት

#### 3.2.1 የሥልጣን ምንነት

ሥልጣን ለሚለው ቃል በነገሮች ላይ ሁሉ የመምራት፣ የመፍረድ፣ የመግዛት ማንኛውንም ነገር የማድረግ ሙሉ መብት ነው በማለት መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1992፣64) ጽንሰ ሃሳባዊ ብያኔ ሲሰጥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናት ምርምር ማዕከል በተዘጋጀው መዝገበ ቃላት (1993፣107) እንዲሁ አንድን ነገር ለመስራት ወይም ለማሰራት የሚያስችል መብት፣ የዲቁና፣ የቅስና ማዕረግ እና ክህነት የሚል ፍቺ ሰጥቶታል።

በዚህ ጥናት የሥልጣነ ክህነትን ሥርዓተ ክዋኔ ለመመርመር እና ፎክሎራዊ ገጽታውን ለማሳየት "ሥልጣን" የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ የሚጠቀመው ከላይ እንደተገለፀው ካህናት የተቀደሰ መንፈሳዊ ተግባር ለማከናወን የሚችሉበትን ሙሉ መብት፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን እና ስርአተ አምልኮን ለመፈጸም፣ ለመፍረድ (ለማውገዝና ለመፍታት) ለማንፃት፣ ለማስተማር፣ … የሚያስችላቸውን ኃይል በተመለከተ ይሆናል።

#### 3.2.2 የክህነት ምንነት

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ለክርስትና ህይወታቸው መሠረት የሆኑ ፣የእግዚአብሔር ፀጋና መንፈስ እንዲያድርባቸው የሚረዱ ሰባት ምስጢራተ ቤተክርስቲያን እንዳሉ ይነገራል። እነሱም ምስጢረ ጥምቀት፣ ምስጢረ ሜሮን፣ ምስጢረ ቁርባን፣ ምስጢረ ክህነት፣ ምስጢረ ተክሊል፣ ምስጢረ ንስሃ እና ምስጢረ ቀንዲል ናቸው። እነዚህ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን የራሳቸው ትርጉምና ለምዕመናን የሚሰጡት አገልግሎት አላቸው።

ምስጢረ ክህነት ከሰባቱ ምስጢራት መካከል በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ቀዳሚዎቹ ሶስቱን ምስጢራት ክርስትያን የሆነ ሰው ሁሉ የግድ ሊቀበላቸው ይገባል። እነዚህን የማይቀበል ሰው የእግዚአብሄርን ጸጋና ልጅነት እንደማያገኝ ይታመናል። ምስጢረ ክህነት፣ ተክሊል እና ቀንዲል ግን እግዚአብሔር ላደለው ለተለየ ሰው ብቻ የሚሰጥ መሆኑን አበራ (1996፡240)፣ ሀብተማርያም (1953፡123) ገልፀዋል።

ክህነት ማለት መንፈሳዊ አገልግሎት ማለት ነው። መልአኩ (1993፡ 117)፣ ብርሃኑ (1990፡90)፣ አባ ገብርኤል (1993፡159)፣ አበራ (1996፡258)፣ አስራት (1991፡228-229)፣ አክሊሉ (1999፡1)፣ ሀብተማርያም (1953፡35)፣ ኃየሎም (2002፡108)፣ አቡነ ኤጲፋንዮስ

(1998፡120-159)፣አበራ እና ዮሐንስ (2002፡81)፡፡ ብዙዎቹ ፀሐፊዎች ክህነት ማለት ማንኛውም አገልግሎት ሳይሆን የተቀደሰ እና መንፈሳዊ አገልግሎት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ሀብተማርያም (1953፡36-37) ክህነት የነፍስና የስጋ ድህነትን መስጠት የሚያስችል አገልግሎት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህን ሲሉ የነፍስ ድህነት ሰማያዊ ፀጋን የሚያጎናጽፍ ሲሆን የስጋ ድህነት ደግሞ በሽታ መፈወስን፣ማስታረቅን ፣ ማረጋጋትን፣ ማጽናናትንና በአጠቃላይ ሰላም የሞላበት ምድራዊ ህይወት ማግኘት የሚቻልበት መንገድ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስለ ክህነት ከፍተኛነት የገለፁ ዮሐንስ አፈወርቅ "ካህን በምድር ይኖራል እንጂ በሰማይ ከሚኖሩት ከመላዕክት ነገድ ይቆጠራል" እንዲሁም ጴጥሮስ "እናንተ ግን የተመረጠ የመንግስትና የክህነት ወገን ናችሁ፤ የተቀደሰች ዘር፤ ለርስት የተለየ ህዝብ፤ ከጨለማ ወደ ማይነገር ብርሃን የፀራችሁን ሥራ ትገልፁ ዘንድ" ማለታቸውን በመጥቀስ ለክህነት ያላቸውን ክብር በአጽንኦት ገልፀዋል፡፡

ክህነት "ተክህነ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ (የተገኘ) ሲሆን ትርጉሙም አገልግሎት ማለት ነው፡፡ አገልግሎቱን የሚሰጥ ሰው (ባለሙያው) ካህን ሲባል አገልግሎቱ ወይም ሙያው ደግሞ "ክህነት" እንደሚባል ሀብተማርያም (1953፡35)፣ ኤጲፋንዮስ (1998፡120)፣ ብርሃኑ (1990፡91)፣ አበራ እና በቀለ (2002፡81) ገልፀዋል፡፡

ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948:522) ክህነት ካህን ቄስ፣ ጳጳስ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ፣ የህዝብ መሪ፣ አስተማሪ፣ መንፈሳዊ አባት ማለት መሆኑን ሲገልጹ ደስታ ተክለወልድም ዲያቆን፣ ቄስ፣ ደብተራ፣ በቤተ መቅደስ (በምኩራብ በቤተክርስቲያን በመስጊድ የምላክ የጣዖት) አገልጋይ፣ የሚቀድስ፣ የሚያወድስ፣ የሚዘምር፣ ሳታት ቋሚ፣ አወዳሽ፣ ቀዳሽ፣ (1962፡641) በማለት ፍቺ ሰጥተዋል፡፡ ክህነት ለሚለው ደግሞ መንፈሳዊ ሹመት፣ አገልግሎት በማለት ፍቺ የሰጡ ሲሆን የሁለቱን ፅንሰ ሀሳብ (የካህን እና ክህነት) ጥምር ይዘት ስንመለከት መንፈሳዊ አገልግሎትን የሚሰጥ ሰው እና የአገልግሎቱን አይነት እንደሚያመለክት ያስዳል፡፡

ክህነት ከፍተኛ የፀጋ ስጦታን፣ ማዕረግን እና ሥልጣንን የሚያስገኝ ነው፡፡ ክህነት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመፈፀምና ለማስፈፀም፣ ሃጢአትን ይቅር ለማለት፣ ምዕመናንን ለመምከር፣ ለመጠበቅ እና ለማስተማርና ለመባረክ በአጠቃላይም ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን ለማስፈፀም የሚያስችል ስልጣን እንደሆነ አበራ (1996፡258)፣ አስራት (1991፡288-289)፣

አክሊሉ (1999፡1)፣ አባ መልከ ጼዴቅ (1994፡283)፣ አቡነ ኤጲፋንዮስ (1998፡120) ይገልፃሉ፡፡

አዕምሮ (1970፡37) "*Holy orders" is the sacrament through which an ordinand receives authority to administer the sacraments and conduct other religious services.*" በማለት አስረድቷል፡፡ከዚህ ጽሁፍ መረዳት እንደምንችለው ካህናት በቤተክርስቲያን ትልቁን ሥፍራ ወይም ሥልጣን የያዙ መሆናቸውንና ማዕረጋቸውም በቤተክርስቲያን ከፍተኛውን ስፍራ የያዘ መሆኑን ነው፡፡

ክህነት ሁሉም ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የሚቀበለው ሳይሆን በፈቃደ እግዚአብሔር የተመረጡ እና በአንብሮተ እድ በጳጳሳት አማካይነት ለሚሾሙ ብቻ የሚሰጥ ሲሆን ተደግሞ (እንደገና) የማይሰጥ የምስጢር አይነት ነው፡፡ (አክሊሉ፣ 1999፡1)፣ ብርሃኑ (1990፡90)፡፡

በአጠቃላይ ሥልጣነ ክህነት በሰው ሀሳብና መብት የሚሰጥ ሹመት ሳይሆን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ፀጋ ነው፡፡ ሥልጣኑም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ ሁለቱንም ማገናኘት የሚያስችል መሆኑን አባይነህ የሐዋ 20፡28 እና ኤር 3፡19 ላይ ያሉትን ጥቅሶች በመጥቀስ ያስዳል፡፡ እንዲሁም የሥልጣነ ክህነትን አጠቃላይ ገጽታ በሐመር መፅሔት ላይ

> *ካህን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሆኖ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኛል፡፡ ስለራሱና ስለህዝቡ መስዋዕትና ፀሎት በማቅረብ፣ በመባረክ፣ በመቀደስ፣ በማጥመቅ፣ በማቁረብ፣ በማስተማር፣ ሃጢያትን በማስተስረይ… ወዘተ አገልግሎት ይፈፅማል፡፡ ይህም ስልጣን የሚሰጠው ከእግዚአብሔር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ስጦታ ሰው መስጠት አይችልም፡፡ እግዚአብሔር ግን በመረጣቸው አድሮ ለሚገባቸው ስልጣኑን እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡ የሐዋ. 13÷2፣ 6÷6፡፡ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ስርዓተ ሲመት (የሹመት ሥርዓት) ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይፈፀማል፡፡ (1992፡ ቁጥር 5 ገጽ 8 )*

በማለት ተገልጿል፡፡

## 3.3 የስልጣነ ክህነት ደረጃዎች እና ምንነታቸው

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አይነቶች ሶስት ሲሆኑ እነሱም ዲቁና፣ ቅስና እና ኤጲስ ቆጶስነት በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ የክህነት አይነቶች ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ አንዱ ከአንዱ በደረጃ የሚለያዩ ሲሆን የሚመሳሰሉበት ባህሪያቸው ደግሞ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት መቻላቸው ነው፡፡ (አዕምሮ 1970፡ 37፣ ኤጲፋንዮስ 2002፡ 129፣ ፒ.ኬ. ማቲው 1970፡ 55-66 አባ ገብርኤል 1993፡162፣ ኃየሎም 2002፡109፣ ሀብተማርያም 1953፡35)

ሦስቱ የስልጣነ ክህነት አይነቶች “ስልጣን” ናቸው ለመባል የቻሉበት ምክንያት ስልጣኑን ለመቀበል የሚደረግላቸው ጥሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆኖ በእግዚአብሔር ፀጋ የማሰር፣ የመፍታት፣ የመገዘት፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን እና አምልኮን የመፈፀም ብቃት ስላላቸው ነው፡፡ እነዚህ የሥልጣነ ክህነት አይነቶች ለሁሉም በዘፈቀደ የሚሰጡ ሳይሆኑ ለተመረጡት ብቻ የሚሰጡ ሰማያዊ ሹመቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ሥልጣነ ክህነቱን ሲቀበሉ መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸዋል፡፡ ይህም እንደሥልጣን አይነቱ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የመፈፀም፣ ሰዎችን ከሃጥያት የማንፃት ፣ ከክፋት መንገድ መመለስ፣ ከበሽታ የመፈወስ፣ ከተለያዩ እስራቶች (የእርኩስ መንፈስ) መፍታት እና ሌሎች በሰው አእምሮ እና ችሎታ ሊፈፀሙ የማይችሉትን የተለያዩ ነገሮች የማከናወን ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

አበራ እና ዮሐንስ ሥልጣነ ክህነት ለተመረጡት ብቻ እንጂ ሁሉም ሰው ሊቀበለው የማይቻል ፀጋ መሆኑ ለማስዳት የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> *“... ክህነት እግዚአብሔር ባወቀ ተመርጠው የሚሾሙበት ፀጋ እንጂ ሁሉ ስለአመነ ብቻ ገንዘብ የሚያደርገው ሥልጣን አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ሰውን ለክህነት መርጠን ይበቃል የምንለው እኛ (ሰዎች) ብንሆንም ቤተክርስቲያንን በመግቦቱና በጥበቃው የማይለይ መንፈስ ቅዱስ አብሮ እንዳለ እናምናለን፡፡ ከምርጫው ውስጥ ጥበበ እግዚአብሔር አለበትና፡፡ በጥሩ ክህነት የሰዎች ይሁንታና ምርጫ ሳይሆን ሰማያዊ ምርጫ ነው፡፡ (2002፡82).*

የሦስቱ ሥልጣነ ክህነት አይነቶቸ እንደደረጃቸው የሚለያዩ ሲሆን ምንነታቸው፣ አንዱ ከአንዱ የሚለይባቸው ባህሪ እና አገልግሎታቸው (ሙያቸው) እንደሚከተለው ነው፡፡

### 3.3.1 ዲቁና

ዲቁና ዲያቆን (DIAKONIA) ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አገልጋይ፣ ተላላኪ፣ ረዳት ማለት ነው አክሊሉ (1999፡11)፣ አበራ እና ዮሐንስ (2002፡9፣ 98) መልአኩ (1993፡145)፡፡

ዲያቆን አገልግሎቱን ለሚፈፅመው ሰው የተሰጠ መጠሪያ ሲሆን አገልግሎቱ ደግሞ ዲቁና ይባላል፡፡ ዲቁና የተጀመረው በሃዋርያት ዘመን መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐዋ. (6÷1-6) ያለውን በመግለፅ መልአኩ (1993፡146) ያስረዳል፡፡ እንደ አበራ እና ዮሐንስ (2002፡92፣ "ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት" (1993፡60)፣ አባ ገብርኤል (1993፡163) እና ሌሎችም ፀሐፊዎች አንድ ግለሰብ የዲቁናን ሥልጣን ከመቀበሉ በፊት የሚያልፍበት አራት ማዕረጎች አሉ፡፡ እነሱም መዘምር፣ ዐጻዌ ኆኅት፣ አናጉንስጢስና ንፍቀ ዲያቆን ናቸው፡፡ የአራቱን ማዕረጋት ምንነት እና አገልግሎት ስንመለከት፡-

1.ዐጻዌ ኆኅት፡- ይህ የግዕዝ ቃል ሲሆን "ደጆችን የሚዘጉ" ወይም "በረኞች" የሚል ትርጉም አለው፡፡ የዐጸውተ ኀዋኀው ተግባር በቤተክርስቲያን ደጃፍ ሆነው እንግዳ የሆኑ ሰዎች (ከህዝበ ክርስቲያን የተለዩ) እንዳይገቡ ዘወትር የቤተክስቲያንን ደጆች የሚጠብቁ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚጠብቁት በወንዶች መግቢያ በኩል ያለውን በር ነው፡፡

1) መዘምር፡- አመስጋኝ፣ ዘማሪ የሚል ትርጉም ያለው ነው፡፡ የመዘምር ተግባር የያሬድና የዳዊት መዝሙራትን በማጥናት ቤተክርስቲያንን ማገልገል ነው፡፡ መዘምር ከመርጌትነት ማዕረግ የደረሱም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

2) አናጉንስጢስ፡- ይህ ቃል Anagonosma ከሚል የግሪክ ቃል የተገኘ ነው፡፡ ትርጉሙም አንባቢ ማለት ሲሆን ከፍ ካለ ቦታ ላይ በመሆን መጻሕፍትን ለምዕመናን የማንበብ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

3) ንፍቀ ዲያቆን፡- ከሁለት ቃላት በጥምረት የተገኘ ስያሜ ነው፡፡ ንፍቅ ማለት ግማሽ (እኩሌታ ማለት) ነው፡፡ ትርጉሙ ረዳት ዲያቆን የሚለውን ይይዛል፡፡ አገልግሎቱም ዋናውን ዲያቆን በተለያዩ ነገሮች መርዳት ነው፡፡

የዲያቆን ሥልጣን የሚመጣው ከነዚህ አራት ማዕረጋት ቀጥሎ ሲሆን አንድ ግለሰብ ዲያቆን ለመሆን እነዚህን ማዕረጋት በቅድሚያ መቀበል አለበት፡፡ አባ ገብርኤል (1993፡162) እና ሌሎች ፀሐፊዎች ስለእነዚህ አራት ማዕረጋት ሲያስረዱ በአንብሮተ ዕድ የማይሰጡ ነገር ግን የመንፈሳዊ አገልግሎት ሹመቶች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

እንደዚሁም ከአራቱ በተጨማሪ ዲያቆናዊት የሚል ማዕረግ መኖሩን ይገልፃሉ፡፡ ዲያቆናዊት የሴት ዲያቆን ስትሆን የምትሰጠው አገልግሎት ሴት ስትጠመቅ ካህኑን የምትረዳ ናት፡፡ከዚህ ውጪ ሴት በቤተመቅደስ ውስጥ ገብታ ስርአተ ቤተክርስቲያንን እና አምልኮን ለመፈጸም የሚያስችል ስልጣን አልተሰጣትም፡፡ በፍትሃ ነገስት እንደተገለጸው ዲያቆናዊት ለመሆን የምትመረጥ ሴት እድሜዋ 60 አመት የሞላት መሆን አለባት፡፡በንጽህናና በአንድ ባል ተወስና የኖረች መሆንም ይጠበቅባታል፡፡ መልአኩ (1993፡158 ) እንደገለጸው ከብሉይ ጀምሮ ሴት በክህነት ደረጃ ላይ ሆና ያከናወነችው ተግባር የለም፡፡ከዚያ ዘመን ተያይዞ የመጣ ታሪክ ባለመኖሩም በሃዲስ ኪዳን ላለመኖሩ ምክንያት መሆኑን ይገልጻል፡፡ጳውሎስ ባስተላለፈው ትእዛዝ መሰረት የ60 አመት ባልቴት ዲያቆን ለመሆን ስትፈልግ ከኤጲስ ቆጶሱ ዘንድ ጸሎትና ቡራኬ ትቀበላለች፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር የሚነሳው ሊቀ ዲያቆናት የተባለው ማዕረገ ክህነት ነው፡፡ይህ የክህነት አይነት ከዲያቆን ከፍ ያለ አገልግሎት የሚሰጥና የዲያቆናት አለቃ የሆነ ነው፡፡ ስራውም መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ማስተባበር፣ ዲያቆናትን በአገልግሎታቸው መቆጣጠር ነው፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ ለመጀመሪያ ጊዜ የቤተክርስቲያን ሊቀ ዲያቆን እንደሆነ በሐዋ. (6÷8) ተጠቁሟል፡፡

የዲያቆን ተግባር ወይም አገልግሎቱ ለጳጳሱና ለቄሱ መታዘዝ፣ የቤተክርስቲያን ሥርዓትን መጠበቅና ማስጠበቅ፣ ቅዱሳት መፃሕፍትን ማንበብ፣ ማስተማር፣ መስበክ፣ በፀሎተ ቅዳሴ ጊዜ ህዝቡ እንዲፀልዩ ማትጋት ነው፡፡ በሥርዓተ ቁርባን ጊዜም ከካህኑ ጎን በመቆም ደሙን ያቀብላል፡፡

### 3.3.2 ቅስና

ቅስና “ቀስ” ከሚል የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አገልግሎት ማለት ነው፡፡ መልአኩ (1993፡138) ቅስና የሚለው ቃል በእብራይስጥ “ቅሻሻ” ማለት እንደሆነ እና ቅስና ከሚለው ቃል ጋር የድምፅ ተመሳሳይነት እንዳላቸው ያስረዳል፡፡ በመሆኑም ይህ ቃል

ከእብራይስጥ የተወሰደ ቃል ሊሆን እንደሚችል ጠቁሞ በሌሎች ቋንቋዎችም ለምሳሌ በሱርስት ቃሽ፣ ቃሻሽ በትግርኛ ቀሽ፣ በአማርኛ ቄስ እንደሚባል አስረድቷል፡፡ አበራ እና ዮሐንስ (2002፡101) ደግሞ ቅስና በሶርያውያን "ካሺሾ" ተብሎ የሚጠራ መሆኑን እና በሁለቱም ቃል መካከል የድምፅ ተመሳስሎ በመኖሩ ቃሉ ከሶርያውያን የተገኘ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ በሁለቱም ፀሐፊዎች ዘንድ ቀሲስ የሚለው ቃል በአማርኛ ቀጥታ ትርጉሙ ታላቅ፣ ሽማግሌ፣ የሚል ፍቺ እንዳለው ተጠቁሟል፡፡ ይህ ትርጉም ግን የሚይዘው ሀሳብ የቄሱ ዕድሜ ትልቅ መሆኑን የሚያመለክት ሳይሆን በ ያዕ. (5÷14)፣ ሐዋ.(14÷23፣ 20÷17፣ራዕ. (4÷10፣1፡16)፣1ኛጴጥ. (5÷1-4)፣1ኛጢሞ. (4÷14)፣2ኛ ዮሐ.(1÷1) ያሉ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማመልከት የቅስና ተግባር የላቀ፣ ኃላፊነቱም ከፍ ያለ እና አገልግሎቱም ጳጳሳት ከሚሰጡት ሹመት በስተቀር ሌሎችን ሥርዓቶች መፈፀም የሚያስችል መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ቄስ የሚለው ቃል መንፈሳዊ አገልግሎትን የሚሰጥ ግለሰብ መጠሪያ ሲሆን ቅስና ደግሞ የሚከወነውን ተግባር (ሙያውን) የሚገልፅ ነው፡፡ ቅስና ከኤጲስ ቆጶስ ሥልጣን ደረጃ ዝቅ ያለ ሲሆን ከዲቁና ሥልጣን ደግሞ ከፍ በማለት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በመሆኑም ስድስቱን ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ማለትም ምስጢረ ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቁርባን፣ ንስሃ ተክሊል እና ቀንዲል መፈፀም ያስችላል፡፡ ምስጢረ ክህነትን መስጠት፣ ሜሮንን ማዘጋጀት፣ ቤተክርስቲያንን ለመጀመሪያ ጊዜ ባርኮ ለአገልግሎት እንዲውል ማድረግ፣ ታቦትን መባረክ፣ አዳዲስ ንዋያተ ቅድሳትን ባርኮ ለአገልግሎት ማዋል እና ማመንኮስን ግን ቄስ ሊያከናውናቸው የማይችላቸው ተግባራት መሆናቸውን በፍትሃነገሥት 1962፡71 ተገልጿል፡፡

### 3.3.3 ኤጲስ ቆጶስ

ኤጲስ ቆጶስ ከፅርዕ የተገኘ ቃል ሲሆን በግዕዝና በአማርኛም ቃሉ ሳይቀየር አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

መልአኩ (1993፡129) ስያሜውን በተመለከተ ሲያስረዳ በጽርእ ቋንቋ በተፃፈው መጽሐፍ ቅዱስ ኤጲስ ቆጶስ ተብሎ ተጽፎ ሳለ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ቦታ ላይ ቃሉን እንዳለ በመውሰድ፤ ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ጳጳስ ተብሎ ተተርጉሞ የተቀመጠ በመሆኑአንዳንድ

ጸሐፊዎች ለኤጲስ ቆጶስ ጽንሰሃሳብ ጵጵስና የሚለውን ቃል መጠቀማቸው በቃሉ ትርጉም ላይ የተፋለሰ ፍቺ እንዳመጣ ያስረዳል፡፡

ኤጲስ ቆጶስ የሚለው ቃል ትርጉም በአማርኛ ጠባቂ ማለት ሲሆን በግዕዝ ደግሞ ኖላዊ ማለት ነው፡፡ ኤጲስ ቆጶስ ከሦስቱ የክህነት ደረጃዎች ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ እና የቤተክርስቲያን ራስ የክርስቶስ ምትክ ወይም ተወካይ ማለት ነው፡፡

የኤጲስ ቆጶስ ማዕረግ ክህነት ከሁሉም ከፍ ያለ፣ ሥልጣንን ሁሉ በስሩ የሚያጠቃልል መሆኑን አባ አበራ (1996፡262) ሲያስረዱ የክርስቶስ እንደራሴ የሆነ፣ ሐዋርያትን ተመስሎ የሚሰራ፣ ሥልጣነ ክህነትን በምልዓት የያዘ፣ ቀሳውስትን እና ዲያቆናትን በአንብሮተ ዕድ የመሾም መብትና ኃላፊነት ያለው ነው በማለት ነው፡፡ እንዲሁም መልአኩ (1993፡ 131፣ ኤጲስ ቆጶስ በቤተክርስቲያን ከፍተኛውን ሥልጣን የያዘ የቤተክርስቲያን መሪ፣ የአስተዳደር፣ የአምልኮትና የማስተማር ሥራዎችን ሁሉ የሚመራ፣ ቤተክርስቲያንን ባርኮ የሚመሠርት በአጠቃላይ ማንኛውንም የአምልኮ ሥራ ፈቅዶና ባርኮ የሚጀምር መሆኑን ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ ሦስቱ አበይት የስልጣነ ክህነት ደረጃዎች የቤተክርስቲያን ሥርዓትን እና አምልኮን ለመፈፀም ወሳኝ ናቸው፡፡ አገልግሎታቸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ መሠረት በሦስት ወገን ተከፍሎ የሚታይ ሲሆን እነሱም ትምህርተ ወንጌልን ማስተማር (ማቴ 28፡19-20)፣ የህዝቡን ሃጢአት ማስተስረይ፣ የቅድስናን ጎዳና ማሳየት ፣ (ዮሐ 20፡23)፣ (1ኛ ጴጥ 1÷17) እና ምዕመናንን መጠበቅ (ዮሐ 21÷ 15-17) መሆናቸውን አባ አበራ (1996፡261-262) ይገልፃሉ፡፡

## 3.4 በኢትዮጵያ ኦርቶክዶስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት ተዋረድ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አሁን ያለው የሥልጣን ክህነት ተዋረድ በጥንት ቤተክርስቲያን የነበረውን ጠብቆ የቆየ ነው፡፡ የሥልጣን ተዋረድ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ የእንግሊዝኛው “HIERARCHY” የሚተካው ሲሆን እንደ ፒ.ኬ ማቲው ቃሉ ከግሪክ የተገኘ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት “HLEREUS” ማለት ካህን (priest) ማለት ሲሆን ARCH’E ደግሞ መሪ (rule) ማለት ነው (1970፡55) ፡፡

ፒ.ኬ ማቲው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (ማቴ 9÷6፣10÷1) ፣(ሉቃ 9÷1 ) (2ኛ ቆሮ 10÷8) ያሉትን ጥቅሶች መሠረት በማድረግ በሐዲስ ኪዳን “ሥልጣን” የተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስ የነበረውን ሃይልና ያከናወናቸውን ተግባራት እንዲሁም አስራ ሁለቱ ሐዋርያት

ነገሮችን ያከናውኑ ዘንድ የሚያስችላቸውን ብቃት ፤ በዚህም የሚፈፅሙትን ተግባር እንዲሁም በተግባራቸው ይሰጡ የነበረውን አገልግሎት መሠረት ያደረገ መሆኑን ገልጾ በአጠቃላይ የሥልጣን ተዋረድ (HIERARCHY) ዲቁና፣ ቅስና እና ኤጲስቆጶስና መሆናቸውንና ካህናት በሥልጣናቸው የሚሰጡትን አገልግሎት መሆኑን አብራርቷል ። ይህ የሥልጣን ተዋረድ በሐዲስ ኪዳን ያለውን ገጽታ ሲያመለክት በአገልግሎቱ ላይ የተመሠረተ እንጂ ካህናት የያዙትን ሥልጣን ብቻ የሚጠቁም አለመሆኑን አመልክቷል።በአንድ ማህበረሰብ ወይም ተቋም ውስጥ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚኖረው ማዕረግ ተቋሙን ለመመስረት (ለመገንባት) የሚያስችል ቅርጽ ሲኖረው እርስ በርስ የሚኖራቸው ግንኙነትና ተያያዥነት ደግሞ ተዋረድን ያመለክታል ። ከአንዱ ቀጥሎ ወደ ሌላው የሚሸጋገርበት ተጠየቃዊ አካሄድ የተቋሙን አደረጃጀት ፣ አመሰራረት፣ አገነባብ (structure) የሚያሳይ ነው።

ራድክሊፍ ብራውን (1952፡9) አንድ ማህበረሰብ ወይም ተቋም እንዴት እንደሚዋቀር ሲገልፅ በቅድሚያ የተለያዩ ነገሮች ቅደም ተከተላዊ አሰዳደር ወይም ቅንጅት እንዴት እንደሆነ በማስረዳት ከዚያም አንድ ግለሰብ በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝበትን ቦታ እንደሚያመለክት ይገልፃል። የአንድ ማህበረሰብ ወይም ተቋም አወቃቀር ህልውናው ተጠብቆ የሚኖረው ቀጣይነት ሲኖረው ብቻ እንደሆነም ያብራራል። ቀጣይነት ሲባል በመዋቅራዊ ሂደት ውስጥ ማንኛውም አዲስ ማህበረሰባዊ ህይወት የሚመሰረትበት ከዚያም ህልውናውን እና የሚኖርበትን ህግ ጠብቆ የሚቀይበት እንዲሁም አንዱ ከአንዱ ጋር ያለውን ተዛምዷዊ ቅንጅት የሚመለከት መሆኑን አስረድቷል።

ራድክሊፍ ስለማህበረሰባዊ መዋቅር ሲያስረዳ ትኩረት ሰጥቶ የገለፀው ማህበራዊ ግንኙነትን ነው። ማህበራዊ ግንኙነት አንድ ማህበረሰብ የሚኖርበትን ወይም የተመሰረተበትን ቅርጽ ይዞ በቀጣይነት እንዲቆይና ማህበራዊ አደረጃጀትን ለመመስረት የሚያስችል መሆኑን ነው።

ይህንንም በአንድ ግለሰብ ብቻ መመስረት የማይቻል ሲሆን ማህበራዊ ሂደት የግድ መኖር አለበት። ይህ ሲሆንም የአንድን ማህበረሰብ ህልውና ጠብቀው የሚቆዩ እሴቶች ፣ ወጎች፣ ባህሎች ፣ልማዶች ሁሉ ተግባራዊ ይሆናሉ። በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ማንኛውም መስተጋብር ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት በማህበረሰቡ ህግ ፣ደንብ ፣ምሳሌ የሚገደብ ወይም የሚጠበቅ ነው። በመሆኑም አንድ ግለሰብ ማህበረሰቡ ባወጣው ህግና ደንብ መሰረት መንቀሳቀስ እንዳለበት ያስረዳል። ይህም አንድ ማህበረሰብ የሚተዳደርበትን

ስርዓትና ደንብ የያዘ "ተቋም" እንደሚፈጥር አብራርቷል። በአጠቃላይ ማህበረሰባዊ መዋቅር የሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ተቀናጅቶ የሚፈጥረው መሆኑን የሚከተለውን በማለት ይገልፃል።

> *Social structure as an arrangement of persons in institutionally controlled or defined relationships, such as the relation ship of king and subject, that of husband and wife, and to use organization as referring to an arrangement of activities. (1952:11)*

ራድክሊፍ ማህበረሰባዊ መዋቅር ገፅታ ከማሳየቱ በተጨማሪ ሃይማኖትና ማህበረሰብ ያላቸውን ግንኙነት ይገልጻል። ሃይማኖት ለአንድ ማህበረሰብ የሚሰጠው አገልግሎት የሰው ልጅ ሁሉ በአንድነት ተስማምቶ ይኖር ዘንድ፣ የተቀናጀ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲኖርና የአንድን ግለሰብ ባህሪ ከተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ለይቶ ለመቆጣጠር ያሚያስችል በመሆኑ እንደመተዳደሪያ ስርአት ያገለግላል ሲል ያስረዳል።

በአጠቃላይ የአንድ ማህበረሰብ ወይም ተቋም መዋቅር የግለሰቦችን የእርስ በእርስ ግንኙነት፣ ሰዎች በሚገኙበት ተቋም ውስጥ ያላቸውን ቦታ እና ድርሻ ወይም ሚና የሚመለከት ሲሆን መዋቅሩ የተመሰረተበትን ሰንሰለትም የሚያመለክት ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተቋም አሁን ያለውን ገፅታ ይዛ ሥርዓቶችንና አምልኮዎችን እስከ ዛሬ ድረስ ለማከናወን የበቃችው ቀጣይነት ወይም ተደጋጋሚነት ባለው ሂደት ካህናት በሚያከናውኑት ተግባር ነው። ካህናት የተለያዩ ተግባራትን ለመፈፀም ይችሉ ዘንድ የሚኖራቸው ማዕረግ ወይም ስልጣን ወሳኝነት አለው። ካህናቱ የሚያከናውኑት ተግባር በዋናነት ሥርዓተ አምልኮና ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ሲሆኑ ከእነዚህ ጋር ማህበረሰብን የመቆጣጠርና የመግራት ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል። የስልጣን ተዋረዱ አሰዳደር ወይም አቀነጃጀት ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የአገልግሎትን ተግባር መሰረት ባደረገ መልኩ የተቀመጠ ነው።የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተቋም ለመመስረትና ቀጣይነት ያለው ስርአተ አምልኮ ይፈጸም ዘንድ በውስጧ ምትይዛቸው ባለማእረግ ሰዎች ሰባት ደረጃዎች አላቸው። እነሱም ከዝቅተኛ ተነስተን ወደ ከፍተኛ የማዕረግ አይነቶች ስንሄድ አፃዌ ኆኅት ⇨ መዘምር ⇨ አናጎንስጢስ ⇨ ንፍቅ ዲያቆን ⇨ ዲያቆን ⇨ ቄስ እና ⇨ ኤጲስ ቆጶስ ናቸው።

# ምዕራፍ አራት

## 4. የንድፈ ሐሳባዊ ዳራዎች ትንታኔ

### 4.1 ወግ ማዕረግ (Rite of Passage)

ማዕረግ የአንድን ግለሰብ ሥልጣን፣ በሥራ ደረጃው ያለበትን ቦታ የሚያመለክት ሲሆን ሌሎች ሰዎችም የግለሰቡን ማዕረግ በማየት ምን ያህል ክብር እንዳለው መረዳት የሚችሉበት ስያሜ ነው፡፡ ማዕረግ ለሚለው ቃል ደስታ ተክለወልድ (1962፡954) "በህብት በሹመት በመንፈሳዊ ስራ የወጣኒ፣የማዕከላዊ የፍፁም ደረጃና ክብር" የሚል ፍቺ ያቀረቡ ሲሆን የሹመትን ፍቺ ደግሞ ክብር፣ ማዕረግ፣ መብት፣የበላይነት በማለት ገልፀዋል፡፡ ኃየሉም (1995፡109) ሹመት የሚለው ቃል መመረጥ፣ መለየትን የሚያመለክት ሲሆን የክህነት ሹመት ደግሞ በውስጡ ሥልጣን ያለበት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ማዕረግ የአንድ ግለሰብ ያለፈበትን ደረጃ ወይም ያለበትን ቦታና ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ አንድ ግለሰብ ለአንድ የተወሰነ ስራ ታጭቶ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ለዚያ ሥራ ብቁ ሆኖ መመረጡን ለማሳየት ሥርዓት ወይም ክብረ በአል ይዘጋጅለታል፡፡ ያ ሥርዓት ያንን ግለሰብ ከነበረበት ህይወት ወይም የስራ ድርሻ ወደተሻለው ወይም ከፍ ወዳለው መሸጋገሩን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የሽግግር ሥርዓቱ ተፈፅሞ ፤ ለትልቅ ዓላማና ተግባር ታጭቶ ግለሰቡ በተለየ ሥርዓት ወደ ቀጣዩ ክፍል ሲራመድ "ለወግ ማዕረግ በቃ" ይባላል፡፡

ለማዕረግ መብቃት እንደማህበረሰባችን አመለካከት ከአንድ ቦታ ከፍ ወዳለ ሌላ ቦታ የሚሸጋገሩበት ፣የቀደመውን የአኗኗርም ሆነ የአስተሳሰብ ፍልስፍና ቀይሮ ወይም አሻሽሎ በአዲስ አቅጣጫ የሚጓበዙበት፣ ቀደም ከነበረው ኃላፊነት ወደ ተሻለው የተጠያቂነት ደረጃ የሚደርሱበት ወይም ከፍ ያለ የስራ ድርሻን የሚወጡበት እንዲሁም የማስልጠን፣የማዘዝና የመምራት ገጽታ የሚታይበት ነው፡፡

ማርታና ማርቲን (2005:17) እንደሚሉት ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ አንዱ የሆነው ሀገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ በጋራ የሚያከናውኗቸውን ልማዳዊ ድርጊቶች የሚገልፅ ነው፡፡ እነዚህ ልማዳዊ ድርጊቶች በማህበረሰቡ ዘንድ የነበሩ እና ለወደፊትም የሚቀጥሉ በልማድ የሚከወኑ የአኗኗር መንገዶች እና የጋራ ቅርሶች ናቸው፡፡

ሀገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ ከአዕምሮው አንቅቶ የሚፈጥረው እና ለትውልድ በክዋኔ ወይም በድርጊት የሚያስተላልፈው ሲሆን በውስጡ፣ ሀገረሰባዊ እምነት (folk religion or belief)፣ ሀገረሰባዊ መድኃኒት (fold medicine)፣ ክብረ በዓል እና ፌስቲቫል (festival and celebrations)፣ ጨዋታዎችና መዝናኛዎች (game and reactions) እንዲሁም የተለያዩ ሥርዓቶችን የያዘ ነው በማለት ዶርሰን (1972፡159-217) ፊቃደ (1991 13-14)ገልጸዋል።

ወግ ማዕረግ (rite of passage) አንድ ግለሰብ በዘመኑ የሚያልፍባቸውን ተከታታይ የህይወት ሂደቶች ወይም ሽግግሮች የሚያመለክት በመሆኑ ከሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተት ነው። እነዚህ ወግ ማዕረግ የተባሉ እና የሰው ልጅ ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ያሉ የህይወት እርከኖች ልደት፣ ክርስትና፣ ግርዘት፣ ጋብቻ፣ አባትነትና እናትነት፣ ሹመት (ለትልቅ ሥራ መታጨት፣ አስተዳዳሪነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ መራቂነት፣ አስታራቂነት)፣ ጡረታ፣ ሞት ናቸው። በእነዚህ የወግ ማዕረግ አይነቶች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ሌሎች ማዕረጎች ያሉ ሲሆን እነሱም ዋና ዋና የወግ ማዕረግ አይነቶችን ሂደት አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው።

የተለያዩ ማህበረሰቦች በህብረት መኖር ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ይህ አይነት ሽግግር ሲገጥማቸው ወይም ለእነዚህ የወግ ማዕረግ አይነቶች ሲበቁ የሚፈፅሟቸው የተለያዩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ስርዓተ ክዋኔዎች አሉ። በዚህም በስርዓተ ክዋኔ ወቅት አራቱ የፎክሎር ዘርፎች ተግባራዊ የሚሆኑበት አጋጣሚ በእጅጉ ሰፊ ነው። በመሆኑም የአንድ ማህበረሰብ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ ዕውቀት፣ ፍልስፍና በአጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤ እንዲሁም ባህላዊ እና መንፈሳዊ እሴት ይገለፅበታል። የሰው ልጅ ህይወት ተከታታይነት ባላቸው ሽግግሮች ውስጥ ያልፋል እንጂ ሁልጊዜ በአንድ የህይወት ዑደት ውስጥ ብቻ አይሽከረከርም ። እነዚህ ሽግግሮች ከአንድ የእድሜ እርከን ወደ ሌላው የእድሜ እርከን ወይም ከአንድ ማህበራዊ ቦታ ወደ ሌላው የሚያስተላልፉ ናቸው። ጌኔፕ በወግ ማዕረግ ውስጥ የሚካተቱ የተለያዩ ገጽታዎችን ዘርዝሮ ከእነዚህም ውስጥ ሹመት (advancement to a higher class) አንዱ መሆኑን የሚከተለውን ሀሳብ በመግለፅ ያስረዳል።

> *Transition from group to group and from one social situation to the next one looked on as implicit in the very fact of existence, so that a man's life comes to be made up of a beginnings: birth, social puberty, marriage, father hood, advancement to a higher class, occupational specialization, and death for every one of these events there are ceremonies whose essential purpose is to enable the*

*individual to pass from one defined position to another which is equally well defined (1960:3)*

ወግ ማዕረግ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የአንድን ግለሰብ የዕድሜ ልክ ገፅታ የሚያመጣውን ለውጥ እና ሰዎች በአኗኗር ዘይቤያቸው ውስጥ ያሉበትን ደረጃ ወይም ሽግግሮች የሚያመለክት ነው። የወግ ማእረግን ገጽታዎች የሚያሳዩ ሁኔታዎች በሶስት ደረጃዎች ተከፍለው ይታያሉ። ቫን ጌኔፕ (1960፣11) እነዚህን ደረጃዎች መለየት /separation/ ሽግግር /transition/ እና መመለስ /reincorporation/ በማለት የገለፃቸው ሲሆን እያንዳንዳቸው የሰው ልጅ ለወግ ማእረግ ለመብቃት የሚያልፉባቸውን የህይወት ገፅታዎች ደረጃ በደረጃ የሚያሳዩ ናቸው።

ለአንድ ታላቅ ስራ መታጨት (ሹመት) እንዲሁም የነበሩበትን አንድ የህይወት ገጽታ ተሻግሮ ወደ ሌላው ማለፍና ከቀደመው የተለየ ህይወት መምራት ጌኔፕ (1960:11) ሽግግር (transition rites) በማለት የገለፀው ሲሆን ሽግግሩን አስመልክቶ የሚፈጸሙ ስርአቶች ‹‹Initiation rituals›› በመባል ይጠራሉ።

ሲምስ እና ስቴፈን (2005፡ 110-119) የሥርዓት አይነቶች ወግ ማዕረግ (rite of passage)፣ የስም አወጣጥ (naming rituals)፣ ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት ዕድሜ ሽግግር (coming-of-age) እና ከነበሩበት ማህበራዊ ቦታ ወደ ሌላው ወይም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለመሸጋገር የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች (Initiation) መሆናቸውን ገልፀዋል። እነዚህ የሥርዓት አይነቶች ከአንዱ የህይወት እርከን ወደ ሌላው የሚደረገውን ሽግግር የሚጠቁሙ ናቸው። ስለ "initation rite" ጌኔፕ (1960) እና ሲምስ (2005) ሲገልጹ ከአንድ ማህበረሰባዊ ቦታ ወደ ሌላው ሽግግር ሲደረግ የሚፈጸሙ ዝግጅቶችን ወይም ድርጊቶችን የሚመለከት ነው። ከዚህ በመነሳት በሥልጣነ ክህነት ተዋረድ አንድ ግለሰብ የዲቁናን ስልጣን ሲቀበል ፣ ከዲቁና ሥልጣን ወደ ቅስና፣ከቅስና ሥልጣን ደግሞ ወደ ኤጲስ ቆጶስና ስልጣን ለመሻገር የሚደረጉ ስርአቶች */initation rites/* ናቸው።

እንደ ዶርሰን (1972:3) ገለጻ ደግሞ ማንኛውም ሀገረሰባዊ ልማድ በማህበረሰቡ ዘንድ ተፈፃሚነት ሲያገኝ እና መከወን ሲችል ritual (ሥርዓተ በዓል) ይባላል ። ከሃይማኖት አንፃር የሚከበሩት ስርዓቶች የአምልኮ ስርዓትን የሚመለከቱ ሲሆን እነዚህ ሥርዓተ አምልኮዎች ጥንት ከነበረው የቤተክርስቲያን ስርዓት፣ የክርስትና እምነት መመሪያ (ህግ) ከነበሩትና ከተለያዩ ስብከቶች ላይ የተለያዩ ትርጓሜዎችን በመስጠት እና ሀገር በቀል በሆኑ

የተለያዩ እምነቶች፣ ግንዛቤዎች ወይም አመለካከቶች ላይ ተመስርተው እንደሚከበሩ ያስረዳል (1972፡2-4)፡፡

"Initiation" እንደ ሲምስ እና ስቴፈን አገላለጽ በግልፅ እና በይፋ የሚፈፀሙ ስርዓተ ክዋኔዎች ያሉት ሲሆን የአንድ ቡድን አባላት የሚያደርጉትን የሽግግር ደረጃ ተመርኩዞ በስርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ ቅደም ተከተላዊ ቅንጅቶችን የሚመለከት እንደሆነ የሚከተለውን በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

> *Initiation rituals express a person's entrance in to membership in a group. Group with initiation rituals are usually well defined, with clear hierarchies and structures, perhaps even laws or rules of conducts. Some initiation ceremonies and rituals are private and secret. Others are open to the public (2005:119).*

ከኤጲስ ቆጶስ የስልጣን አሰጣጥ ስርአት በስተቀር ሌሎቹ ሥርዓቶች ለማንኛውም ህዝብ ግልፅና ይፋ በሆነ አውድ የሚከወኑ ሳይሆኑ ግላዊና ምስጢራዊ ፣ እንዲሁም በተወሰነ ወይም በተመረጠ መቼት ላይ የሚከወኑ ናቸው፡፡ ይህም ከላይ የቀረበውን የማርታና የማርቲንን ገለፃ የሚያረጋግጥ የሥርዓተ ክዋኔ ዓይነት ነው፡፡

አንድ ስርዓት የደመቀ እና ከፍ ያለ የክዋኔ አውድ አልያም ከዚህ ባነሰ መልኩ ዝቅ ያለ (high and low-context) የክዋኔ አውድ ሊኖረው ይችላል፡፡ የ "Initiation" ስርዓት ከፍ ያለ የክዋኔ አውድ ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም በከፍተኛ የክዋኔ ስርዓተ አውድ ውስጥ የጊዜ ሰሌዳ ወጥቶ ፣በተቀናጀ መልኩ ልምድ ያላቸውና ስርዓተ ክዋኔውን የሚመሩ ግለሰቦች የሚሳተፉበት፣ ከዋኙና ተሳታፊዎቹ የስርአተ ክዋኔውን መመርያ በመከተል ስርአቱን የሚፈጽሙበትና አንድ ከዋኝ ክዋኔውን ለመምራት መፅሐፍ በማንበብም ሆነ ከዚህ ቀደም በልምድ የሚያውቃቸውን ንግግሮች ሲናገር የሚታይበት ነው፡፡ ከተሳታፊዎቹ አንፃር ደግሞ የተለያዩ መዝሙሮችንም ሆነ ዘፈኖች እንዲሁም የተለያዩ ድርጊቶችን የሚከውኑበት ነው፡፡ ጎልድስቲን እነዚህን ጉዳዮች ‹‹የአውድ አይነቶች›› በማለት በሶስት ከፍሏቸዋል፡፡እነሱም *highly formal context, formal context,* እና *informal context* ናቸው፡፡የእነዚህ ጽንሰሃሳብ ከላይ የተገለጸውን ማብራሪያ የሚጋራ ነው፡፡

ከሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ውስጥ በ" initiation ritual " እይታ መሰረት ከፍተኛ የክዋኔ አውድ ያለው የጵጵስና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ነው፡፡ ይህ

ሥርዓተ ክዋኔ የሚፈፀመው የተለያዩ ቀሳውስት፣ዲያቆናት፣ ምእመናን፣የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በተገኙበት ሲሆን ሥርዓቱን ለመፈፀም የተለያዩ ፀሎቶች፣መዝሙሮች፣ ምስጋናዎች ይቀርባሉ። እነዚህ ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ክዋኔውን ከቅስና እና ከዲቁና ሥርዓት የበለጠ እንዲደምቅ የሚያደርጉ በመሆናቸው ስርአቱ ከፍ ያለ የክዋኔ አውድ /high context/ እንዲኖረው የሚያስችሉ ገፅታዎች ናቸው።

## 4.2 ሥርዓተ ክዋኔ (Performance)

### 4.2.1 የሥርዓት ምንነት

ሥርዓት "ሠርዐ" ከሚል የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም የህግና የትዕዛዝ መጠበቂያ ደንብ፣ መመሪያ፣ ገደብ፣ አሠራር፣ መርሃ ግብር መሆኑን ደስታ ተክለወልድ (1962፡1094)፣ አክሊሉ (1993፡37)፣ ክንፈገብርኤልና ጌታቸው (2002፡3) ገልፀዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ (30፡27 )፤ 1ቆሮ (14፡40)እና ገላ (1፡14)ያሉትን ጥቅሶች መሰረት በማድረግ የስርአትን ምንነት "የመንግስት፣ የቤተክርስቲያን፣ የህዝብ ወይም የአንድ ድርጅት የአስተዳደር ፣ የአመራር ወይም የአካሄድ ሕግ ፣ደንብ፣ብያኔ "በማለት ይገልጻል።

ሥርዓት "ritual" የሚለውን ቃል የሚተካ ሲሆን ብዙዎቹ ተመራማሪዎች የአንድን ነገር ቅደም ተከተላዊ ሂደት መመሪያ የሚያሳይ መሆኑን አመልክተዋል። የሥርዓት ህልውናው የተመሠረተው በክዋኔ (performance) ላይ መሆኑን "If there is no performance, there is no ritual" በማለት ራፖርት (1992፡250) አስረድቷል። እንዲሁም የሥርዓት ሙያ (ተግባር) አንድ ነገር ከሌላው ጋር ያለውን ተያያዥነት እና ግንኙነት የሚያሳይ በርካታ ገጽታዎች ያሉት፣ የነገሮችን ቅንጅት ወይም መዋቅር የሚያሳይ ቅርጽ መሆኑንም ጠቁሟል።ስርአት አንድን እምነት መሰረት ያደረጉ ሚቶች፣አፈታሪኮችና ነገረ ተፈጥሮዎች የሚገለጹበት ነው።

በርካታ የፎክሎር ተመራማሪዎች በትኩረት ከሚመለከቷቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ፎክሎር የሚከወኑባቸውን ሥርዓቶች መመርመር ነው። ምክንያቱም ሥርዓት የትውፊት /የባህል/ መገለጫዎች አንዱ የሆነና ትእምርታዊ ፋይዳ ባላቸው በልማዳዊ ድርጊቶች፣ በድግግሞሽ፣ በንግግር፣ በገለጻ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍና በዚህም የማህበሰቡን አጠቃላይ

ገጽታ ለማሳየት የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ ሲምስ እና ስቴፈን ይህንን በተመለከተ Rituals are performances that are repeated, patterned, and frequently include ceremonial actions that incorporate symbols, actions and repetition (2005:95).ብለዋል፡፡

### 4.2.2 ሃይማኖታዊ ሥርዓት

ሃይማኖት መንፈሳዊ እና አምልኮታዊ ስርአቶችን የሚፈጽም ፣የእምነት ስርአት ያለው፣የስነምግባር ደንቦችንና የሰዎችን የህይወት ፍልስፍና የያዘ ማህበራዊ ተቋም መጠርያ መሆኑን ቴዎድሮስ(2001፡254) ገልጻል፡፡ ሃይማኖታዊ ስርአት ሰዎች ንጽህናን፣ ፈውስን ፣የአእምሮ እረፍትን፣የነፍስ ድህነትን በአጠቃላይ መንፈሳዊ እና ስጋዊ ጥቅሞችን የሚያገኙበት ደንብ ነው፡፡

ራድክሊፍ ብራውን ሃይማኖታዊ ስርአት የአንድ ማህበረሰብ ማንነት የሚገለጽበት እና ማህበረሰባዊነትን የሚያጸና መሆኑን ሲገልጽ እንደሚከተለው ነው፡፡

> *Religious ritual is an expression of the unity of society and that its function is to 're-creat' the society or the social order by reaffirming and strengthening the sentiments on which the social solidarity and therefore the social order itself depend.*(1952፡165)

ከብራውን ገለጻ መረዳት እንደምንችለው ሃይማኖት ማህበረሰብን ለማደራጀት፣እምነታቸውን ለማጽናት ፣አንድነታቸውን ለማጠንከር፣በማህበረሰብ መካከል ያለውን የወዳጅነት ስሜት ለማጥበቅ የሚያገለግል መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሁለት አይነት የስርአት አፈጻጸም ገጽታዎች አሉ፡፡ እነሱም ግልጽ( ለህዝብ ይፋ የሆኑ) እና ምስጢራዊ የሆኑ ናቸው፡፡

ግልጽ ስርአቶች ምእመናን የሚሳተፉባቸው ወይም በነጻነት የሚመለከቷቸው ሲሆኑ ለአብነት ስርአተ ጥምቀት ፣ተክሊል፣ ቅዳሴ ይጠቀሳሉ፡፡ምስጢር የሆኑት ደግሞ ማስታወቂያ ሳይነገር ፣ሰው ሳይሰማ በስርአቱ ፈጻሚዎች ዘንድ ብቻ የሚከናወን ነው፡፡ የስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ ሁለቱንም አጣምሮ የያዘ ነው ምክንያቱም የጵጵስና ስርአት ቀኑ ተወስኖ

ለምእመናን ተነግሮ እንግዶች እና የመንግስት ባለስልጣናት ባሉበት የሚሰጥ ሲሆን ዲቁና እና ቅስና ግን ዲያቆናት እና ጳጳሳት ብቻ ሆነው የሚፈጽሙት ስርአት ነው።

በማህበረሰቡ ዘንድ ተዘውትረው የሚፈጸሙ ክርስቲያናዊ ስርአቶች መመርያን እና ደንብን የተከተሉ ናቸው።እነሱም መስቀልን እና ቤተክርስቲያንን መሳለም፣ማተብ በአንገት ላይ ማሰር፣ከስራ በፊትና በኋላ ፊትን በትእምርተ መስቀል ማማተብ፣ ካህናት በአዘቦት ቀን ከሌላው ማህበረሰብ የሚለያቸውን ልብሰ ተክህኖ መልበስ፣ነጠላ በመስቀለኛ ቅርፅ አጣፍቶ መልበስ፣ ጫማ አውልቆ ወደቤተ መቅደስ መግባት፣በስርአተ አምልኮ ጊዜ የተፈቀዱ ንዋያተ ቅድሳትን ፣ ያሬዳዊ መዝሙሮችና የመዝሙር መሳሪያዎችን መጠቀምና ሌሎችም ድርጊቶች ሲሆኑ እነዚህ የጥንት አባቶችን ሥርዓት የተከተሉና አገርኛ እውቀትን የሚያንፀባርቁ ናቸው።መልአኩ (1993፡39-40) ሃይማኖታዊ ሥርዓት እንዴት እንደተጀመረ ሲገልፅ

> *ልዑል እግዚአብሔር ለቤተ እስራኤል የአምልኮት መግለጫ በሰጣቸው በምስክር ጽላቱ ላይ ዐሠርቱ ቃላትን (ህጎችን) ጽፎ በሙሴ አማካይነት በሰጣቸው ጊዜ የቤተ መቅደሱን ወይም የድንኳኑን ሥርዓት፣ በውስጡ የሚያገለግሉትን የካህናቱን የአሻሻምና የአለባበስ፣ የአገልግሎት ወዘተ ሥርዓት እንዲሁም በአጠቃላይ የአምልኮቱን፣ የአምላኪዎቹን ሥርዓትና የተመላኪውንም ፈቃድ ጨምሮ አስረድቷቸዋል (1993፡40)*

በማለት በኦሪት ዘጸአት 25፡8 ላይ ያለውን በመጥቀስ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ወይም የሚዘጋጅ እንደሆነ አስረድቷል።

ከባህላዊ ሥርዓቶች አንፃር የሃይማኖታዊ ስርዓት አገልግሎት የተለያዩ ጥቅሞችን ያስገኛል። ኃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ለማስጠበቅ፣በጥሩ ሥነ ምግባር ለማነጽ፣ፈውስን ለማነስገኘት፣የመንፈስ ንፅህናን ለመጠበቅና ለመቀደስ እንዲሁም የተለያዩ መልካም ገፅታዎችን በማህበረሰቡ ለማስረፅ ይረዳል። ይህንን በተመለከተ ስቼልበርግ

> *Religious rituals are designed for no single purpose, serve multiple and sometimes widely disparate purposes. Nevertheless, they often consist of practices intended to inculcate, reinforce or transform specific beliefs and habits, and thereby to shape human conduct in deliberate ways (2004:115)*

በማለት ይገልጻል።

### 4.2.3 የሥርዓት አስፈላጊነት

ስርዓቶች የተለያዩ ፋይዳዎችን ስለሚያስገኙ ማህበረሰቦች በእምነታቸው፣አመለካከታቸውና እውቀታቸው ላይ ተመስርተው ስርአቶችን ያበጃሉ፡፡ ስርአቶች ከሚሰጡት ፋይዳዎች መካከል ከዝቅተኛ የማህበረሰብ አባልነት ወደ ተሻለው፣ ከዝቅተኛ የሥራ ቦታ ወይም ከነበራቸው ክብርና ማዕረግ ከፍ ወዳለው እና ለታላቅ ስልጣን እና የሥራ ኃላፊነት ማድረስ አንዱ መሆኑን ሲምስ እና ስቴፈን (2005፡100) ገልጸዋል፡፡

የተለያዩ ማህበረሰቦች የአንድን የፎክሎር ገጽታ ሥርዓት ሲፈፅሙ ለሥርዓቱ መፈፀም ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች አሏቸው፡፡ ሥርዓቶችን ሲያበጁ እንደሚኖሩበት ርዕዮተ አለም ፍልስፍና የተለያዩ ገጽታዎችን በማሳየት አጠቃላይ የማህበረሰቡን ህይወት አመለካከት፣ ዕውቀትና ልዩ ልዩ ጠባዮች ያሳያሉ፡፡

ራፖርት (1992፡252) የሥርዓት አስፈላጊነት ሁለት ገጽታዎችን ወይም መልዕክቶችን ለማስተላለፍ እንደሚረዳ ይገልፃል፡፡ የመጀመሪያው በማህበረሰቡ ዘንድ የማይለወጡ፣ የማይቀየሩ (invariant) የተለያዩ ቀኖናዎችን፣ ህጎችን፣ደንቦችን መመሪያዎችን የአቋም ደረጃዎችን ለማስገንዘብ ሲሆን ሁለተኛው ከዚህ በተቃራኒ በማህበረሰቡ ዘንድ ሊሻሻሉ የሚችሉ (የሚለወጡ) (variant) የሆኑ የተለያዩ ህጎችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን ለማመልከት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ የፎክሎር ተለዋዋጭነት ባህሪው የሚታይበት ነው፡፡

ታደሰ (1999፡7)ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው የጥናት ጽሁፍ ላይ ሬይን (1976፡78) በመጥቀስ ሥርዓት በሽታን ለመፈወስ፣ ዘርን ለማብዛት፣ ጠላትን ድል ለመንሳት፣ የሰዎችን ማህበራዊ ደረጃ ለመለወጥ፣ ሃጥያትን ለማንፃት እና መጪውን ጊዜ ለመተንበይ ይከወናሉ በማለት ሥርዓት የሚሰጠውን ማህበራዊና ግለሰባዊ ፋይዳ አስረድቷል፡፡ የሬይ ሀሳብ ከሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ አንጻር ሲታይ ስርአት የሰዎችን ማህበራዊ ደረጃ መለወጥ የሚለው ብያኔ ካህናት የሚያደርጉትን የሥልጣን ሽግግር ያመለክታል ፡፡

ሥርዓት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሊታዩና ሊዳሰሱ የማይችሉ እምነቶችን አመለካከቶችን አስተሳሰቦችንና እሴቶችን ተጨባጭ በሆነ መልኩ ለማሳየት የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም ሥርዓቱን ለሚያጠና ሰውም ሆነ ለተመልካች ስለሚፈፀመው ስርዓት ምንነት ግንዛቤ በማስጨበጥ የአንድን ማህበረሰብ አጠቃላይ ገጽታ ለማሳየት የሚያስችል መሆኑን ሲምስ

እና ስቴፈን /2005-96/ ገልፀዋል፡፡ከዚህ አንጻር ሥርዓት ለስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርአተ ክዋኔ አስፈላጊነቱን ስንመለከት

- የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት የሚፈፀመው በካህናት ነውና ሥርዓቱን ለመጠበቅ ያስችል ዘንድ ክህነትን በመስጠት መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ማድረግ
- ሥርዓተ ክዋኔው የካህናትን የሥልጣን ደረጃ ለመለወጥ እና በአገልግሎታቸው ምን ምን ተግባሮችን መፈፀም እንደሚገባቸው ለማሳወቅ
- ካህናት ቤተክርስቲያንንና ህዝቡን በፍፁም ልቦናቸው ማገልገል እንጂ ክህነታቸውን ለስጋዊ ጥቅም ማዋል  አንደማይገባቸው ለማሳወቅ
- እስከ ህይወት ፍፃሜአቸው ድረስ በጥሩ ስነ ምግባር ታንፀው ኃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶችን መጠበቅ እንዲችሉ ለማድረግ
- የተለያዩ ማህበረሰቦችንና ግለሰቦችን በማስተማር፣በመቀደስ፣በመፈወስ፣ከበሽታና ከደዌ ከእስራት ከእርኩስ መንፈስ ነፃ የሚያደርግ ኃይልን ለማጐናፀፍ
- የተለያዩ ሰዎችን በነፍስም ሆነ በስጋ መከራ እንዳይገጥማቸው ጥሩውን መንገድ ማሳየት፣መምራት፣የተጣሉትን ማስታረቅ፣ክፉዎችን መገሰፅ፣ከክፉ ሃሳብና መንገድ መመለስ እነዲሁም የኃይማኖታቸውንና የባህላቸውን ቀኖና ተከትለው ለተተኪው ትውልድ አርአያ መሆን ይችሉ ዘንድ የሚያስችላቸውን ፀጋ ለመስጠትና ለመሳሰሉት ጉዳዩች ይጠቅማል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 4.3 ክዋኔ

### 4.3.1 የክዋኔ ምንነት

ክዋኔ ማንኛውም የፎክሎር ገጽታ በቃል እና በድርጊት የሚቀርብበት ወይም የሚንፀባረቅበት ቅጥ (mode) ነው፡፡ የክዋኔን ትርጉም ደስታ ተክለወልድ (1962፡642) “ብጅታ፣ ድርጊት፣ ዝግጅት” በማለት የገለፁ ሲሆን ከዚህ ትርጉም በመነሳት የቃሉ ጽንሰ ሀሳብ የአንድን ነገር አሰራር፣ አፈጣጠር፣ አቀነባበር የሚያመለክት መሆኑን እንረዳለን፡፡

ክዋኔ በአውድ ላይ የተመሠረተ የፎክሎር ማጥኛ መንገድ ነው፡፡ የፎክሎር ገጽታዎችን ለማጥናት ካለው ጉልህ አስተዋጽኦ የተነሳ ከዚህ ቀደም “contextual”, “text” እና“verbal

Art" በመባል ይጠናበት የነበረውን መንገድ በመቀየር ‹‹performance›› የሚል ጽንሰ ሀሳብ እንዲኖር ያስቻለ ነው፡፡

ክዋኔ ባህልን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ፣ ሥርዓቶችና እሴቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ለማስረጽ የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ምሉዕ ትውፊት የሚገለፀው በክዋኔ አማካይነት ነው፡፡ በመሆኑም ባህል ይቀጥል ዘንድ፣ ትውፊቶች፣ እሴቶች፣ ሥርዓቶች፣ ልማዶች፣ ወጎች ሁሉ መከወን አለባቸው፡፡

ካፑቻን (1995፡479) የቃሉን (የክዋኔን) ፅንሰ ሀሳብ ምንነት ስትገልፅ የአንድ ማህበረሰብን ጠባይ አጠቃሎ የያዘና የአነጋገር ዘዴ የሚገለፅበት፣ የተለያዩ ማህበረሰቦች ባህል ሥርዓት የሚስተዋልበት፣ የአንድን ግለሰብም ሆነ ቡድን ማንነት ገልፆ የሚያሳይ ውበት ያለው የሚያስደስትና የሚያዝናና ልማድ ነው በማለት አብራርታለች፡፡

የአንድ ማህበረሰብ ትውፊት ባህላዊ ተቋም (cultural institution) ነው፡፡ትውፊቱ የዘመንን ለውጥ በመቀበል በማህበረሰቡ ውስጥ የሚንፀባረቅ ነው፡፡ ትውፊት ዘመን የሚያመጣቸውን ለውጦች ለመቀበል በቅድሚያ ቅራኔ የሚፈጥር ቢሆንም ከባህሉ፣ ከሰዎች አመለካከት እና ከአኗኗር ዘይቤዎች ጋር በማጣጣም ዘመኑ የደረሰበትን ገጽታ ሊቀበል ይችላል፡፡ የፎክሎርን ገጽታ የሚያንፀባርቅ ትውፊት በድግግሞሽ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ወይም ሲከወን በከዋኙ እና በተሳታፊዎች ዘንድ ያለው የአከዋወን ስልት በፊት ከነበረው የአከዋወን ስልት ጋር አንድ አይሆንም፡፡ አንድን ድርሰት /text/ ሁለት ሰዎች በተመሳሳይ እና ፍፁም አንድ አይነት በሆነ የክዋኔ ስልት እንደማይፈፅሙት ሁሉ በጊዜ፣ በቦታ እና በዘመን የተለያዩ ማህበረሰቦች የተለያዩ የመከወኛ ስልቶች አሏቸው፡፡ ማንኛውም ማህበረሰብ እና ግለሰብ እንደ ዘመኑ የባህል፣ ወግ፣ ልማድ እና ሁኔታ የአከዋወን ብቃታቸው ስለሚለያይ አንድ አይነት የክዋኔ አውድ ሊኖራቸው ይችላል ለማለት ያስቸግራል፡፡

ኬሪን ባርበር (2005፡264) ክዋኔ የተለዋዋጭነት ገጽታ እንዳለው የድርሰትና የክዋኔን ባህርይ በማስረዳት ይገልፃል፡፡ ይኸውም ክዋኔ የአንድን ድርሰት /text/ ህልውና ህይወት የሚዘራበት፣ የድርሰቱን የተለያየ ገጽታ የሚያሳይ የተለዋዋጭነት ባህሪ የሚታይበት በድርሰቱ ውስጥ ያለውን እውነት ገልጦ የሚያሳይ እንጂ እንደ ድርሰቱ በቋሚነት አንድን ገጽታ ብቻ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ይህም የአንድ ድርሰት ክዋኔ በከዋኙ፣ በዘመኑ፣ በጊዜው፣ በቦታውና በተለያዩ ሁኔታዎች አማካይነት ሊለዋወጥ የሚችል መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

4.3.2 የክዋኔ አለባውያን /Elements of Performance/

የክዋኔ ቲዎሪ በዋናነት የሚመለከታቸው:

- ድርጊቱን ማን ፈፀመ? (ከዋኙን)
- ምን ተፈፀመ? (ድርሰቱን)
- ለምን ተፈፀመ? (የክዋኔን ተግባር)
- ድርጊቱ ለማን ቀረበ ወይም ተፈጸመ (ተመልካች)
- ድርጊቱ መቼና የት ተፈጸመ? አውድ( መቼት)
- ድርጊቱ እንዴት ተፈፀመ? (የአከዋወን ስልት) የሚሉትን ጥያቄዎች ነው።የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ የክዋኔን ገጽታዎችና አላባውያን ያመለክታሉ።

የክዋኔ አላባውያን /Elements of Performance/ አንድ ክዋኔ የሚይዛቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች የሚያሳዩ ናቸው። የአለባውያኑ አቀነጃጀት የሚያመለክተው ቅደም ተከተላዊ ሂደትን ሲሆን የእርስ በርስ ተደጋጋፊነታቸው ወይም ተያያዥነታቸው የክዋኔውን ቅርጽ ወይም መዋቅር የሚያሳይ ነው። እነዚህ አላባዊያን ፎክሎርን በአውድ ለማጥናት የሚያስችሉ ነገሮች ሲሆኑ የሚጠናውን ርእሰ ጉዳይ ምንነት ገልፀው የሚያሳዩ ናቸው። ስለሆነም አንድ አጥኚ በፎክሎር ዘውጎች ላይ ጥናት ሲያካሄድ አነዚህን አላባዊያን መሰረት ማድረግ ይኖርበታል።

የክዋኔ አለባውያን አንድ ክዋኔ የሚያጠቃልላቸው ነገሮች ናቸው የሚመለከቱትም ከላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ነው። እንደ ቦውማን አገላለፅ (1975፡299) አላባውያኑ፡

1. መቼት /setting/:- ክዋኔው የተፈፀመበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ሁኔታ... ያሳያል።
2. ህግ፣ ደንብ /rule/:- የክዋኔውን ሥርዓተ ሂደት መመሪያ፣ ትዕዛዝ የሚመለከት ነው።
3. ተሳታፊ /Participant/:- የተሳታፊዎችን ሁኔታ ማለትም በምን መልኩ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ይጠቁማል።
4. ከዋኝ /Performer/፡- የከዋኙን የአከዋወን ስልት ይጠቁማል
5. ተመልካች /Audience/፡- ሥርዓተ ክዋኔውን ይመለከቱ የነበሩ ግለሰቦች ለክዋኔው የነበራቸውን ስሜት እንዴት እንዳንፀባረቁ የሚገልፅ ነው።
6. ድርጊት ቅደም ተከተል /Act sequence/:- ሥርዓተ ክዋኔው የተካሄደበትን የጊዜም ሆነ የአከዋወን ቅደም ተከተል ይመለከታል።

ሌሎች አጥኚዎች እንደገለፁት ክዋኔ ሌሎች አለባውያንን ጭምር እንደሚይዝ ያስረዳሉ፡፡

እነሱም፡-

- ድርሰት /text/ በክዋኔው ወቅት የሚቀርበውን ርእሰ ጉዳይ ያመለክታል
- ፍሬም (framework) (ክዋኔው ተጀምሮ እስኪፈፀም ያለውን ቅርጽ ማለትም በመክፈቻ፣ በመሃል እና በመዝጊያ ላይ ያለው የክዋኔ ሥርዓት)፣
- መልዕክት (message)፣ በሥርዓተ ክዋኔው ወቅት የተላለፈውን አቢይ ጉዳይ የሚመለከት ነው) የተባሉ የክዋኔ አለባውያን የሚገኙ ሲሆን በአጠቃላይ እነዚህ የአንድን ሥርዓት ክዋኔ ገጽታና መዋቅር የሚያሳዩ ናቸው፡፡

### 4.3.3 የክዋኔ መገለጫ ባህርያት

አንድ ማህበረሰብ የሚመራባቸው መርሆች በትውፊት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ህብረተሰቡም የአኗኗር ዘዴው ፎክሎር በያዛቸውና በሚያስተላልፉቸው እሴቶች የሚመራ ነው፡፡ እነዚህም የህብረተሰቡን ባህርያት የሚገልፁ ተብለው የሚቀመጡ ነጥቦች ህጎች፣ ደንቦች፣ ባህላዊ እሴቶች፣ መመሪያዎች፣ የአኗኗር ስልትንና የአስተሳሰብ ደረጃን ያጠቃለሉ ሁሉ ናቸው፡፡ እነዚህ አብይ የአንድ ማህበረሰብ መርሆች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት በመደረግ በመከወንና በመገለፅ ነው፡፡ ክዋኔ በሕግ ወይም በደንብ የተገዛና የተገደበ (rule guvernanc) እና የፊት ለፊት ተሳትፎን (face to face interaction) የሚጠይቅ ነው፡፡

ማንኛውም የፎክሎር ገጽታ በድርጊት ወይም በገለፃ ሲከወን በአውድ (context) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡በመሆኑም በክዋኔው ወቅት የሚፈፀሙት ድርጊቶች ትእምርት (symbolism)እና ትርጉም (Interpritation) ይሰጣቸዋል፡፡ ክዋኔው የተፈፀመበት ዓላማ በክዋኔ ወቅት የነበሩ አጠቃላይ ገፅታዎች የዚያን ማህበረሰብ ሁኔታ የሚያመለክቱ በመሆናቸው የነዚህ ጭምቅ ይዘት የክዋኔውን አላማ ወይም ተግባር /function/ ያመለክታል፡፡

ክዋኔ በህግ የተገዛና የፊት ለፊት ተሳትፎን የሚጠቁሙት ‹‹situation markers›› በመባል የሚጠሩ ናቸው፡፡እነዚህ የተለያዩ አውዳዊ ሁኔታዎችን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎች የመቼትን ዋና ዋና ገጽታዎች የሚያንጸባርቁ (ለምሳሌ ከፍ ያሉ ደረጃዎችን ወይም ቦታዎችን)፣ ቁሶችን፣ ወቅታዊ ክብረበዓሎችንና መንፈሳዊ በዓሎችን በማህበረሰቡ

ውስጥ የሚንፀባረቁ የተለያዩ መስተጋብሮችን (interactions) ፣እንደ ማህበረሰቡ አመለካከት ትርጉም የተሰጣቸውን ጉዳዮች እንዲሁም ክዋኔው ተጀምሮ እስኪፈጸም ያሉ ደንቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡

በባህላዊ ክዋኔዎች (cultural performance) ላይ የክዋኔ ባህሪ በማህበረሰቡ ዘንድ የላቀ (የጎላ) ተሳትፎ ወይም ድርጊያ የሚታይበት ነው፡፡ ባህላዊ ክዋኔ ሰፊ ገጽታን የያዘ በመሆኑም ለክዋኔው ፕሮግራም ይወጣል፤ የፕሮግራሙ መክፈቻና መዝጊያ ጊዜም ይመደባል፡፡ ይህ በመሆኑም ማህበረሰቡፕሮገራሙን ጠብቆ በንቃት የሚከውነው ገጽታ ነው፡፡ ባህላዊ ክዋኔዎች ከሌሎቹ ተለይተው የሚታወቁበት ባህርያቸው የሰዎች በአንድ ላይ ተቀናጅተው መገኘት እና ባህላቸውን የሚያንጸባርቅ የተለያዩ መሳሪያዎችን (ቁሶችን) ይዘው መገኘታቸው ነው፡፡ ይህ አይነቱ ገጽታ ደማቅና ከፍተኛ የክዋኔ ገጽታ ሥርዓት የሚታይበት /heightened occasion/ መሆኑን ቦውማን (1992፡40) ይገልጻል፡፡

### 4.3.4 የክዋኔ ገጽታዎች

1. ድርሰት (text)፣ ጂፍ ቶድ (1995፡433) ድርሰት (text) ንግግሮች፣ መዝሙሮች፣ በስሜት የሚገለፁ የፎክሎር ዘውጎች፣ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶች፣ ማህበረሰቡ ስሜቱን የሚገልፅበት ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ባህሎችን የሚያቀርብ ወይም የሚይዝ ጽሑፍ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁልጊዜ በጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኝ ነው ማለት ሳይሆን በአንድ የክዋኔ ስርአት ላይ የሚቀርብን ጉዳይ ፣ አጠቃላይ የአንድን ፎክሎር ዘውግ የሚያመለክት ነው፡፡

በዚህ የጥናት ጽሁፍ ድርሰት የሚያመለክተው በሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔው የቀረበው የትኛው የፎክሎር ዘርፍ እንደሆነ የሚጠቁም ሲሆን እሱም በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተት ሃይማኖታዊ ሥርዓት መሆኑን ያሳያል፡፡ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ሰዎች ሃይማኖታቸውን የሚያፀኑበት፣ ከኃጢያት የሚፈወሱበት፣ የስጋና የነፍስን ድህነት የሚያገኙበት… በመሆኑ ይህንን ሥርዓት እንደ ባህላቸው ቁሳዊና መንፈሳዊ ሁኔታ፣ ምድራዊውንና ሰማያዊውን አለም የሚተረጉሙበት መንገድ ያበጃሉ፡፡ የሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔውን ሲያበጁ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በመንገርና በመግለፅ ሲሆን በቃል ያለው እየተረሳ ሥርዓቱ እንዳይጎድል ደግሞ በፍትሃ ነገስት፣ በዲስቅሊያ፣ በቀሌምንጦስ ተጽፎ ተቀምጧል፡፡

2. ቴክስቸር (Texture)፡- ቴክስቸር የከዋኙን እና የተሳታፊውን አጠቃላይ ሁኔታና እንቅስቃሴ የሚመለከት ሲሆን በእነዚህ ውስጥ ጽሁፋዊ፣ ሥነልሳናዊ፣ አካላዊ ገጽታዎች ይስተዋሉበታል፡፡ በሥርዓተ ክዋኔው ወቅት የሚቀርበው ቋንቋ፣ ዜማዊ ፣ ድምፀት እና አጠቃላይ የአቀራረቡን ገጽታ፣ የከዋኙ የአቀራረብ ስልት፣ እንዲሁም የተቀባዮቹ ስሜት እንዴት እንደተንፀባረቀ የሚገለፅበት መሆኑን ዳንደስ (1978 ፡ 25-26)፣ ማርታና ማርቲን (2005፡136) ገልጸዋል፡፡ ከዋኙና ተሳታፊው አንድን ድርሰት ሲከውኑ በራሳቸው ዘዴ ስለሆነ ክዋኔውን ለማሳመርም ሆነ ለማድመቅ ብለው ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን ይፈጽማሉ፡፡ስለዚህ ዋናው የክዋኔ ገጽታ ይቀየራል፡፡ በመሆኑም ቴክስቸር በድርሰቱ ላይ ለውጥ የሚያመጡ ናቸው፡፡

3. አውድ (context)፡- ሜሪ ሃፍርድ (1995፡328) context "contecxere" ከሚለው የላቲን ቃል የመነጨ መሆኑን በመግለፅ ትርጉሙም "to weave together, interweave, join together compose", በማለት መሆኑን ገልፃለች፡፡ የአውድን ጽንሰ ሀሳብ ከዚህ ጽሑፍ ስንረዳ የአንድን ነገር የእርስ በርስ ተያያዥነት ወይም ቁርኝት፣ እንደ ድርና ማግ እርስ በርሱ ተጠላልፎ ወይም ተወሳስቦ አንድን ተጨባጭ ነገር ለማመልከት የተቀመጠ ገፅታ መሆኑን ነው፡፡

በፎክሎር ዲሲፕሊን ለመጠናት የሚችሉ ሁሉ በአውድ ላይ የተመሠረተ ጥናት መካሄድ እንዳለበት ጎልድስቲን (1964፡80) ያስረዳል፡፡ የሚያነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች ሰዋዊ የሆኑ እና ከሰው ህልውና ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው ዘርፈ ብዙ አቅጣጫ አለው፡፡ የሰውን ዕውቀት፣ ማንነትና የማህበረሰብን አደረጃጀት አውቆ ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት ለማወቅ ደግሞ በቱባው (በዋናው) ማህበረሰብ ውስጥ ገብቶ ወይም ተቀላቅሎ አውዳዊ ገጽታዎችን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ዳንደስ (1978፡27) አውድ የአንድ ፎክሎራዊ ዘርፍ ርዕሰ ጉዳይ የሚይዘውን ማህበራዊ ሁኔታ የሚመለከት መሆኑን ሲገልፅ ሲምስ እና ስቴፈን (2005፡137) ድርሰትን እና ክዋኔን አቅፎ ወይም ከብቦ የሚይዝ ማንኛውንም ሁኔታ የሚመለከት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ዳንቤን አሞጽ (1993፡209) ዊልያም ባስኮም በ1954 ዓ.ም ያቀረበውን ጽሑፍ በመጥቀስ አንድ አጥኚ በማንኛውም ተግባራዊ ትንታኔ ላይ የአንድን ጉዳይ አገልግሎት ወይም ተግባር ለመተንተን ቢፈለግ የፎክሎርን ማህበራዊ አውድ በመጠቀም ወይም በማወቅ ትንታኔ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

መስጠት እንዳለበት ይገልፃል። አጥኚው በዚህ ውስጥ ሊመለከታቸው የሚገቡት ነገሮችም ጊዜንና ቦታን የክዋኔን ቅርጽ፣ የተራኪዎችን (የከዋኞችን) ማንነት የአድማጮችን ወይም የተሳታፊዎችን ጠቅላላ ሁኔታ፣ የከዋኙና የተሳታፊዎች ግንኙነት፣ ከዋኙና ድርሰቱ ያላቸውን ግንኙነት በክዋኔው ጊዜ የሚታየው ጥበባዊ እንቅስቃሴ ወይም ድራማዊ የሆነ አጠቃቀም የአከዋወን ሂደት፣ የአድማጮች ተሳታፊነት፣ የተለያዩ የባህል ገጽታዎች የሚኖራቸውን ህገረሰባዊ ክፍፍል እንዲሁም የሰዎችን ሥርዓትና አስተሳሰብ መሆናቸውን በዝርዝር አስረድቷል።

አውድ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በ1971 ዓ.ም ከመታየቱ በፊት ቀደምት አጥኚዎች በክዋኔ ወቅት የሚኖሩ የተለያዩ ነገሮችን ያለ ትርጓሜ እንዲሁ ይገልፃሉ እንጂ የእያንዳንዱን የፎክሎር ገጽታ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር በማያያዝ ትርጓሜ ወይም ፍቺ አይሰጡም ነበር። እንደ ቤን አሞጽ ገለፃ አውድ የፎክሎርን ትንተና እና የፎክሎርን ተግባር ወይም አገልግሎት ለማሳየት የሚያስችል አንድ የክዋኔ ገጽታ ነው። የፎክሎር ክዋኔ በአውድ ሲጠና የይዘት ገለፃን፣ ትንታኔን፣ ቅርጽንና መዋቅርን፣ ድርጊትን ለማሳየት ያስችላል። በመሆኑም አውዳዊ ትንተና ፎክሎርን ይተረጉማል እንጂ አይገልፅም። በፎክሎር ጥናት ድርሰቱን (text) ብቻ መመልከት እርባና ቢስ ይሆናል። ከአውድ ውጪ የሆነ ክዋኔ የለም። በመሆኑም ትክክለኛው አካሄድ ፎክሎርን በማህበረሰቡ ውስጥ በመመልከት መመርመር የተፈለገውን ጉዳይ ከባህሉ አውድ፣ ከማህበረሰቡ አውድ እና ከሁኔታ አውድ አንፃር መመልከት ወይም እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ማጥናት ነው። አሞጽ (2005፡210)።

በአንድ ክዋኔ ውስጥ የፎክሎር ዘውጎች ሲገለፁ አንድን ርዕሰ ጉዳይ ብቻ የሚያመለክቱ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም። በማንኛውም የክዋኔ ድርሰት (text) የሚተላለፈው በጽሑፍ፣ በታሪክ ወይም በባህላዊ አውድ ውስጥ ነው። በእነዚህ ውስጥ ሲተላለፉ በየጊዜው እንደዘመኑ፣ እንደማህበረሰቡ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ ርዕዮተ አለም፣ የአኗኗር ዘይቤ የነበረው እንዳለ ሆኖ አዲስ ትርጉምን ሊይዙ ወይም ሊጨምሩ ይችላሉ።

ዳን ቤን አሞጽ የድርሰት (text) ፍቺ ሊገለፅ ወይም ሊሰጥ የሚገባው በአውድ ውስጥ መሆኑን "The meaning of a text is its meaning on context" (2005፡210) በማለት ይገልፃል። ይህም ድርሰት (text) በአውድ ሲጠና ወይም ሲመረመር አውዱ የሚተላለፈውን መልዕክት የተለየ (unique) ፍቺ እንዲኖረው ያደርጋል። እነዚህ ሁሉ ሀሳቦች "አውድ ፎክሎርን የመተርጎሚያ መንገድ ነው" ወደሚል ማጠቃለያ የሚወስዱ ናቸው።

በውማን (1990፡68) እና ዳን ቤን አሞጽ (1993፡215) ፎክሎርን የመተርጎሚያ መንገዶች ማህበራዊ አውድ (context of social) እና የሁኔታ አውድ (context of situation) መሆናቸውን ማሊኖዊስኪን (1935 [1965]፡118) በመጥቀስ ጠቁመዋል፡፡ ማህበራዊ አውድ የሚገለፅባቸው መንገዶች ባህላዊ ሁኔታዎችን የሚያንፀባቁ በተለያዩ ግለሰቦች መካከል የጋራ የሆነ፣ የራሳችን ነው የሚሉት የሚያስተሳስሯቸው ነገሮች ናቸው፡፡

ማህበራዊ አውዶች የቋንቋ፣የእውቀት፣የእሴት እና የእምነት ሥርዓት፣የአስተሳሰብ ደረጃ፣የፍላጐት መጠን፣ የአለባበስ፣የአመጋገብ፣ በጥቅሉ የአንድ አይነት የታሪክ ባለቤትነት የሚገለፅባቸው ናቸው፡፡

የሁኔታ አውድ የከዋኙን እድሜ፣ፆታ፣ማህበራዊ ደረጃ፣ስልት፣አከዋዋን፣የክዋኔ ቦታና ጊዜ እና ሌሎች ከማህበራዊ አውድ ባነሰ ወይም በጠበበ መልኩ የተለዩ ገፅታዎች መሠረት በማድረግ ትእምርታዊ ፍቺዎችን የምንመለከትበት የአውድ ዓይነት ነው፡፡

ማህበራዊ አውድ እና የሁኔታ አውድ ዋና ዋና ፎክሎርን የመተርጎሚያ መንገዶች ናቸው፡፡ በውስጣቸው ስድስት ፍሬ ነገሮችን (elements) ይዘዋል፡፡

1. የፍቺ አውድ (context of meaning) ትእምርታዊ ፍቺዎችን፣የእምነት ስርዓት ተምሳሌቶችን፣የእሴት ሥርዓቶችን በአጠቃላይ በአንድ ክዋኔ ወቅት ያሉ ሁኔታዎችንንና ምልክት የቆመለትን አንድ ተምሳሌታዊ ፍቺ የሚመለከት ነው፡፡
2. ተቋማዊ አውድ (institutional context) ባህላዊና መንፈሳዊ ተቋማትን በተመለከተ የሚመሩበትን ህጐች፣የተቋም አመሰራረት ከየት መጣነት፣በተለያዩ ህጐች እንዴት እንደሚመሩ፣ማህበረሰቡ ለዚያ ህግ ምን ዓይነት ትርጉም እንደሚሰጠው የሚመለከት ነው፡፡ አንድ ማህበረሰብ ከሌላው የሚለይበት አንዱ የዕምነት ሥርዓት ነው፡፡ የዕምነት ሥርዓት እየተከወነ የሚፀናው በእሴቶቹ ሲሆን እነዚህ እሴቶችም ህጎችና ደንቦች አሏቸው፡፡ እነዚህ ህጎችና ደንቦች አንድም ከመለኮት (super natural) የሚገኙ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ በልምድና በተሞክሮ ማህበረሰቡ አምኖ የሚያበጃቸው ናቸው፡፡ ጥንት የነበሩ እሴቶች ለአሁን ወይም ለሚቀጥለው ዘመን የሚተላለፉት በትውፊት ነው፡፡ መንፈሳዊ ተቋሞች ከስነመለኮት፣ ከሀይማኖት፣ ከዕምነት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ መንፈሳዊ የሆኑ የአስተዳደራዊ ተቋማት ርዕዮተ አለሙን የሚተረጉሙበት አቅጣጫ እንደ ሃይማኖታቸው ህግና ደንብ መሠረት ነው፡፡

3. የግንኙነት ሥርዓት አውድ (context of communicative system) አንድ ማህበረሰብ ተለይቶ የሚገለፅበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህም የአንድን ማህበረሰብ ወይም ተቋም መሪ ከዚያም በስሩ ያሉት ሌሎች አስተዳዳሪዎች፣ቀጥሎም በእድሜ ደረጃ ያሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች ያላቸውን የርስ በርስ ግንኙት ያመለክታል፡፡ ከግንኙነታቸው ባሻገር አንድ ቡድን ከሌላው የሚለይበትን ገፅታ ለምሳሌ በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ መሪ ከሌሎች የተመረጠበትና የተለየተበት ምክንያት የአኗኗር፣የአለባበስ፣የአመጋገብ ሥርዓተ ደንቡን የሚያመክት ነው፡፡

4. ማህበረሰብ የተመሰረተበት የኢኮኖሚ መሠረት (social base) አንድ ማህበረሰብ የሚተዳደርበትን የኢኮኖሚ መሰረት እንዴት መረጠ? ከብት በማርባት፣መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት፣እህል በመዝራት፣ አሳ በማጥመድ ወዘተ... የሚሉ መተዳደሪያ ደንቦችን ከየት እንደደነገጉ የሚያመለክት ነው፡፡

5. ሁኔታ አውድ (context of situation)፡ ባህል አቅፎ ከሚይዛቸው የማህበረሰብ መገለጫዎች ውስጥ የሚወጡ ውሱን ገጽታዎች መሆናቸውን አብራርቷል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ አውድን የማጥኛ መንገዶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሥልጣነ ክህነትን አጠቃላይ ገጽታ ለማመልከት የሚውሉ መሆናቸው በስርዓተ ክዋኔው የፍቺ አውድን በተመለከተ ልዩ ልዩ ገፅታዎች ትእምርታዊ ፋይዳቸው የተገለፀበት፣በተቋማዊ አውድ የካህናትን የሥልጣን ተዋረድ በመመልከት የቤተክርስቲያንን ሥርዓት እንዴት እንደሚፈፅሙ የታየበት፣በግንኙነት ሥርዓት አውድ ዲያቆን ከቄስ፣ ቄስ ከኤጲስ ቆጶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና እነዚህም ከሌሎቹ ተለይተው የሚገለፁበት ሁኔታ፣የተጠቆመበት እንዲሁም ማህበረሰብ የተመሰረተበት የኢኮኖሚ መሰረትን በተመለከተ ካህናት የሚተዳደሩበትን መሰረት የመረጡበት ምክንያት ተጠቁሞበታል፡፡

### 4.3.5 ትእምርት እና ትርጉም

ክሊፎርድ ጊርቲዝ ስለ ትርጉም ( interpritation) ንድፈ ሃሳባዊ ብያኔ ሲያመነጭ የመዋቅራዊ፣የፍቺ እና የክዋኔን ንድፈ ሃሳቦች በአንድላይ በማምጣትና በውስጡ ያለውን ይዘት ጨምቆ በማውጣት የቀረጸው መሆኑን ዶ/ር ባይለየኝ በክፍል ውስጥ በሰጡት

ማስታወሻ ላይ ገልጸዋል፡፡ይህ ቲዎሪ የትእምርቶችን ትርጉም ምንነት በመመርመር ያላቸውን ፋይዳ የሚገልጽ ነው፡፡ በአንድ ስርአተ ክዋኔ ላይ የተለያዩ ትእምርቶች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ድርጊቶች፣ቁሶች፣ የንግግር ይዘቶች፣ በጽሁፍ የቀረቡ መልእክቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ቋንቋና ፅህፈት ሃሣባችንን የያዙ ውክሎች በመሆናቸው ትዕምርት ናቸው፡፡ ቋንቋ በድምፅ ጽህፈት ደግሞ በቅርጽ ይገለጻሉ፡፡ የሚወክሉት ነገርም በአድማጭ አዕምሮ ውስጥ የሚቀረጽ ወይም የሚከሰት ሃሣብን (idea) ፣ምስል (image) እና ስሜትን (emotion) ነው፡፡ የአንድን ትዕምርት ፍቺ ስንሰጥ ወይም ስንወስድ ፍቺውን የሰጠንበት መንገድ ወይም ምክንያት ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ተጠየቃዊ አካሄድ ወሳኝነት አለው፡፡ ያለዚያ ትዕምርታዊ ፋይዳው ለአንዱ ትክክል ለሌላው ደግሞ ሐሰት ሊሆን ይችላል፡፡

የአንድን ቁስ ትዕምርት ወይም ውክልና ለመስጠት የሚያስችሉ ነገሮች የቁሱ ቅርጽ፣ ቀለም፣ የሚቀመጥበት ቦታ (position) እና የተሰራበት ጥሬ እቃ ናቸው፡፡እነዚህን ገጽታዎች መሠረት በማድረግም የቁሱን አገልግሎት መወሰን ይቻላል፡፡ ይህ ማለትም ከዚህ በፊት ለአንድ ተራ አገልግሎት የሚውልን ጥሬ ዕቃ በመውሰድ ቅርጽ አበጅቶ በመስራት፣ቀለሙን በመለወጥና የተለየ ቦታ በማስቀመጥ ግኡዝ የነበረውን አካል የሚያምኑት መንፈስ እንዲሰፍንበት በማድረግ የቁሱን ተግባር መቀየር ነው፡፡ሰዎች ይህንሲያደርጉ እምነታቸውን፣ አመካከታቸውን፣ ዕውቀታቸውን መሠረት አድርገው በመሆኑ ያ ቁስ ለእነዚህ ሰዎች ማንነትና እምነት መግለጫ ይውላል ማለት ነው፡፡ Whitehead (1985 : 1-19)

ለምሳሌ "ከሰው መርጦ ለንጉስ ከእንጨት መርጦ ለታቦት" እንዲሉ" ግራር ከተባለው የዛፍ አይነት ታቦት ይቀረፃል፡፡ አጋጣሚ በዚህ ዛፍ ታቦት ሳይቀረጽበት ቢቀር እንደሌሎቹ እጽዋቶች ሁሉ ተቆርጦ ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውል ይችላል፡፡ አልያም በስብሶ ይቀራል፡፡ ታቦት ከተቀረጸበት በኋላ ግን አስርቱ ትዕዛዛት ይፃፍበታል ፤ የሰዎች አመለካከትም ለዚህ ቁስ የተለየ ይሆናል፡፡ በህገ ኦሪት ጊዜ እንደነበረው ሁሉ የእግዚአብሄር መንፈስ ያድርበታል ብለው ስለሚያምኑ ክብር ይሰጡታል፤ በቅድስተ ቅዱሳን መንበር ላይም ይቀመጣል የቤተክርስቲያን ሥርዓትም ይፈፀምበታል፡፡ አንድን ቤተክርስቲያን ለመመስረትም አስፈላጊው መሳርያ ሆኖ ይገኛል፡፡ስልጣነ ክህነት በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ መስጠቱም እግዚአብሄር በዚያ ስላለ ቦታው የተቀደሰ መሆኑን በማመን ነው፡፡ ይህ ማለት የማይታየውን የእግዚአብሄር መንፈስ በሚታየው ታቦት ላይ መወከል ነው፡፡ እግዚአብሄር በዚያ እንዳለ

በማመናቸው በሙሉ ልብ ያከብሩታል ፣ይሳሉለታል ይህም እንደ እምነታቸው ይደረግላቸዋል።

ወንበር፣ጠረጴዛ፣ቁምሳጥንና መስቀል ከአንድ ዛፍ ሊሰሩ ይችላሉ። መስቀል የሰውን ልጅ ለመባረክ፣ለመቀደስ፣አጋንንት ለማስወጣት፣ ለመፈወስ የሚችል ሃይል ሲያድርበት ሌሎቹ በየሰው ቤት ውስጥ አልባሌ ቦታ ላይ ሊገኙ ይችላሉ። መስቀል የተጠቀሱትን አይነት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው ቅርፁ እና የሚቀመጥበት ቦታ እንዲሁም መስቀሉን የሚጠቀሙት ካህናት ኃይል እንዲኖረው በእርሱ ከላይ መቀደሳቸውና መፀለያቸው ነው። ሰዎችም የእንጨቱን ቅርፅ ሲያዩ መስቀል መሆኑን የሚረዱት በአእምሯቸው ለእሱ በሚሰጡት የተቀደሰ ትርጉም ነው።

ቁሳዊ ለሆኑና ላልሆኑ ትእምርቶች ትርጉም (Interpritation) የሚሰጠው ሰዎች በተስማሙበት አለም አቀፋዊ እና ማህበረሰባዊ በሆኑ ስምምነቶች ላይ ተመስርቶ ነው እንጂ በሳይንስ ሊረጋገጥ በሚችል እውቀት አይደለም። ለምሳሌ በአንድ ስርአት ያለን ድርጊትን ወይም ክዋኔን ብንወስድ ሰዎች ወደ ግራና ወደቀኝ ወይም ወደፊትና ወደኋላ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በራሳቸው ስሜትና ፍላጎት ሳይሆን ያ ድርጊት እንዲፈፀም በሚያዛቸው መመሪያ ነው። መመሪያው የሚወጣው ከማህበረሰቡ ባህል፣ትውፊት፣ወግ፣ልማድ፣ስርዓትና ከህይወት ልምድ ነው።ማህበረሰቡ በስርአተ ክዋኔው ወቅት ለሚጠቀሙባቸው ቁሶች እና ለሚያከናውኗቸው ተግባሮች ዋጋ እና ትርጉም ይሰጧቸዋል እንጂ ያለምክንያት የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች አይኖሩም።ለምሳሌ በስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔ ወቅት ጳጳሱና ዲያቆናቱ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የስልጣን አሰጣጥ ስርዓቱ የሚያዘውን ነው። ዲያቆናቱ ወደ ምስራቅ ዞረው ስልጣኑን ሲቀበሉ ምስራቅ ፀሐይ የሚወጣበት አቅጣጫ ብርሃን የሚታይበት፣ የቀኝ ፣ የድል ተምሳሌት ነው። እነሆ የጽድቅ ጸሐይ ይወጣላችኋል ተብሎ እንደተጻፈው ፀሐይ በኢየሱስ ክርስቶስ ይመሰላል ። ዲያቆናቱ ድርጊቱን ሲፈጽሙ የሚቀበሉት እምነት ትክክለኛ አቅጣጫ፣ በብርሃን መንገድ መጓዛቸውን ለማመልከት ነው።

ዕውቀት ገቢር (fact) የሆነና ሊቀያየር የማይችል ሐቅ ነው። ትዕምርት ግን አንድን ነገር የሚወክለውና ትርጉም የሚሰጠው አንድ ማህበረሰብ ተስማምቶ ሲቀበለው እና የትእምርቱን ፍቺ ለማግኘት ተጠየቃዊ አካሄዱ የሚያስማማ ሲሆን ብቻ ነው።

# ምእራፍ አምስት

## 5. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ

### 5.1 የዲቁና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ

#### 5.1.1.ቅድመ ስርዓተ ክዋኔ

ዲቁና ከሶስቱ የስልጣነ ክህነት አይነቶች ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ አንድ ግለሰብ የዲቁናን ስልጣን ለመቀበል እንደማንኛውም ማህበረሰብ "በዘፈቀደ" የሚኖር ሳይሆን ከአስተዳደጉ ጀምሮ የሚጠብቃቸው ህጎች እና የሚፈፅማቸው ጥሩ ስነ ምግባሮች መኖር አለባቸው፡፡

መወለድ ስልጣነ ክህነትን ለመቀበል የሚያስችል የተለየ ገጽታ የለውም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ሰው ይወለዳልና፡፡ ስልጣነ ክህነትን ለመቀበል ምክንያት ወይም መስፈርት ሊሆኑ የሚችሉ ከመወለድ በኂላ የሚኖሩ የተለያዩ ክንዋኔዎች ሲሆኑ እነሱም ክርስትና መነሳት( ስርአተ ጥምቀትን መፈጸም)፣ የቤተክህነት ትምህርት መማር እና በድንግልና፣ በቅድስና እና በጥሩ ስነምግባር መኖር ናቸው፡፡

##### 5.1.1.1. ሥርዓተ ጥምቀት

የጥምቀትን ሥርዓት መፈፀም ክርስትና መነሳት ይባላል፡፡ ሥርዓተ ጥምቀት ክርስቲያን መሆን ለሚችል ሁሉ የሚፈፀም ሥርዓት ነው፡፡በመሆኑም ስልጣነ ዲቁናን መቀበል የሚችሉ ሁሉ ክርስትና መነሳት አለባቸው፡፡

ክርስትና መነሳት ክርስቶስን የመቀበል ተምሳሌት ነው፡፡ ጥምቀት ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ ላይ የሚፈፀም ሲሆን የክርስትናን ህይወት ለመጀመር በቀዳሚነት የሚፈፀም ስርአት ነው፡፡ ጥምቀት በስላሴ ስም በተፀለየበት ውሃ መነከር ሲሆን የሚጠመቀውም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው፡፡አላማውም መንፈስ ቅዱስን በመቀበል መንፈሳዊ ፀጋን ለማገኘት፣ የእግዚአብሄር ልጅ ለመሆንና ከውርስ ኃጢአት ለመጻት ነው፡፡

በሐዲስ ኪዳን ዘመን ኢየሱስ ክርስቶስ (ዮሐ 3 ÷5) ‹‹ከውሃና ከመንፈስ ዳግመኛ ካልተወለዳችሁ ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት አትችሉም›› በማለት አስጠንቅቋል፡፡ በመሆኑም የስርአቱ መፈጸም ለክርስቲያኖች ሁሉ ተግባራዊ ሲሆን ክርስትናውን ለመቀበል የሚፈፀሙ የተለያዩ ክንዋኔዎች አሉ፡፡ እነዚህ ክንዋኔዎች የሚፈጸሙት በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሥርዓቱን ለመፈፀም ተብሎ በተዘጋጀ ወይም በተሰራ በክርስትና ቤት ውስጥ ነው፡፡



*የስርዓተ ጥምቀት አፈጻጸም*

ከክርስትና ጋር ተያይዞ የሚፈጸም ልማድ በአንገት ላይ ክር ማሰር ወይም መስቀል ማድረግ ነው፡፡ አንዳንድ ክርስቲያኖች በህገወጥነት ማተብ ወይም መስቀል ሳያደርጉ ቢታዩም ካህናት ግን ስርአቱን ጠባቂ ናቸውና አንገታቸው ባዶ እንዲሆን አይፈቀድላቸውም፡፡ ይህ ስርአት የተጀመረው በቅዱስ ያዕቆብ ዘ እልበረዳኢ በጉባኤ ኬል ቄዶን የሃይማኖት መለያየት በተፈጠረ ጊዜ የእርሱን ወገኖች ለመለየት ሲል በአንገታቸው ማተብ እንዲያስሩ ካዘዛቸው ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ይህንን ስርአት የእስክንድርያ ጳጳሳት ወደ ሃገራችን ይዘውት ከመጡ በኋላ ሊቃውንተ ቤተክርስትያን ከጥምቀት ስርአት ጋር ሲፈጽሙት ቆይተው አሁን እስካለንበት ጊዜ መድረሱን የሰዋሰው ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ የስነመለኮት መምህራን ለማስተማሪያ ባዘጋጁት ‹‹ሃንድ አውት››(ማስታወሻ) ላይ ገልጸዋል፡፡

### 5.1.1.2 የቤተክህነት ወይም የአብነትን ትምህርት መማር

ክህነትን ለመቀበል ከጥምቀት ሥርዓት በተጨማሪ የአብነትን ትምህርት መማር ዋናውና በጣም አስፈላጊው ተግባር ነው። ምክንያቱም ክህነትን ተቀብለው ለአገልግሎት በሚነሱበት ጊዜ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን እና የአምልኮ ስርዓትን ለማስፈፀም እንዚህን ትምህርቶች ማወቅ እና መተግበር የግድ በመሆኑ ነው።

የአብነት ትምህርት በዲቁና፣በቅስናና በኤጲስ ቆጶስነት ስልጣን ለማገልገል የሚያስችል ዕውቀት የሚሰጥበት ነው። ትምህርቶቹ የንባብና የቅዳሴ ትምህርቶች ሲሆኑ የንባብ ትምህርቶች ፊደል፣አቡጊዳ፣ መልዕክተ ዮሐንስ ፣መዝሙረ ዳዊት፣የውዳሴ መፃህፍቶች፣ መልክዐ መልክዕ ፣ የቅዱሳን ገድላት፣ሰዓታት ሲሆኑ የቅዳሴ ትምህርቶች ግብረዲቁና እና በአጠቃላይ መዝገበ ቅዳሴ ላይ ያሉትን የሚያጠቃልል ነው።

የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን ብፁዕ አቡነ ጢሞቲዎስ ግንቦት 23/2003 ዓ.ም በተደረገው ቃለ መጠይቅ አንድ ግለሰብ የክህነትን ስልጣን ከመቀበሉ በፊት እንዲያውቅ የሚጠበቅበት ትምህርቶች በቃል የሚጠኑ መሆናቸውን ገልፀዋል። እነሱንም አንድ በአንድ ሲያስረዱ ለቃል ትምህርቶች መግቢያ የሆኑት በስመአብ፣ ነአኩተከ፣አቡነ ዘበሰማያት፣ፀሎተ ሃይማኖት...ያሉ ሲሆኑ ፤ሌሎች ደግሞ ውዳሴ ከሰኞ እስከ እሁድ ያሉት ውዳሴ ማርያም፣ አንቀጸ ብርሃን ፣መልክዐ ማርያም፣ መልክዐ ኢየሱስ፣ አባ ጊዮርጊስ ደረሱት ከለሊቱ ስድስት ሰዓት ጀምሮ የሚፀለይ ሰዓታት እንዲሁም የዜማና የቅዳሴ ትምህርቶች መሆናቸውን ነው።

በመንበረ ፓትሪያክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተክርስቲያን የሚያገለግለው ዲያቆን ዕጌ ግንቦት 19/2003 ዓ.ም በተደረገው ቃለ መጠይቅ የዲቁናን ስልጣን ለመቀበል በቅድሚያ ፊደል ከዚያም ደግሞ አቡጊዳ እና መልዕክተ ዮሃንስን በቁጥር፣በግዕዝ፣ከግዕዝ ወደ ጉርድ ንባብ፣ከጉርድ ንባብ ወደ ንባብ እያለ እንዳጠናቀቀና ከዚያ በኂላ ወደ ብራና ፅሁፎች በማለፍ በቁጥር፣በጉርድ ንባብ እና በንባብ እንዳነበበ አስረድቶኛል። ከዚያም ዳዊትን "ፍካሬ ዘ ፃድቃን ወሃጥኣን..." እያለ በመጀመር ከጨረሰ በኂላ መምህሩ "እንብበው" የሚል መመሪያ ሲሰጡ መቶ ሃምሳውን ዳዊት ንባባት እንደዚሁ አጠናቆ እናዳነበበ ገልጾልኛል። ከዚህ ቀጥሎ ያለው የሌሊት ትምህርት ሲሆን በዚያም ውዳሴዎችን ከበስመ አብ ጀምሮ እስከ መልክዐ ኢየሱስ ያሉትን በቃል አጥንቷል።

ሰላምለኪ ተብሎ የሚጀመረውን የውዳሴ ማርያም ከዚህ ቀጥሎ በማጠናቀቅ ከሰኞ ጀምሮ እስከ እሁድ ያሉትን በቃል አጥንቷል።በመጨረሻ ላይም መስተጋብዕ፣ አርባዕት፣አርያም፣ሰለስት…የተባሉ የዜማ ይዘቶችን ፆመ ድጓ እስከ ማለፍ ድረስ በመማር የቅዳሴ ትምህርቶችን አጠናቋል። ከነዚህ ትምህርቶች በኋላም የዲቁና ስልጣን እንደተሰጠው አብራርቶልኛል።

እነዚህ ትምህርቶች "የቆሎ ትምህርት" ተማሪው ደግሞ "የቆሎ ተማሪ" በመባል የሚጠራ ሲሆን በገጠር አካባቢ ከውሻ ጋር እየታገሉ "በእንተ ስማ ለማርያም" በማለት ቁራሽ እንጀራ እየለመኑ የሚማሩት ትምህርት ነው። በአሁኑ ጊዜ "የቆሎ ተማሪ" የሚለው ስያሜ መልካም ገጽታቸውን የሚያመለክት አይደለም በሚል እሳቤ ‹‹የአብነት ተማሪ›› በሚል እተተካ ይገኛል።

ክህነትን ለመቀበል የቅዳሴ ዜማ ትምህርት መከታተልና ማወቅ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ቅዳሴ የህዝቡ ሃጥያት የሚሰረይበት፣ በሽታቸው የሚፈወስበት፣ ፀሎታቸው ወደ አምላካቸው የሚደርስበት፣ ምስጋናቸው የሚቀርብበት፣ ልመናቸው የሚሰማበት በተለይ ስጋ ወደሙ የሚፈተትበት(ወይኑና ህብስቱ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋና ደም የሚቀየርበት) በመሆኑ ይህንን ስርአት ለማስፈጸም ይችሉ ዘንድ ነው። የቅዳሴውን ዜማ ሲማሩ የድምፅ አነሳስ፣ አወዳደቅ በአጠቃላይ የያሬድን የዜማ ስልት ይዞ ትክክለኛውን ቅዳሴ መቀደስ ይረዳ ዘንድ የሚያስችል ትምህርት ይሰጣል።

ዲያቆናት ሥልጣነ ክህነቱን ከመቀበላቸው በፊት የሚማሩት የቅዳሴ ትምህርት ገፅታ ምን ይመስል እንደሆነ ለመመልከት ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ/ም በበዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ትምህርት መማርያ ቦታ በመገኘት ሁኔታውን ተመልክቼዋለሁ።

ከረፋዱ 4:30 ላይ በቦታው ስደርስ ተማሪዎቹ በሶስት ምድብ ተመድበው ቅዳሴን ያዜሙ ነበር። የቅዳሴ መማርያ ክፍሎች ከሆኑት ውስጥ ተማሪዎች ሲያዜሙ ያገኘኋቸው በስተቀኝ በኩል ባሉት ክፍሎች ውስጥ ነው። የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቱ የቅዳሴ መምህር መጋቤ የማነ ብርሃን ጌታ ከተቀመጡበት ክፍል ስደርስ ተማሪዎቹ ግራና ቀኝ እርሳቸው ደግሞ ከመሃል ሆነው ትምህርቱን ሲያስተምሩ አገኘኋቸው።



*መምህር የማነ ብርሃን ጌታ ለአብነት ተማሪዎች የቅዳሴ ትምህርት ሲያስተምሩ*

የቅዳሴ መምህሩ መምህር የማነ ብርሃን ጌታ እንደነገሩኝ በዚያ ቦታ የሚማሩት የቅዳሴ ትምህርት ግብረ ዲቁና፣መዝገበ ቅዳሴ እና አጠቃላይ የቅዳሴ ትምህርት ሲሆን ትምህርቱ የሚሰጥበት ጊዜ ከሰኞ እስከ አርብ ጠዋትና ከሰዓት ነው፡፡ የተለያዩ ዝግጅቶችና ክብረ በዓሎች ሲኖሩ ግን ተማሪዎች ለአገልግሎት ስለሚሄዱ ትምህርት ላይኖር ይችላል፡፡

በመምህር የማነ ብርሃን ጌታ ግራና ቀኝ የተቀመጡ ተማሪዎች የተለያዩ ዜማዎችን የሚያጠኑ ሲሆኑ ሁለቱ ቡድኖች ካላቸው ልምድ የተነሳ አንዱ የአንዱን ቅዳሴ በመስማት እርስ በእርሱ አይደበላለቅባቸውም፡፡ መምህሩ ለማስተማር የፈለጉትን የቅዳሴ ዜማ ሲያሰሟቸው የ በጥንቃቄ እየደጋገሙ በማዜም እስከመጨረሻው የሚዘልቁት ሲሆን በዜማ የሚናገሩትን ቃል ከቅዳሴ መፅሐፍ በማንበብ ያጠናሉ፡፡ መምህር የማነ ብርሃን የቅዳሴን ዜማ ከማስተማር ጥልቅ ችሎታቸው የተነሳ ሁለቱ ቡድኖች የሚያዜሙትን ዜማ በአንድ ጊዜ በመስማት የተሳሳተውን ለይተው ተማሪዎቹ እንዲያስተካክሉ የማድረግ ብቃታቸው ከፍተኛ መሆኑን ተመልክቻለሁ፡፡



*ተማሪዎቹ በመማሪያ ክፍል ውስጥ እና በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ ሆነው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ*

እንደ መምህር የማነ ብርሃን ገለፃ ተማሪዎቹ መጀመሪያ ክፍል ላይ ግብረዲቁና የተባለውን በግዕዝ ፣ በእዝልና በአራራይ ዜማ የሚዜም የቅዳሴ ትምህርት የሚያጠኑ ሲሆን ይዘቱም በቅዳሴ ጊዜ ህዝቡ የሚያዜሙትን ዜማ የያዘ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል መዝገበ ቅዳሴ የሚማሩበት ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል ላይ ያጠናቀቁትን እና በስርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ካህን የሚቀድሰውን ‹‹ይበል ካህን›› የሚለውን ዜማ የሚያጠኑበት ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ በሁለቱ ክፍሎች ውስጥ የተማሯቸውን እየከለሱና በመምህሩ አጋዥነት ይበልጥ ትምህርቱ እየጠራ፣እየጠነከረ ትክክለኛውን የቅዳሴ ዜማ የሚማሩበት ነው፡፡ እነዚህን ትምህርቶች ተምሮ ለመጨረስ የተማሪዎች ብቃት የሚወሰነው እንደችሎታቸው ነው፡፡ ከወራት ጀምሮ እስከ አመታት ሊያስቆጥር የሚችሉ ጊዜያትን ሊፈጅ ይችላል ፡፡ በመሆኑም የጊዜ ገደብ ተሰጥቶት በዚህ ቀን ማለቅ አለበት የሚባል አይደለም ፡፡

በአጠቃላይ የአብነት ትምህርት የሃገራችንን ትውፊት የሚያመለክት ገጽታ ያለው ነው፡፡ይህም ትምህርቱ የሚሰጠው ጥንት የነበረውን ሥርዓት ተከትሎ በቃል ነው፡፡ቃላዊነቱ ጥንታዊ መጽሐፎች በተቃጠሉ ጊዜ በጽሑፍ ተክቶ ለማቆየት ያስቻለ ነው፡፡በተማሪዎች እና በመምህራን መካከል ያለ ግንኙነት፣የአነጋገር ዘይቤ፣የጸሎት መክፈቻና መዝጊያ ሥርዓቶች፣የማስተማሪያ ዘዴ እና ሌሎችም ከቀደምት አባቶች እና ትውልዶች በድግግሞሽ ፣በገለጻ እና በድርጊት ተስተላልፈው የመጡ(የተገኙ) ናቸው፡፡

### 5.1.1.3 ንፅህና እና መልካም ስነ-ምግባር

በፍትሃ ነገሥት አንቀፅ ሰባት ላይ እንደተደነገገው ዲያቆን ለመሆን በንጽህና እና በቅድስና መኖር ያስፈልጋል፡፡ በድንግልና ፀንቶ ያልኖረ ዲቁና ሊሰጠው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከክህነት ደረጃዎች የመጀመሪያው በመሆኑና ዲያቆኑ የጵጵስናን ስልጣን ለመቀበል ቢፈልግ ድንግል መሆኑ እና አለመሆኑ ስለሚያስጠይቀው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቤተክርስቲያን ስርአት አንድ ግለሰብ ከማግባቱ በፊት ከሴት ጋር መገናኘት አይፈቀድለትም፡፡ ይህ ስርአት በዘመነ ሐዲስ ጊዜ ሐዋርያት በንጽህና ሆነው አገልግሎት ይሰጡ እንደነበር በማሰብ የእነርሱ ደቀመዝሙር ለመሆን፣ አርአያነታቸውን ለመከተል ነው፡፡ እድሜውም ከ 30 አመት በታች ቢሆን ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ከዚያ በላይ አግብቶ፣ ልጅ ወልዶ የመኖር ፍላጎት ሊያድርበት ስለሚችል በምኞቱ እንደይሰናከል ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ያገባም ሆነ ከሴት የደረሰ ወንድ ለሥልጣነ ዲቁና ሊበቃ አይችልም፡፡አንድ ዲያቆን ሚስት ካገባ በኋላ የዲቁና አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡ነገር ግን ወደ ቀጣዩ የስልጣን እርከን ለመሻገር ቢፈልግ መስፈርቶችን ካሟላ በኋላ የቅስና ስልጣንን መቀበል ይችላል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዲያቆናት (ጢሞ 3፡8-13) ትእግስት ያላቸው፣ቁጡ ያልሆኑ፣ነውር የሌለባቸው፣የማይሰክሩ፣ ሀሰት የማይናገሩ፣የሚታዘዙ፣ትጉህና ቅን መሆን እንደሚገባቸው ያስረዳል፡፡

### 5.1.2 ሥርዓተ ክዋኔ

አንድ ግለሰብ ምንም እንኳ ለሥልጣነ ዲቁና የሚያበቁትን መሥፈርቶች አሟልቶ ሥልጣኑን ለመቀበል ቢፈልግ ወዲያው ሊሰጠው አይችልም፡፡ ክህነት በሰው መብት የሚሰጥ ማዕረግ ሳይሆን በእግዚአብሄር ሃሳብ፣ ምርጫ እና ፍላጎት የሚፈፀም ነው ተብሎ ስለሚታመን አንድ ግለሰብ ክህነቱን የሚሰጡት ጳጳስ ዘንድ ሄዶ "ዲያቆን መሆን እፈልጋለሁና ዲቁና ይስጡኝ " ቢል እውነተኛ ጥሪ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ እውነተኛ ጥሪ መሆኑን የሚረዱባቸው መንገዶች በፆምና በፀሎት እግዚአብሄርን በመጠየቅ እውነታው እንዲገለጥላቸው ማድረግ እና ግለሰቡን የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ ናቸው፡፡

ጳጳሱ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቁት የልጁን ዕድሜ እና የአዕምሮ ብስለት በመገምገም በአመላለሱ የትኛውን አቅጣጫ እንደተከተለ ለመረዳት ነው፡፡ ለምሳሌ "ዲያቆን መሆን ለምን ፈለግህ?" ብለው ቢጠይቁት‹‹ በሰው ፊት ጥሩ ካባ ለብሶ ወዲያ ወዲህ ማለት ደስ ያሰኛል፣

ዲቁና ጥሩ ደሞዝ አለው፤የሚቀድሱ ዲያቆኖች ጥሩ ልብስ ለብሰው ሳያቸው ቀንቼ እኔም እንደነሱ እሆናለሁ ብየ›› እና እነዚህን የመሳሰሉ መልሶች ቢመልስ ይህ ሰው የተጠራው ከእግዚአብሄር ዘንድ ሳይሆን በራሱ ተነሳሽነት ለስጋዊ ፍላጎቱ እና ራሱን ደስ ለማሰኘት ብቻ ዲቁናውን ለመቀበል መወሰኑን ያመለክታል ።

ይህን አይተው ሥልጣኑን ቢሰጡ ክህነቱ ከዕውነት ያልሆነ በመሆኑ አንድ ቀን ዋጋ ሊያጣ ይችላል፡፡በአንፃሩ ደግሞ "ዲቁናን መቀበል የፈለግሁት ልቤ ዲያቆን እንድሆን ይገፋፋኛል፤ከሁሉም ነገር አሰቀድሜ ዲያቆን ሆኜ ባገለግል ፣ መብላት መጠጣት… እናት አባትም ቀርቶብኝ ቤተክርስቲያን ውዬ ባድር ደስ ይለኛል ፣ የቤተክርስቲያን ደወል ስሰማ ሂድ… ሂድ ይለኛል እንጂ ተኝቼ እንቅልፍ አይወስደኝም…..ወደ ቤተክርስቲያን ስሄድ ልቤን ደስ ይለዋል እንጂ ከዚያ ውጣ ውጣ አይለኝም ፣ ማገልገል ፣ መታዘዝ ያስቀናኛል" የሚሉ እና የመሣሠሉትን መልሶች ከዲያቆኑ ከሰሙ ይህ ትክክለኛ ጥሪ መሆኑን መገንዘብ የሚችሉበት ሁኔታ መሆኑን የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል ሰኔ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገው ቃለ መጠይቅ ገልፀውልኛል፡፡ ዲቁናውን የሚሰጡት ጳጳስ እነዚህን ሁኔታዎች ካጣሩ እና መርምረው ትክክለኛውን ሁኔታ ከተረዱ በኋላ ዲቁናው ለሚገባቸው ሰዎች ሥልጣኑን ይሠጣሉ፡፡

የዲቁና ሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓት እንዴት እንደሚከወን ለመከታተል እና በክዋኔው የሚታዩ ፎክሎራዊ ገፅታዎችን ለማየት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተክርስቲያን ግንቦት ሃያ (አርብ ግንቦት አስራ ዘጠኝ ለቅዳሜ አጥቢያ) ቀን ተፈጽሞ የነበረውን የስልጣነ ዲቁና ሥርዓተ ክዋኔ እንደሚከተለው ተከታትየዋለሁ፡፡

በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተክርስቲያን ሥልጣነ ዲቁናውን የሰጡ የአዲስ አበባ ሃገረስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቀውስጦስ ናቸው፡፡ አቡነ ቀውስጦስ ሥልጣነ ዲቁናውን ለሚቀበሉ ግለሰቦች ስርዓቱን ከመፈፀማቸው በፊት በዚህ ጥናት የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በሚገባ ማሟላታቸውን አረጋግጠው ከጨረሱ በኋላ የሚሰጡበትን ዕለት አሳወቁ፡፡ ተቀባዮችም በግላቸው ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ፈፅመው (ተቀባዮቹ እንደነገሩኝ አስራ ስምንት ሰዓት ፆመው፣ ጸልየው፣ንስሃ ገብተው፣ራሳቸውን ከበደል አንፅተው) ለስርአቱ ቀረቡ፡፡አስራ ስምንት ሰዓት መጾማቸው በሆዳቸው ውስጥ የቀረ ምንም አይነት ምግብ ሳይኖር ስጋ ወደሙን መቀበል ስላለባቸው ነው፡፡ ዲያቆናቱ ወደ

ቤተክርስቲያን ከመምጣታቸው አስቀድሞ ከሌሊቱ አስር ሰዓት ሲል ቀድሜ በመገኘት የተለያዩ ሁኔታዎችን ስቃኝ ነበር። ከቤተክርስቲያኑ ደርሼ ወደ ውስጥ ሳመራ በሩ ተከፍቶ ካህናት በውስጥ ሆነው ኪዳን( ማንኛውም ሥርዓት ከመፈጸሙ በፊት የሚጸለይ ጸሎት) ያደርሱ ነበር። ቀድመው ያልደረሱ ሌሎች ካህናት እና ህዝበ ክርስቲያን አንድ በአንድ እየመጡ ቤተክርስቲያኗን እየተሳለሙ ወደ ውስጥ በመዝለቅ በስርዓተ ኪዳኑ ላይ ይሳተፋሉ።

አስር ሰዓት ተኩል ሲል በዕለቱ ሥልጣነ ዲቁናውን የሚቀበሉ ስድስት ወጣቶች በአንድ ላይ መጡ። እነዚህ ወጣቶች በስርዓቱ ላይ ለመገኘት ማርፈድ እንደሌለባቸው ስለሚያውቁ ተጠባብቀው መምጣት እንዳለባቸው ከዚህ ቀደም ተነጋግረው ነበር። ሁሉንም በአንድነት ሳያቸው አብረው እንደሚመጡ ጠብቄ ነበርና አልተገረምኩም። ይልቁንስ ልክ እንደመጡ ምን እንደሚሰሩ፣ ለስርዓተ ክዋኔው ምን አይነት አካላዊ እና ስነልቦናዊ ዝግጅት እንዳደረጉ ለመረዳት ጣርኩ ።

ሁሉም ነጠላቸውን መስቀለኛ አጣፍተው ለብሰዋል። አንድ ልጅ የፀሎት መፅሃፍ ይዟል። አለባበሳቸው ቀለል ቀልጠፍ እና ጠንቀቅ ያለ ( ስነስርአት ያለው) ነው። አንዱ ብቻ ነጭ ሱሪ ሲለብስ ሌሎቹ ጥቁር፣ ቡኒ እና ሰማያዊ ቀለም ያለው ሱሪ ለብሰዋል። ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ከገቡ በኋላ እርስ በእርስ አያወሩም ነበር። በር ላይ ሲደርሱ እያማተቡ ጫማቸውን እያወለቁ ወደ ውስጥ ገቡ። በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲገቡ እነዚህን ሥርዓቶች የሚፈጽሙት በኦሪት ዘመን የነበረውን ቀኖና ተከትለው ነው።በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተጻፈው እግዚአብሔር ሙሴን በደብረሲና ሲያነጋግረው የቆምክባት ስፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን አውልቅ ብሎታል።እንዲሁም በመጽሐፈ ኢያሱ (5:15) ላይ የእግዚአብሔር መልአክ ኢያሱን ሊያነጋግረው በፈለገ ጊዜ ጫማውን ሳያወልቅ ወደ እርሱ እንዳይጠጋ ተናግሮታል። የተቀደሰች ቦታ የተባለችው የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት። ቤተክርስቲያን የተቀደሰች በመሆኗም የእግዚአብሔር ማደሪያ ናት። በመሆኑም በእርሱ ፊት በትህትና፣ በአክብሮት እና በፍርሃት በፊቱ መቆም እንደሚገባ የሚያመለክት ነው ሲሉ ሊቀካህናት ክንፈገብርኤል አልታዬ ገልጸውልኛል።

ዲያቆናቱን ከስርዓተ ክዋኔው በኋላ በሌላ ቀን የቡድን ውይይት ባደረግንበት ጊዜ ስማቸውን ጠይቄያቸው፡-

አዲሱ ንብረት (ገብረ ማርያም)

ተሾመ ደምለው ( ገብረ ህይወት)

አለማየሁ ዘለቀ (ገብረ እግዚአብሔር)

አስቻለው ግርማ (ተክለ ማርያም)

ምስጋናው ካሱ (ኃይለ ሚካኤል)

ሰለሞን ሞላልኝ (ወልደ ኪዳን)

እንደሚባሉ ገልፀውልኛል። (በቅንፍ ውስጥ ያለው የክርስትና ስማቸው ነው።) እድሜያቸውንም ጠይቄያቸው ከ 21-23 ባለው ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

ወደ ቤተክርስትያን ውስጥ ከገቡ በኂላ በወንዶች መቆሚያ በኩል በመሆን የግል ፀሎታቸውን ማድረግ ጀመሩ። የቅዳሴን ትምህርት ለሶስት አመታት በበዓታ ለማርያም መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከመምህር የማነብርሃን ጌታ ዘንድ ተምረዋል።

ጊዜው ወደ አስራ አንድ ሰዓት ሊጠጋ ሲል ብዙ ሰዎች የዕለቱን ኪዳን (ፀሎት) ለማድረስ እና ሥርዓተ ቅዳሴውን ለመከታታል መምጣት ጀመሩ። ከተመለከትኳቸው ሰዎች መካከል በዕድሜ ገፋ ያሉ ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም መነኩሴዎች በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው ሲሆን ከህፃናትና ከወጣቶች ደግሞ ጎልማሶች በተሻለ ቁጥር በዛ ብለው ይታዩ ነበር። እየነጋ ሲሄድ ግን ቀስ በቀስ የወጣቶችና የህፃናት ቁጥር ጨምሮ ነበር። አብዛኛዎቹ ሰዎች ነጠላ ጋቢ እና ኩታ ለብሰው ይታያሉ።

ልክ አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ መጡ። ስልጣኑን የሚቀበሉ ወጣቶች እሳቸው ዘንድ በመቅረብ ቡራኬ ተቀበሉ። እሳቸውም ወደ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ በመግባት በስተግራ በኩል ባለው በወንዶች መቆምያ በኩል ሥርዓተ ክዋኔውን ለመፈፀም ተዘጋጅተው ቆሙ። አቡነ ቀውስጦስ ጥቁር ሙሉ ልብስ (ቀሚስ) ለብሰዋል፤አክሊለ ሶክ (ቆብ) እና የማርያም ምስል ያለበት ረጅም የአንገት መስቀል(አይከን) አድርገዋል፤ ፀሎቱን እየፀለዩ የሚባርኩበት ተለቅ ያለ ከብር የተሰራ የእጅ መስቀልም ይዘዋል።

የዲቁና ሥልጣን ሥርዓተ ክዋኔ የተካሄደው በቅኔ ማህሌቱ ቦታ( ወደ ቤተክርስቲያኗ በዋናው በር በኩል ገብተው በስተግራ በኩል እጥፍ ሲሉ የሚገኘው የወንዶች መቆሚያ ) ላይ ነው። እዚያ ቦታ ላይ ሆነው ወደፊት ለፊት ሲመለከቱ የኢየሱስ ክርስቶስ


ስቅለት፣የማርያም፣ የስላሴዎች፣ቅዱሳትና ሰማዕታት ስዕሎች ይታያሉ። ወለሉ ቀይ ዥንጉርጉር ቀለም ያለው ምንጣፍ ተነጥፎለታል። በወንዶችና በሴቶች መቆሚያ በኩል ከእንጨት የተሰሩ አግዳሚ ወንበሮች በስርዓት ተደርድረው ተቀምጠዋል። ሰዎችም በእነዚህ ወንበሮች አንፃር ቆመው ሥርዓተ ኪዳኑን ይከታተላሉ። ይህንን አልፈው ወደፊት ሲመለከቱ ከፍ ያለ ቦታ ይታያል።ስሙም ቅድስት ይባላል።

ይህ ቦታ ከብረት የተሰራ "አጥር" ተበጅቶለታል። አጥሩ የሰውን ሙሉ አካል እንዲሸፍን ወይም ማንንም እንዳያሳይ ሆኖ የተሰራ ሳይሆን ቦታውን ለመከለል ብቻ በብረት የተሰራ ነው። በዚህ ቦታ ላይ የሚቆሙት ወንዶች ሲሆኑ እነዚህ ሰዎች በቅዳሴው ሥርዓት ላይ ተሰጥኦውን በመመለስ ከሌሎች ይልቅ እንደሚገባው የሚሳተፉ ናቸው። ቦታው እርገት በወረደ ጊዜ ሴቶች በሴቶች መቆምያ በኩል ፣ወንዶች ደግሞ በፊት ለፊት ሆነው ስጋውንና ደሙን የሚቀበሉበት ነው። ይህንን ቦታ ከቀጣዩ ክፍል የሚለየው ወርቃማ ቀለም ያለው ትልቅ መጋረጃ ሲሆን ወደ ውስጥ ዘልቀው ለመግባት የሚያስችሉ ሁለት ባለመጋረጃ በሮች አሉት። አይንን ከዚህ ቦታ ነቅለው ወደ ውስጥ ሲመለከቱ ቅድስተ ቅዱሳኑን ያገኛሉ።

ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ የዲቁናን ሥልጣን ለመስጠት ስርዓተ ክዋኔውን ሲጀምሩ ዲቁናውን የሚቀበሉ ወጣቶችን በትኩረት ተመልክተው ቡራኬ በመስጠት ነው።በቤተ ክርስቲያን ስርዓት ካህናት ከምእመናን ጋር ሲገናኙ እና የተለያዩ ፕሮግራሞች ሲጀመሩ ቀጣዩ ሂደት የተሳካ ይሆን ዘንድ፣ለተቀባዮቹ የመንፈስ ንጽህና፣ቅድስና፣ደህንነት ማግኘት ይችሉ ዘንድ ቡራኬ መስጠት የተለመደ ነው። ከዚያም ክህነት ተቀባዮቹ ከጳጳሱ ፊት ለፊት ( ትይዩ ) ሆነው በመቆም የክርስትና ስማቸውን ተራ በተራ ነገሯቸው።ለማዊ ስማቸውን ያልተናገሩበት ምክንያት ክርስትና ሲነሱ በእግዚአብሄር ፊት የተሰጣቸው ስም መሆኑና ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሄር የሰውን ልጅ በመንፈሳዊ ህይወቱ እና ስራው እንጂ በአለማዊ ህይወቱ ሊያውቅ እንደማይፈልግ መሆኑን ዲቁናውን የተቀበሉት ዲያቆን አስቻለውና ተሾመ ገልጸውልኛል።

ከዚህ ቀጥሎ አቡነ ቀውስጦስ ፊታቸውን ወደ መቅደሱ፣ ሥልጣኑን የሚቀበሉት ደግሞ ወደ እሳቸው አዙረው ፀሎት መፀለይ ጀመሩ። ከተፈፀሙት ሥርዓቶች ውስጥ ረጅም ሰዓት የወሰደው የጸሎት ስርአት ነው። ስርአቱ የተፈጸመው በንባብ ሲሆን ውስጣዊ ይዘቱ

ለዲያቆናቱ እግዚአብሐሄርንና ሰውን ማገልገል እንዳለባቸውና አጠቃላይ ተግባራቸውን የሚያሳውቅ ነው። ይህም ድሆችን፣ባልቴቶችን፣ሽማግሌዎችን፣እናት አባት የሌላቸውን ይረዱ ዘንድ፤ለቄሱና ለጳጳሱ በአክብሮትና በትህትና በመላላክ አገልግሎት መፈጸም ነው።




*ብጹእ አቡነ ቀውስጦስ ስርአተ ዲቁናውን በንባብ ሲፈጽሙ*

ጳጳሱ የዲቁናውን ሥልጣን ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት የተፃፈበትን መፅሐፍ ሲያነቡ ዲቁናን ከሚቀበሉት ወጣቶች ውስጥ ተሾመ የተባለው ልጅ መጽሐፉን የያዘላቸው ሲሆን እንዲይዝ የተደረገው እንደሌሎቹ ፊቱን ወደ እሳቸው አዙሮ የመፅሐፉን ጀርባ ደግሞ ወደ ደረቱ አስጠግቶ የተገለጠውን ፅሁፍ ወደሳቸው በማድረግ ነው። መጽሐፉን አትሮንስ ላይ አስቀምጦ ከማንበብ ይልቅ ሰው እንዲይዘው የተደረገበት ምክንያት ለስርአተ ክዋኔው ክብር ለመስጠት ሲባል ነው።በዚህ ስርአት የክዋኔው ድርሰት ቃላዊ( verbal ) ፣ ጽሑፋዊና ምልክታዊ(non verbal)፣ ተምሳሌታዊ (behavioral) በሆኑ ቅርጾች የቀረበ ሲሆን እነሱም የሚነበቡት በጽሑፍ ያሉ መመሪያዎች ፣ በቃል የሚባሉት ጸሎቶችና ንግግሮች ፣ እንዲሁም ትእምርታዊ ፋይዳ ያላቸው ድርጊቶች ናቸው።

በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ጽሁፎች  የተፃፉት በጥቁርና በቀይ ቀለም ሲሆን አብዛኛው ፅሁፍ በጥቁር ቀለም ተፅፏል፡፡ በቀይ ቀለም የተፃፉት የእግዚአብሄር፣ የቅድስት ማርያም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የመላዕክታን፣ የፃድቃን ሰማዕታት ስሞችና ሌሎች አጽንኦት የተሰጣቸው ጉዳዮች ሲሆኑ ቀይ መሆኑ ለእነሱ ስም ክብር ሲባል ከሌሎች ጽሑፎች ለመለየት ነው፡፡ ስርአተ ክዋኔው የተካሄደበት ቋንቋ ግእዝ ነው፡፡ በመፅሐፉ ውስጥ ያሉት ፅሁፎች የተፃፉትም በግዕዝ ቋንቋ ነው፡፡  ይህ የሆነበት ምክንያትም የቤተክርስቲያን ቋንቋ ግእዝ በመሆኑና ስርዓቱ ጥንት በቋንቋው ተጽፎ የተቀመጠ በመሆኑ ነው፡፡

በዕለቱ የቀረበው *ሥርዓት*  የአናጉንስጢስነት ፣የመዘምር፣የንፍቀ የዲቁናእና የሊቀዲቁና ሹመት ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም አንድ ዲያቆን ለመሆን የሚችል ግለሰብ በቅድሚያ እንዚህን ሹመቶች በደረጃ ማግኘት ስለሚጠበቅበት ነው፡፡ይህ የስልጣን አሰጣጥ ስርአት ልማዳዊ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የክርስትናን ሃይማኖት ተቀብላ ጳጳሳትን ከግብጽ ታስመጣ በነበረበት ጊዜ  የሚላከው አንድ ብቻ  በመሆኑ ለሁሉም ለማዳረስ  አስቸጋሪ ነበር፡፡ስለዚህ ሁሉንም ሹመቶች በአንድ ቀን ይሰጧቸው ነበር፡፡ ይህንን ስርአት ብፁአን አባቶች ይፈጽሙት ነበርና ያ ተይዞ  አሁን በዚህ መልኩ በልማድ ይሰጣል፡፡

እነዚህ ስርአቶች ሲፈፀሙ ለእያንዳንዱ ሹመት የሚሆኑ ጸሎቶችን ጳጳሱ ጸልየዋል፡፡ በእጃቸውም እያሳለሙ ቡራኬ ሰጥተዋል፡፡ ስልጣኑ ለእነሱ እንዲሆን ለማድረግ  የክርስትና ስማቸውን "ለገብርከ!" ብለው የጠሩ ሲሆን እነሱም  በህብረት ሆነው "ገብረ እገሌ!" (በእገሌ ፋንታ የራሳቸውን የክርስትና ስም) በማለት   ተናግረዋል፡፡ለስርአተ ሹመቱ የሚባለውን የጸሎት ምእራፍ አንብበው ሲጨርሱና ሹመቶቹን ሲሰጡ ‹‹ወ እሰይመከ ….››ብለው ስማቸውን በመጥራት ሲሆን እነሱም ሹመቱን መቀበላቸውን ወደ ቤተ መቅደሱ እየዞሩ በመስገድ ገልጸዋል፡፡



*የዲቁና ስልጣን መቀበላቸውን ለማመልከት ‹‹ወእሰይመከ ንፍቀ ዲያቆን›› በማለት ሲገልጹላቸው*

ተሳታፊዎች ይህንን ሥርዓት ሲከታተሉ ቀልባቸውን በመሰብሰብ እያዳንዷን የጳጳሱን ድርጊት በተመስጦ በመከታተልና በመፈፀም ነው፡፡ ሁሉም ሥርዓት ሹመቱ ሲከናወን እና ስልጣኑ ሲሰጣቸው ተሰምቷቸው የነበረው ስሜት ይህ ነው የማይባል ደስታ እና ክብር እንደሆነ ገልፀውልኛል፡፡ ምክንያቱም ማንም ሰው እንደፈለገው ማግኘት የማይቻለውን ሥልጣን በእግዚአብሔር ሃሳብና ፍቃድ ማግኘታቸው እና ስርዓቱ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉበት ፣ ለተለየ አገልግሎትም እንዲሰማሩ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ነው፡፡ስልጣነ ክህነት የተሰጣቸው ዲያቆናት በክዋኔው ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ግን ስርአቱን ከመመልከት በቀር ተሳትፎ ያላደረጉ በመሆናቸው ፍዝ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡

ክህነት የሚሰጠው በቅዳሴ ስርዓት ላይ ነው በመሆኑ ጳጳሱ የንፍቀ ዲቁናውን ስርአት ፈጽመው ወደ ዲቁናው ስርአት "ኦ ንፍቀ ዲያቆን ወልድየ…"ብለው ሲገቡ በእለቱ የቅዳሴ ተረኛ የነበሩ ካህን የኪዳኑን ስርዓት ሲፈፅሙ ቆይተው ስልጣነ ክህነቱ በሚሰጥበት አቅጣጫ ከሰራዒ( ገባሬ ሰናይ) ዲያቆንና ዣንጥላ ከያዘው አናጉንሲጢስ ጋር ሆነው መጡ፡፡ ዲያቆኑ ትልቅ መስቀል ቄሱ ደግሞ ጥናቸውን ይዘዋል፡፡ከዚያም አካባቢው (ቦታው) በእጣን መዓዛ ተሞልቶ (ታውዶ) ጢሱ እስኪትጎለጎል ድረስ አጠኑና ሄዱ፡፡ ዳዊት በመዝሙሩ አቤቱ

ጸሎቴን በፊትህ እንደ እጣን ተቀበልልኝ ባለው መሰረት ይህ መደረጉ ጸሎታቸው እንደ እጣኑ ለእግዚአብሔር እንዲደርስ በሚል እሳቤ ነው፡፡

በስርአተ ክዋኔው ለሰባት ጊዜ ያህል ወደ ምዕራብ እና ምስራቅ ቦታቸውን እየቀያየሩ ዑደት የፈጸሙ ሲሆን የዚህ ድርጊት ተምሳሌት ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን ለማመልከት ነው፡፡እንደዚሁም ድርጊቱ ቤተ መቅደሱን (ያሉበትን ቦታ) እንደ ዓለም በመቁጠር ክርስቶስ በዘመነ ስጋዌው ወቅት በተለያዩ አቅጣጫዎች ተዟዙሮ ማስተማሩን ለመግለፅ ሲሆን እነሱም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይህንን ተግባር ለመፈፀም ሃላፊነት የተጣለባቸው መሆኑን ለማመልከት እንደሆነ የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህር ደጉ ዓለም ካሳ ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ/ም በተደረገው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡ እንደዚሁም በእያንዳንዱ የሹመት አሰጣጥ ስርዓተ ፍፃሜ ላይ ወደ ቤተ መቅደሱ ዞረው መስገዳቸው ለአምልኮተ እግዚአብሔር መግለጫ መሆኑን ጨምረው ገልፀውልኛል፡፡



ከዚያም የዲቁና ሥልጣን ለመስጠት የሚያስችለውን ፀሎት ከመጽሐፉ ላይ ከደገሙ (ከጸለዩ) በኋላ እጃቸውን በራሳቸው ላይ ተራ በተራ ጭነዋል፡፡ ይህንንም ሲፈጽሙ የቀኝ እጃቸውን በዲያቆናቱ ራስ ላይ ጭነው ከመጽሐፉ አንቀፆችን አነበቡ፡፡ቀጥለውም ሁለት እጃቸውን ደራርበውበመጫን ጸለዩ፡፡





*የአንብሮተ ዕድ ስርዓት አፈፃፀም*


ይህ ስርአት "እንብሮተ ዕድ" የሚባል ሲሆን ሲፈጽሙም እጃቸውን በራሳቸው ላይ ጭነው ለተወሰነ ደቂቃ ወደ ላይ እየተመለከቱ በተመስጦ ፀሎት እያደረጉ ነው። ይህም ስርዓት እንደተፈፀመ ጸሎት ካደረጉ በኋላ በግራ እጃቸው አገጫቸውን ፣ በቀኝ እጃቸው ደግሞ መስቀላቸውን በመያዝ ግንባራቸውን፣ አገጫቸውን፣ የግራ ጉንጫቸውንና የቀኝ ጉንጫቸውን ጠበቅ ጠበቅ እያደረጉ በማስነካት ባረኳቸው። በዚህ ጊዜም በግዕዝ የሚፀልዩት ፀሎት ነበር፣ ይህ ሥርዓትም ጸጋ እግዚአብሄርን የሚያገኙበት፣ስልጣነ ዲቁናውን ከጳጳሱ እጅ የሚቀበሉበት እና መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በእነሱ ላይ እንዲያድር የሚደረግበት መሆኑን ሊቀካህናት ክንፈገብርኤል አልታዩ ገልጸውልኛል ።

*ብጹእ አቡነ ቀውስጦስ የእግዚአብሄር ጸጋና በረከት እንዲያድርባቸው ዲያቆናቱን ሲባረኩ*

በሉቃስ ወንጌል (11፡2 ) ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ምን በማለት መጸለይ እንዳለባቸው ባስተማራቸው መሰረት የቤተክርስቲያን ሥርዓት እና አምልኮ በሚፈጸምበት ጊዜ አባታችን ሆይ ተብሎ እንዲጸለይ ይደረጋል። በሥልጣን አሰጣጥ ስርዓቱም ይህ ጸሎት እንዲጸለይ ከተደረገ በኋላ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ 12 ጊዜ እንዲሉ አዘዟቸው። በቤተክርስቲያን ስርዓት እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ሲባል በተለምዶ አራቱን ጣቶች በመዘርጋት በአውራ ጣት የጣቶችን አጥቅ በመንካት ነው። አራቱ ጣቶች ሶስት ሶስት አጥቆችን የያዙ ስለሆነ እነዚያ ሲቆጠሩ (4x3= 12) ይሆናሉና። 12 ጊዜ እንዲባል የታዘዘበት ምክንያትም በቀን ውስጥ 12 ሰዓታት ስላሉ ቀኑን ሙሉ ስንሰራው የዋልነውን ሃጢአት ለማስረይ ነው በማለት ያምናሉ። ይህ እንደተጠናቀቀም ዲቁና የተቀበሉትን ወደ

እሳቸው ጠጋ እንዲሉ በማድረግ ቃለ ምዕዳን( ማስጠንቀቂያና ምክር) ሰጧቸው ።
ከሰጧቸው ማስጠንቀቂያዎች ውስጥ ለምሳሌ “ በድፍረት ቤተክርስቲያን ገብቼ አገለግላለሁ፣ ንጽህናየን አጎድፋለሁ ፣በስውር ሃጢያት እሰራለሁ ብትሉ በስውር የሚያይ እግዚአብሄር ሃጢያታችሁን ይይዝባችኇል” ብለው ያስጠነቀቋቸው ሲሆን ከሰጧቸው ምክሮች “ ክህነት የማይደገም ምስጢር ነውና ክህነታችሁን የሚያጎድፍ ተግባር አትፈጽሙ፣እግዚአብሄርንና ሰውን ብቅንነት አገልግሉ።።ይህንን ባታደርጉ ግን ምእመናን እንኳ ይከሷችኇል። ‘ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ’ ….ይህ አገልጋይ ሊሆን አይችልም” በማለት ይመሰክሩባችኇል። በአንጻሩ ደግሞ መልካም አገልጋይ ከሆናችሁ “ለከፍተኛ ማእረግ የሚበቃ ነው ፣ እግዚአብሄርንም ማገልገል ይችላል።” በማለት ይመሰክሩላችኇል።የሚሉ እና ሌሎችም ናቸው።በስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ቃለምእዳን ስርዓተ ክዋኔው ከተፈጸመ በኇላ የሚያስተላልፈውን ‹‹መልእክት›› የሚያሳይ ሲሆን በአጠቃላይ ዲያቆናቱ ለአገልግሎት የሚበቁበትን ሐይል ተጎናጽፈው ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው የሚጠቁም ነው።።





*ዲያቆናቱ ቃለምእዳን ሲቀበሉ*

አቡነ ቀውስጠስ የዲቁናውን ስልጣን ሰጥተው እንዳጠናቀቁ ሁላቸውንም ባረኳቸው። ከዚያም ቀጣዩ ስርአት የሆነው ዲያቆናቱ ስልጣኑን ከተቀበሉበት ቦታወደ ቅድስቱ በማለፍ በወንዶች መቆምያ በኩል ሆነው ሥርዓተ ቅዳሴውን እንዲከታተሉ የተደረገው ስርአት ነው። በስርዓተ አምልኮ ጊዜ የወንዶችና የሴቶች መቆምያ ቦታ የተለያየ መሆኑ ወንዶች ሴቶችን ሴቶች ደግሞ ወንዶችን በመመልከት ሐሳባቸው ወደሌላ አቅጣጫ እንዳይወሰድና እንዳይበታተን፣በሙሉ ልባቸው እግዚአብሄርን ማምለክ እንዲችሉ ነው።።

በስርአተ ቅዳሴው መካከል ላይ በቅዳሴው ሲሳተፉ የነበሩት ቄስ ከቅድስተ ቅዱሳኑ በመውጣት በመስቀላቸው ባረኳቸው። ለእለቱ የተመረጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ (ወንጌል) ተነበ ካበቃ በኋላ ወንጌሉን ዲያቆናቱ እና ምእመናን እንዲሳለሙ ተደረገ። ወንጌሉን የመሳለማቸው ዓላማ የተነበበውን የእግዚአብሔር ቃል አምነው መቀበላቸውን የሚያመለክት ነው።

ልክ ቅዱስ ቁርባን ወይም ዕርገት ሊወርድ ሲል ከሌሎች ቆራቢዎች ቀድመው ፊት ለፊት ተስልፈው እንዲቆሙ በማድረግ ለቁርባን አዘጋጇቸው። እርገት ወርዶ ቅዱስ ቁርባን ሊቀበሉ ሲሉ ከነጠላቸው በላይ የክህነት ካባ አምጥተው አለበሷቸው። ይህም የሚያመለክተው ስልጣነ ክህነት መቀበላቸውንና ለዚያም ክብር መብቃታቸውን ነው።

ስጋ ወደሙን ተቀብለው ወደቦታቸው ሲመለሱ ጸበል እየተቀዳ ተሰጣቸው። ያንን ከጠጡ በኋላ አፋቸውን በነጠላቸው ሸፍነው ቆሙ። ስርዓተ ቅዳሴው እንደተጠናቀቀ ዲያቆናቱ ከቤተ መቅደስ በመውጣት በመጠለያው ስር ተቀምጠው ፃዲቅ (ዳቦ) ቀመሱ። አንድ ሰው ቆርቦ ከሰዎች ጋር ከመነጋገሩ በፊት ከቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሳይወጣ እህል በአፉ መቅመስ ያለበት ስጋወደሙን በተቀበለበት አፉ ወሬ ማውራት በሰውነቱ ውስጥ የሰረጸውን ቁርባን ማቅለል፣ ክብር አለመስጠት ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በቤተክርስቲያን ውስጥ ገብቶ የተቀደሰበት እህል(ጸበል ጸዲቅ) መቅመስ በረከት ነው ተብሎ ይታመናልና በረከቱንም ለመካፈል ነው። እንዲሁም የቁርባኑን ክብር ያጓድላል ተብሎ ስለሚታመን ስጋ ወደሙን ተቀብለው ወደቤታቸው ሲሄዱ እንደ ወትሮው ሆኖ የመዋል ልማድ የተከለከለ በመሆኑ አብዝቶ መብላት እና መጠጣት፣ ገላን መታጠብ፣ ምራቅ መትፋት፣ረጅም መንገድ መሄድ፣ ከበሉትና ከጠጡት ላይ ማትረፍ ፣ ማልቀስ ፣ከባድ ስራ መስራት፣ የቆረቡበትን ልብስ መቀየር… አይፈቀድም። በክዋኔው ላይ ከመጀመሪያ አንስቶ አስከመጨረሻ ድረስ ስርአቱ የተቀነበበበት ቅርጽ የክዋኔውን ‹‹ፍሬም›› የሚያሳይ ሲሆን ይህም በመጀመሪያ ፣መካከል እና መጨረሻ ላይ የተፈጸሙትን የክዋኔ ገጽታዎች ይጠቁማል።

### 5.1.3 ድህረ ስርዓተ ክዋኔ

ከዲቁና ስልጣን አሰጣጥ ስርአት ጋር ተያይዞ ዲያቆኑን እና ስልጣኑን በተመለከተ ትኩረት የሚሰጥባቸው የተለያዩ ስርአቶች አሉ።አንድ ግለሰብ ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ስልጣነ ዲቁናን ከተቀበለ በኋላ ወዲያው ወደ ዋና አገልግሎት አይገባም። ቅዳሴ ለመቀደስ እና የተለያዩ ምልዓት ያላቸውን የዲቁና ተግባር ለመፈፀም ምስጢር ማየት አለበት። ምስጢሩን የሚያየው ዲቁናውን እንደተቀበለ ወዲያው አይደለም። ምስጢር ያላየና ሙሉ አገልግሎት ያልሰጠ ‹‹ንፍቅ ዲያቆን›› ይባላል። ትርጉሙም ተጨማሪ ፣ረዳት ማለት ነው።

ንፍቅ ዲያቆን ዋና ዲያቆን እስኪሆን ድረስ ጸበል ወደ ቤተመቅደስ ማስገባት እና ለሰዎች መቅዳት፣ ከቤተልሄም ወደ ቤተ መቅደስ ሲመጡ እና እግዚኦ ሲባል ቃጭል መምታት‹‹ፀልዩ በእንቲያሁ›› ብሎ ወንጌል በማንበብ አገልግሎት ይሰጣል።

በስርዓተ ክዋኔው ላይ ዲያቆናቱ እንደተሰጣቸው ቀኖና አይነት (ፆም፣ ፀሎት፣ ስግደት... ሊሆን ይችላል) ፈፅመው ከጨረሱ በኋላ ምስጢር የማየት ሂደት አለ። ይህንን ለማድረግ በቅድሚያ ለቤተክርስቲያኑ አስተዳደር “ምስጢር ማየት እፈልጋለሁ” በማለት ማስፈቀድ አለበት። ምስጢር የሚታየው ስጋወደሙ በሚዘጋጅበት በቤተልሄም ውስጥ ነው። ቤተልሄም የሚሰራው በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በስተምስራቅ አቅጣጫ ነው።ይህ ስጋወደሙ የሚዘጋጅበት ቤት “ቤተልሄም” የሚል ስያሜ የተሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በቤተልሄም ከተማ በመሆኑ ሲሆን ትርጉሙም የእንጀራ ቤት ማለት ነው። ቤተልሄም ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘበት በመሆኑ የእርሱ ስጋና ደም የሚዘጋጅበት ቤት በቤተልሄም ይመሰላል። ምስጢሩ ይህ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘች (የወለደች) ድንግል ማርያም በመሆኗ ቤተልሄም የማርያም ምሳሌ ናት ተብሎ ይታመናል። በቤተልሄም ምስጢሩን የሚያሳዩት ቄሰገበዙ እና ሊቀ ዲያቆኑ ናቸው።

ዲያቆኑም ምስጢራትን ካየ በኋላ ለማንም መናገር የለበትም። ምክንያቱም ምስጢር ነውና። መነጋገር ያለበት ምስጢር ካዩት ዲያቆናት ጋር እንጂ ንፍቅ ዲያቆን ከሆኑት( ምስጢር ካላዩት) ጋር እንኳ ጋር ማውራት አይችልም።ይህንንም ይጠብቅ ዘንድ ሊቀ ዲያቆኑ እና ቄሰ ገበዙ ቃል ያስገቡታል።ምስጢሩን ሳይጠብቅ የእግዚአብሄርን ክብር አጉድሎ ቢገኝ እንደ አሮንና እንደ ኤሊ ልጆች የእግዚአብሄር ቁጣና መቅሰፍት እንደሚወርድበት አበክረው ይነግሩታል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ምስጢሩን ጠብቆ ይኖራል። ምስጢሩን እንዳየ ከካህናት ጋር

አብሮ መሶበ ወርቅን አክብሮ ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዳል፡፡ መሶበ ወርቁን አክብረው ወደ ቤተ መቅደስ ለመሄድ ሶስት ካህናት ያስፈልጋሉ፡፡ አንደኛው ዲያቆን ከፊት ለፊት ሆኖ ቃጭል የሚመታ ሁለተኛው ደግሞ መሶበ ወርቅን የሚያከብር (የሚሸከም) ሶስተኛው ቄስ ደግሞ አከባቢውን የሚያጥን ነው፡፡ ዲያቆኑ ቃጭሉን እየመታ ሲሄድ የቃጭሉ ድምፅ የሚወክለው የዮሃንስን ድምፅ ነው፡፡ ይህ ድምፅ በመጽሐፍ ቅዱስ ማቴ (3፡3)፣ሉቃ(3፡3-4) “የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ጥርጊያውን አቅኑ” ተብሎ የተጠቀሰውን የዮሃንስ ስብከት የሚያስታውስ ሲሆን ከዮሃንስ ቀጥሎ ኢየሱስ ከማርያም ተወልዶ መምጣቱንና ማስተማሩን ለማመልከት መሶበ ወርቁን ያከበረው(ወይኑንና ህብስቱን የተሸከመው) ዲያቆን ከቃጭሉ ድምፅ ተከትሎ ወረ ቤተመቅደስ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃጭሉ ድምፅ ማንቂያ ነው፡፡ በዚያ በኩል የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋና ደም ከቤተልሄም ወደ ቤተመቅደስ ተዘጋጅቶ ሲገባ ለክብሩ መገለጫ ህዝበ ክርስቲያኑን በዚያ አካባቢ ጥንቃቄ አድርገው እንዲፀልዩ ለማድረግ ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ ወደ ቤተመቅደስ ሲገቡ ዲያቆኑ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ከሆነ ያንኑ እንደለበሰ፣ነጠላ ለብሶ ከሆነ ደግሞ መስቀለኛ አጣፍቶ መልበስ አለበት እንጂ እንደፈለገው ለብሶ አይገባም፡፡ይህም የሆነበት ምክንያት የቤተክርስቲያን ቀኖናው ወገቡን ታጥቆ ወይም አደግድጎ ወደቤተመቅደስ ይግባ ብሎ ስለሚያዝ ነው፡፡ ይህ የማይገደፍ ህግና ስርዓት ነው፡፡ ስርዓተ ቅዳሴውን ተከታትሎ ከፈፀመ በኋላ እንደ ሌሎች ካህናት እሱም ይቆርባል፡፡ የሚቆርበውም ቤተ መቅደስ ውስጥ ሆኖ ነው እንጂ ምእመናኑ የሚቆርቡበት ቦታ ላይ ሆኖ አይደለም፡፡ ከዚህ በኋላ በቤተመቅደሱ ውስጥ ያሉት ሌሎች ምስጢራት ይነገሩታል፡፡ እስከ ሶስት ቀን ድረስ እየገባ ሌሎች ስርአቶችን ሁሉ በጥንቃቄ እንዲያይ ይደረጋል፡፡ ለሶስት ቀንም እንዲቆርብ ከተደረገ በኋላ ቤተመቅደስ ውስጥ እንዲገባና እንዲያገለግል ይፈቀድለታል፡፡ሶስት ቀን እንዲቆርብ የሚደረግበት ምክንያት የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ሶስትነት ምሳሌን ለማመልከት ነው፡፡ ከዚህም በኋላ መስቀል ይዞ ዋና ዲያቆን ሆኖ መቀደስ ይችላል፡፡ በፊት ተከታይ (ንፍቅ) የነበረው ዲያቆን አሁን ዋና ዲያቆን ይሆናል ማለት ነው፡፡



*ከንፍቅ ዲያቆንነት ወደ ዋና ዲያቆንነት ተሸጋግሮ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ዲያቆን*

ዋና ዲያቆን ሰራዩ ዲያቆን ይባላል፡፡ ሰራዩ ከሆነ በኋላ ራሱን ችሎ መቀደስ ፣ ማወደስ፣ ደሙን ማቀበል ይችላል፡፡ አገልግሎቱ በተግባር ታይቶለት ምስጢሩን አይቷልና በቅዳሴው ስርዓት ሙሉ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡ ይህ ሲባል ግን በቤተ መቅደስ ውስጥ ያሉ ማንኛውንም ተግባር የማከናወን ስልጣን አለው ማለት አይደለም፡፡ በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዳይፈፅም የተከለከሉ የተለያዩ ድርጊቶች አሉ፡፡ እነሱም ታቦት (በንበሩን) መንካትና መዳሰስ ፣ከመንበሩ ላይ ጧፍም ሆነ እጣን ማስቀመጥ እና ማንሳት አይችልም፡፡ ጥናውን ወገቡ ላይ ይዞ ፍም ያመጣል እንጂ ጫፉን ይዞ አያጥንም፡፡ እጣንም ወደ ጥናው ውስጥ መጨመር አይችልም፡፡ በዚህ ሁኔታ የቅስና ስልጣን እስኪሰጠው ድረስ በእነዚህ አገልግሎቶች ፀንቶ ይቆያል የሚል ገለፃ የበዓታ ለማርያም ቀሲስ ዓለም እሸት ግንቦት 16፣ 2003 ዓ/ም በተደረገው ቃለመጠይቅ ሰፊ ገለጻ ሰጥተውኛል፡፡

ዲያቆናት ስልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኋላ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ልማዳዊ አኗኗር እንደማንኛውም ግለሰብ በራስ ፈቃድና ምኞት ተገዝተው የፈለጉትን ማድረግ የሚችሉ ሳይሆን በህግና በስርዓት ተወስነው ይኖራሉ፡፡ ይህንን ካላደረጉ ክህነታቸው ይሻራል፡፡ ዲያቆናት ከማህበረሰቡ ተለይተው የሚታዩበት ገፅታቸውን ለማመልከት ዲያቆን ዮሃንስና ዲያቆን ፅጌ ከራሳቸው የአኗኗር ልማድ በመነሳት የገለፁልኝ ጉዳዮች በአጠቃላይ የሚከተሉትን

መስመሮች የያዙ ናቸው። እነዚህም ጭፈራ ቤት አለመሄድ፣ከሴት ጋር አለመገናኘት(ዝሙት አለመፈፀም) ፣ አለመስከር፣ትሁትና ታጋሽ መሆን፣አለመጣላት፣በጊዜ ወደ ቤት መግባት (አለማምሸት)፣አልባሌ ቦታ አለመገኘትና ሌሎችም በማህበረሰባችን ዘንድ በጥሩ ስነምግባር ውስጥ በማይካተቱ ጉዳዮች ላይ አለመሳተፍ ናቸው። በአንፃሩ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ፣ የባህልና ወግ መገለጫዎች የሆኑን ለምሳሌ ለታላቅ ክብሮት መስጠት፣ መጠያየቅ፣ መከባበር፣ መረዳዳት፣ መቻቻል፣ ትምህርታቸውን በአግባቡ መከታተል… አዘውትረው የሚተገብሯቸው ናቸው። ዲያቆናት በጭፈራ ቤት ተገኝተው ሲጠጡ፣ ሲሰክሩ እና ክህነታቸውን አቅለው ቢገኙ፤ እንኳን በእግዚአብሄር ዘንድ በማህበረሰቡ ዘንድ ነውር መሆኑን ለማመልከት “ ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ ዋጋ የለውም ” በማለት ተርተውባቸዋል።

## 5.2 የቅስና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ

### 5.2.1 ቅድመ ሥርዓተ ክዋኔ

የቅስና ሥልጣን ለመቀበል የሚያስችሉ ሁለት ገጽታዎች አሉ። የመጀመሪያው ገጽታ ግለሰቡ ዲያቆን ከሆነ በኋላ በዲቁናው ማሟላት የሚጠበቅበትን መስፈርቶች አሟልቶ በሥልጣኑ ምልዓት ያለው አገልግሎት በመስጠት ሚስት ማግባት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በድንግልና ወደ ገዳም በመግባት መመንኮስ እና የክህነትን ትምህርት በመማር ቄስ መሆን ነው። የበዓታ ለማርያም የስብከተ ወንጌል ሃላፊ ቀሲስ ዓለምእሸት አንድ ዲያቆን ቄስ ሆኖ ለማገልገል ሚስት ማግባት እዳለበት ሲገልፁ የሚከተለውን ብለዋል።

> *አንድ ካህን ሚስት የሚያገባው በዲቁና እያገለገለ ሳለ ሆኖ ልክ ሚስት አግብቶ ከሰላሳ ዓመት በኋላ የቅስና ስልጣን መቀበል ይችላል። የቅስናን ስልጣን ለመቀበል ይህ ዲያቆን ጋብቻውን በስርዓተ ተክሊል እና በቅዱስ ቁርባን መፈፀም አለበት እንጂ አለማዊ ጋብቻን አግብቶ ቄስ መሆን አይችልም። ማግባት ያለበትም አንዴ ነው። ከዚህ በፊት ያላገባ፡ያልወለደ መሆን አለበት። (ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም)*

ቀሲስ ዓለም እሸት ከዚህ መስፈርት በተጨማሪም የተለያዩ ጸሎቶችን ቅዳሴዎችን ማወቅ እንዳለበትና እነሱም ኪዳን፣መስተቁም፣ሊጦን ፣የተባሉን በቃል መያዝ እንደሚገባ አስረድተውኛል።

የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የትርጓሜ መፃህፍት መምህር ደጉዓለም ካሳ ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገው ቃለመጠይቅ ላይ አንድ ካህን የቅስና ስልጣን ለመቀበል በቅድሚያ ለዚህ ስልጣን የሚመረጥበት ስነምግባር ሊኖረው እንደሚገባ ፣ ለህዝብ የተለያዩ ትርጓሜዎችን የሚያሳውቅበት የዕውቀት ደረጃው ከፍ ያለ ፣ብሉይና ሐዲስን ጠንቅቆ በማወቅ በተለያዩ ቋንቋዎች ተጠቅሞ ሊያስተምር የሚችል መሆን እንዳለበት ገልፀዋል። ከዋናው ትምህርት ጋር ተያይዘው የሚታዩ እንደ አለመጠጣት፣አለመስከር፣ አለመቆጣት፣ አለመማታት ፣ ለጸብ አለመቸኮል ዋና ዋና መመዘኛ ነጥቦች መሆናቸውንም አክለው አስረድተዋል።

### 5.2.2 ስርዓተ ክዋኔ

በፍትሃ ነገስት አንቀጽ 6፣211 ላይ ዲያቆናት ሰላሳ አመት ከሆናቸው በኋላ የቅስናን ስልጣን መቀበል እንደሚችሉ ተገልጧል።ይህ ትውፊት የቤተክርስቲያን ቀኖና ሆኖ እያገለገለ የሚገኝበት ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ በሰላሳ አመቱ ተጠምቆ አገልግሎት መጀመሩ ለስልጣነ ክህነት አገልግሎት መነሻ ይሆን ዘንድ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው። ስልጣነ ክህነቱን ይሰጥ ዘንድ የተፈቀደለት ኤጲስ ቆጶስ ነው። ቅስና መቀበል የሚፈልግ ዲያቆን ራሱን ከተለያየ አቅጣጫ ከመረመረና ለቅስና ህይወት ከተዘጋጀ (ሚስት ካገባ ወይም ከመነኮሰ) በኋላ አገልግሎቱን በማስመስከር ወደ ጳጳስ ዘንድ ሄዶ " ቅስና ስጡኝ " በማለት መጠየቅ ይችላል። ጳጳሱም ከላይ በቀረበው ክፍል ላይ ያሉትን መስፈርቶች ማሟላቱን፣ የዚህን ዲያቆን ሃይማኖታዊ እና ስነምግባራዊ እሴቶች ጊዜ ወስደው መርምረው ካጠናቀቁ በኋላ የቅስናውን ሥልጣን መስጠት ይችላሉ።

ሥርዓቱ የሚፈጸምበት ቦታ (መቼት)በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው። ዲያቆኑ ቅስና ለመቀበል ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጣ እንደ ዲያቆናት ሁሉ ቅድመ ዝግጅቶችን መፈፀም አለበት። በስርዓተ ክዋኔው ወቅትም ልክ እንደ ዲቁናው ሥርዓት ለቅስና የሚያበቃ ጸሎት በሥርዓት መፅሐፉ ላይ ተፅፎ ይገኛል። ፀሎቱ በኦሪትም ሆነ በሃዲስ ክርስቶስ ለሃዋርያት ሥልጣነ ክህነትን እንዴት እንደሰጣቸው እና የሚሰጡትን አገልግሎት የሚገልፅ ነው።

ጳጳሱ እና ዲያቆናቱ ክህነቱ በሚሰጥበት ቦታ ላይ በምስራቅ እና በምዕራብ አቅጣጫ በመዘዋወር ፀሎት ያደርሳሉ። ይህም በዲቁናው ሥርዓት ላይ እንደተገለፀው ክርስቶስ

ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ከሰሜን ወደ ደቡብ እየተዘዋወረ ማስተማሩን ለማመልከትና እነሱም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የእሱን አርአያ ተከትለው መንዝ እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነው አቅጣጫቸውን እየለዋወጡ የሚዟዟሩበትን ቦታ ወይም ቤተ መቅደስ እንደ አለም አድርገው ይቆጥራሉ፡፡

በስርዓተ ክዋኔው ላይ በፍትሃ ነገስት አንቀጽ ስድስት ላይ በተጠቀሰው መሰረት ዲያቆኑን እንዲንበረከክ በማድረግ የአንብሮተ ዕድ ስርአት ( እጃቸውን በላያቸው ላይ መጫን) ይፈፅማሉ፣ቀሳውስትም ቆመው ይዳስሱታል፡፡ ይህም ስልጣኑን የመስጠት፣የማስተላለፍ እና የመባረክ መገለጫ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ላይ እንዲያድር ለማድረግ የሚፈፀመው ስርዓት "ንፍሀት" ሲሆን አሰጣጡም ‹‹ንሳ መንፈስ ቅዱስ››በማለት በተቀባዮች ፊት ላይ እፍ በማለት ነው፡፡ ይህን ስርአት የሚጠብቁትም ክርስቶስ ለሐዋርያት ስልጣነ ክህነትን ሲሰጣቸው መንፈስ ቅዱስን እፍ ብሎ እንዲቀበሉ በማድረጉ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ‹‹ቤተክርስቲያንን እንድታገለግል ስልጣን ተሰጥቶሀል›› በማለትም መቀበሉን ያረጋግጡለታል፡፡ ቀጥሎም እግዚኦ መሃረነ ክርስቶስ አስራ ሁለት ጊዜ እንዲሉ እና አቡነ ዘበሰማያትን እንዲደግሙ ይደረጋል ፡፡ ከዚህ በኋላ ጳጳሱ ቃለ ምዕዳን ይሰጣሉ፡፡ ይህም ክህነቱን እንዳይሽር፣ ሀይማኖቱን እንዲጠብቅና ስልጣኑ በሚያዘው ህግና ስርአት መሰረት መንዝ እንደሚጠበቅበት፣ እንዲሁም ሰውንና እግዚአብሄርን ማገልገል እንዳለበት የሚጠቁም ነው፡፡ዲያቆን የነበረው ግለሰብ ከዚህ ስርዓት በኋላ የቅስና ስልጣን ተቀብሏልና የዚህ ስልጣን(ማዕረግ) መገለጫ የሚሆን ነጭ ጥምጣም በራሱ ላይ ይጠመጥማል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወደ ሌላ የሥልጣን እርከን እስኪሻገር ድረስ ሻሽ መጠምጠም የተለመደ ነው፡፡ ነጩ ጥምጣም የሚዘጋጅበት ጥሬ እቃ ጥጥ ሲሆን ተዘጋጅቶ ሲታይ የነጠላና ጋቢ አይነት ዲዛይን ያለው ነው እንጂ ለዚህ አላማ ተብሎ በሌላ ቀለምና ቅርጽ የሚሰራ አይደለም፡፡ ጥምጣሙ በተግባር ላይ ሳይውል እንዲሁ ተዘርግቶ ሲታይ ስስ ነው፡፡ በተለምዶ "ሻሽ" ይባላል ፡፡ይህ ሻሽ ቀለሙ በጣም ነጭና ንፁህ መሆን አለበት፡፡ ሻሹን ለማስጌጫ ተብሎ ነጭም ሆነ ሌላ አይነት ቀለም ያለው ጥለት እንዲኖረው አያስፈልግም፡፡ በዚህ ሻሽ ጥምጣም ሰርተው በራሳቸው ላይ የማድረጋቸው ትርጉም የረድኤተ እግዚአብሄር መገለጫ ተምሳሌትነትን የያዘ ነው ፡፡ ይህ ገፅታ ሀገረሰባዊ ልብስን የሚያመለክት ሲሆን ይዘቱም አንድ ካህን ከሌላው ማህበረሰብ ተለይቶ የሚሰጠውን ክብር፣ የሥራ ድርሻውን ወይም አገልግሎቱን፣ እንዲሁም አንድ ምእመን ካህን መሆኑን ለይቶ እንዲያውቀውና አስፈላጊውን

መንፈሳዊ እርዳታ ለመጠየቅ እንዲችል የሚጠቅም ነው። ከዚህ ስርዓተ ፍፃሜ በኋላ የቅስናውን ስልጣን የተቀበለው ካህን ወደ ቤተመቅደስ ውስጥ በመግባት ስርዓተ ቅዳሴውን ተከታትሎ ስጋ ወደሙን እንዲቀበል ይደረጋል ።



*ካህናት ጥምጣማቸውን አድርገው ወረብ ሲያቀርቡ*

### 6.2.3. ድህረ ስርዓተ ክዋኔ

የቅስና ስልጣን ከተሰጠ በኋላ ኤጲስ ቆጶሱ ስልጣኑን ለተቀበለው ካህን ‹‹..... ከዚህ ቀን ጀምሮ ቅስና ተቀብሏል በማለት›› የማረጋገጫ ደብዳቤ ይሰጡታል። ደብዳቤውን እንደተቀበለ ግን አገልግሎት ይጀምራል ማለት ሳይሆን እስከ አርባ ቀን ድረስ እንዲያም፣ እንዲፀልይና እንዲሰግድ ቀኖና ይሰጠዋል። ቀኖናው በአርባ ቀናት እንዲወሰን የተደረገበት ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀናት በገዳመ ቆሮንጦስ ጾም የጸለየ እና በህማማት መስቀል ከተቀበላቸው መከራዎች ውስጥ የተገረፈው አርባ ጊዜ በመሆኑ ያንን ለማስታወስ ነው። ይህን እንዳጠናቀቀ ህዝበ ክርስቲያኑን የሚባርክበት የእጅ መስቀል በማምጣት በመንበሩ ላይ ለሰባት ለአስራ አራት ወይም ለሃያ አንድ ቀናት እንዲጸለይበት እና እንዲቀደስበት ያደርጋል በማለት ቀሲስ አለምሸት ሲገልጹ ሊቀካህናት ክንፈገብርኤል አልታዩ እነዚህን ቁጥሮች ትርጓሜ በሰባት ቤት የተወሰኑበትን ምክንያት ሲገልጹ በቤተክርስቲያን ስርአት አንድ ሱባኤ ሰባት ቀናት አስራ አራት ሲሆኑ ሁለት፣ ሃያ አንድ ሲሆኑ ደግሞ ሶስት ሱባኤ ማለት ነው።ቀናቱ ሰባት መሆናቸው የሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው በማለት ነው።እንደዚሁም መጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ ቤቷን ሰራች ሰባቱ ምሰሶዋንም አቆመች በማለት ሲገልጽ ጥበብ የኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቤት የቤተክርስቲያን፣ ምሰሶ የተባሉት ደግሞ የምስጢራተ ቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን

ሲመሰርት እነዚህን ምስጢራት ያካተተ መሆኑን የሚያመለክት ነው ሲሉ አክለው ገልጸዋል፡፡ ይህ የቁሳዊ ባህል መገለጫ የሆነ የእጅ መስቀል የሚዘጋጅበት ጥሬ እቃ ከእንጨት፣ ከወርቅ፤ ከብር እና ከነሀስ ሊሆን ይችላል፡፡ካህናት የእጅ መስቀል መያዛቸው አንድም ለመባረኪያ ሲሆን ሌላው ደግሞ ክርስትናን መስበክ ነው፡፡


ካህናት የአገልግሎት ሥራቸውን ሲጀምሩ በአለባበስ፣ በአነጋገር፣ በአካሄድ፣ በአጠቃላይ በአኗኗር ዘይቤያቸው ሁሉ ክህነታቸውን የሚያንጸባርቅ መሆን እንዳለበት ስርአቱ ስለሚያዝ ህይወታቸው በጥንቃቄ የተሞላ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአኗኗር ልማዳቸው ከሌላው ማህበረሰብ መካከል እንዲለዩ የሚያደርጋቸው ሀገረሰባዊ የክህነት አለባበስ ስርአታቸው ሲሆን ይህም እስከ ቁርጭምጭሚታቸው ድረስ ቀሚስ መልበሳቸው በዚያ ላይ ነጠላ ደርበው የእጅ መስቀል ይዘው በራሳቸው ላይ ደግሞ ጥምጣም ወይም ቆብ ማድረጋቸው ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሚለብሱት ቀሚስ ጥቁር ቀለም ያለው ሲሆን አልፎ አልፎ ደግሞ ነጭ ይለብሳሉ፡፡ ቀሚሱ የስጋንና የነብስን ንፅህና የሚያመለክት ሲሆን ጥቁሩ የሃዘን ምሳሌ ሆኖ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ ለማሰብ ነው፡፡ ነጭ ሲለብሱ ደግሞ ዘመነ ፍስሐ ማለትም በትንሳኤና በተለያዩ ክብረ በዓላት ጊዜ ደስ መሰኘታቸውን ለመግለፅ ነው፡፡ ቆቡ ከመነኩሴዎች ይለያል ይህም የካህናት መሃሉ ክፍት ሲሆን የመነኩሴዎች ደግሞ ድፍን ነው፡፡ ይህ መሆኑ ማዕረጋቸውን ለመለየት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የካህናት መሃሉ ክፍት መሆኑ በትዳር አለም ውስጥ ያሉ መሆናቸውን ሲያመለክት የመነኩሴዎች ድፍን መሆኑ ደግሞ ድንግልናቸውን ለማመልከት ነው ሲሉ ሊቀ ካህናት ክንፈገብርኤል አልታዬ ገልጸውልኛል፡፡ እንዲሁም ያገቡ ካህናት ካላገቡት የሚለዩት ሱሪና ካፖርት በላዩ ላይ ደግሞ ነጠላ ደርበው በመልበሳቸው እና ሻሽ በመጠምጠማቸው ነው፡፡ከስርአተ ክዋኔው በኋላ ያለው ሌላ ገጽታ “አባ” የሚል ቅጽል ስም የሚሰጣቸው ሲሆን ለምእመናን አባት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ካህናት በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተደማጭነት፣ ተቀባይነት እና ከበሬታ አላቸው፡፡ ምክንያቱም "ካህን ሲያዩት ሰው ይመስላል፤ ፀበል ሲያዩት ውሀ ይመስላል" ተብሎ እንደተነገረላቸው አገልግሎታቸው የነፍስና የስጋ ደህንነትን የሚያሰጥና በሰማይም በምድርም የማሰርና የመፍታት ስልጣን ያላቸው በመሆናቸው ነው፡

ካህናት በማህበረሰቡ ውስጥ ሲኖሩ ከሚያሳዩት ሀገረሰባዊ ልማድ መካከል ሌላው የሆነው ከምዕምናኑ ጋር ሲገናኙ ሰላምታ የሚለዋወጡበት መንገድ ነው፡፡ይህም በመጨባበጥ ሳይሆን

መስቀል በማሳለም ነው፡፡ ይህ የሰላምታ ልውውጥ የሚከናወነው ምዕምናኑም ወደ ካህኑ በመቅረብ "ይፍቱኝ አባ እገሌ" ሲሉ እሳቸውም እግዚአብሄር ይፍታህ/ሽ/ በማለት በመስቀሉ ይባርካሉ፡፡ምዕመናኑ ካህናቱን በመንገድ ላይም ሆነ በሌላ ቦታ ሲያገኙ ለመባረክ ወደ እነሱ የሚሄዱት እግዚአብሄር ይፍታሽ/ህ/ መባልን ስለሚፈልጉና ባርኮቱ ከክፉ ነገር ይጠብቀናል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ምዕመናኑ በአለም ውስጥ ሲኖሩ የተለያዩ ክፉ ድርጊቶችን ሊያከናውኑ ይችላሉና ወደ ካህናቱ ሄደው ሲባረኩም በውስጣቸው ያለ ስሜት "አውቄም ሆነ ሳላውቅ የሰራሁትን ኃጢያት ይቅር ይበሉኝ" የሚል ኑዛዜን ያዘለ ነው፡፡

ካህናት ስልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኋላ የህዝበ ክርስቲያኑን ስነምግባር በመቆጣጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ይህን ተግባር የሚፈጽሙት የመቆጣጠርና የመግራት ሃላፊነትን ስለተቀበሉ ነው፡፡ይህን ሲያደርጉም ባህላቸውና ወጋቸውን ጠብቀው ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ይችሉ ዘንድ ዘወትር በማሳሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ በአለባበስ፣ በአካሄድ፣ በአነጋገር እና በሌሎችም የሀገርን ትውፊትና ልማድ በመጠበቅ ረገድ ትክክለኛ ስርአቶች ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ለማስፈጸም ጥረት ያደርጋሉ፡፡ እነዚህን አለመፈጸም እግዚአብሄር የማይከብርባቸው መንገዶች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ በረከትን እንደሚያሳጣና የእግዚአብሄር ቁጣ ሊነሳ እንደሚችል ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ለአንድ በመወሰን ጋብቻን በቅዱስ ቁርባንና በስርዓተ ተክሊል መፈፀም እንደሚገባና የተፃፈውን ስርዓት ዘወትር በመግለፅ ሲያስረዱ በተዘዋዋሪ ዝሙት አትፈፅሙ፣ እግዚአብሄር በመረጠላችሁ አንድ ሰው ብቻ ጸንታችሁ ኑሩ ሲሉ ከቀሳፊው የኤድስ በሽታ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ያደርጋሉ፡፡



*በስርአተ ተክሊል ጋብቻቸውን የፈጸሙ ሙሽሮችን አርአያ በማድረግ ምእመናን አንድ ለአንድ ተወስነው እንዲኖሩ ካህኑ ምክር ሲሰጡ*

በሌሎችም ማህበራዊ ጉዳዮች ለምሳሌ የተጣሉትን በማስታረቅ፣ የበደሉትን ይቅር በማለት፣ ንሰሀ በመስጠት ዳግመኛ ወደ ጥፋት እንዳይገቡ በመምከር፣ የነፍስ ልጅ በመያዝ በመንፈሳዊ ህይወት እንዲጠነክሩ በማድረግ፣ ሰው ሲሞት ኑዛዜን በመቀበል እና ኑዛዜያቸው ተፈጻሚነትን እንዲያገኝ በማድረግ የሃገራችንን የአኗኗር ልማድ ገጽታ በጉልህ አንጸባርቀው ያሳያሉ። ካህናት ክህነታቸው እንዳይፈርስ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። አንድ ሚስት ብቻ እንድትኖራቸውም ይፈቀዳል። አጋጣሚ ሚስታቸው ብትሞት ልክ በሞተች በአርባኛው ቀን መመንኮስ ይኖርባቸዋል። ሳይመነኩሱ ቀርተው ሌላ ሚስት ቢያገቡ ክህነታቸው ይፈርሳል።

## 5.3 የኤጲስ ቆጶስ ስልጣን አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔ

### 5.3.1 ቅድመ ስርዓተ ክዋኔ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የኤጳስ ቆጳስነትን ሥልጣን ለመቀበል ወይም ለማግኘት የሚያስችሉ አቅጣጫዎች ሁለት ናቸው።

የመጀመሪያው አንድ ግለሰብ ለዲቁና የሚያበቁትን መስፈርቶች (የትምህርትና ስነምግባር) አሟልቶ የዲቁናን ሥልጣን ተቀብሎ፤ በቅድስና ሲያገለግል ኖሮ ንፅህናውን ጠብቆ ሚስት ሳያገባ፣ ከማንም ጋር ሳይነካካ ገዳም ሄዶ በመመንኮስ ካህን (ቄስ) መሆን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የዲቁናን ሥልጣን ሳይቀበል ነገር ግን ንጽህናውን ጠብቆ፣ ገዳም ገብቶ፣ ሥርዓተ ምንኩስናውን ፈፅሞ ከመነኮሰ በኋላ ዲያቆን እና ካህን (ቄስ) መሆን ናቸው። በሁለቱም አቅጣጫዎች ውስጥ ድንግልና፣ምንኩስና እና ክህነት አይቀሬዎች ናቸው። ክህነቱ ለአገልግሎት፣ምንኩስናው አለምን ንቆ ለመተው ሲሆን ድንግልናው ደግሞ ለንጽህና ሃዋርያትን እና ክርስቶስን ለመምሰል ነው። ከሊቀካህናት ክንፈገብርኤል ጋር ባደረግሁት ቃለመጠይቅ በድንግልና ጳጳስ መሆን ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተጀመረ ስርአት መሆኑን ነው።ከዚያ በፊት ጳጳሳት ሚስትም ልጅም ነበራቸው።ጳጳሳቱ ትዳር ይዘው ሙሉ በሙሉ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት መፈጸም ባለመቻላቸው፣ ልጆቻቸውና ሚስቶቻቸው የአባታችን ሀብት ነው በማለት የቤተክርስቲያንን ንብረት በማቀርቀዛቸው እንዳያገቡ መከልከላቸውን ገልጸውልኛል።

ከዚህ መረዳት እንደምንችለው የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ሁለት ነገሮችን አጣምሮ መያዝን ይጠይቃል ማለት ነው። እነሱም ክህነት እና ምንኩስና ናቸው። አንድ ካህን ወይም መነኩሴ

የሆነ ግለሰብ እነዚህን “ሥልጣን” አጣምሮ ስለያዘ ብቻ የኤጲስ ቆጶስነትን ማዕረግ ያገኛል ማለት ሳይሆን በእነዚህ ውስጥ መጠናቀቅና መሟላት የሚገባቸው ሌሎች ሥርዓቶች፣ ትምህርቶች እና ሥነ ምግባሮች ሁሉ መፈጸም አለባቸው፡፡

የኤጲስ ቆጶስና ሥልጣን ላይ ለመድረስ ግለሰቡ የምንኩስናን ህይወት ብቻ አጣጥሞ መኖር የሚጠበቅበት ሳይሆን ከዝቅተኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የአስተዳደር ሥርዓት (አበምኔት) ውስጥ ማለፍ አለበት፡፡ ይህም ኋላ ቤተክርስቲያንን በአግባቡ ማስተዳደር እንደሚችል ያስመሰክርለታል፡፡ በፍትሃ ነገሥት እንደተደነገገው በምንኩስና ሥርዓት ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ገጽታዎች ከተለያዩ አባቶች ጠይቁ እንደተረዳሁት በሥርዓቱ ግንዘት እና ፍትሃት ይፈጸማል ፡፡ ይህ የሚያመለክተው ዓለምን ትተው ወደተለየ አኗኗር ዘዴ ውስጥ መግባታቸውን ነው፡፡ ይህ ሥርዓት የሚያመለክተው ሰዎቹ እንደሞቱ ተደርገው መቆጠራቸውን ነው፡፡የቀደመውን ዓለም ትተው አዲስ ህይወት መጀመራቸውን ለማመልከት ፀጉራቸውን ተላጭተው ቆብ ያደርጋሉ፡፡ ወይባ (ቢጫ) ልብስም (ቀሚስ) ይለብሳሉ፡፡ ለጽጽስና ማእረግ እስኪበቁ ድረስ ቀሪ ህይወታቸውን የሚያሳልፉት በገዳም ውስጥ በፆምና በፀሎት ነው፡፡

በድንግልና የመነኮሱ ይህንን ማዕረግ ማግኘት ይችሉ ዘንድ በገዳም መኖር፣ ማቅ መልበስ የሚጣፍጥ ምግብ ከመመገብ መቆጠብ፣ ሥጋን የሚመች ተግባር አለማከናወን፣ መፆምና መፀለይ መጻህፍትን በማንበብ መትጋት፣ዘወትር መልካም ሥራን የሚሰሩ ፣ ለዚህ አለም ኑሮ የማይጓጉ ወይም አለምን የተው፣ ምግባቸው ሁሉ ሰማያዊውን እንጂ ምድራዊውን የማያንፀባርቅ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ አንድ ቆሞስ ጳጳስ ለመሆን አራት አይና መሆን አለበት በማለት መምህር ደጉአለም ካሳ እና መጋቢ ጥበብ ቀሲስ ዓለምሸት ገልፀዋል፡፡ ብዙ የህይወት ልምድ እንዲኖራቸው እድሜያቸውም ከሃምሳ አመት በታች ባይሆን ይመረጣል፡፡ ይህን ሲሉም ብሉይንና ሐዲስን፣ቅዳሴውን ሁሉ ጠንቅቀው ማወቅ እንዲሁም በስነምግባርና በመንፈሳዊ ዕውቀት የበሰለ ሙያ ያላቸው መሆን የሚገባቸው መሆኑን (ግንቦት 16/2003 ዓ.ም) በተደረገው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

ከጤንነት አንጻር ኤጲስ ቆጶሳት ስልጣነ ክህነትን ይቀበሉ ዘንድ ማየት እና መስማት የተሳናቸው ፣ የሚዘነጉ፣ ጋኔን ያደረባቸው፣አማኒ ያልነበሩና ቆይተው የተጠመቁ መሆን የለባቸውም፡፡

### 5.3.2 ስርዓተ ክዋኔ



የኤጲስ ቆጶስና ሥልጣን ከዲቁና እና ከቅስና ስልጣን በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በመሆኑም ስልጣነ ክህነቱን ለመስጠት ከሁለቱ ስልጣኖች ከፍ ያለ አውድ ይጠይቃል፡፡ ስልጣነ ክህነቱ የሚሰጠው በሁለት ሊቀጳጳሳት ወይም በፓትሪያርክ ነው፡፡አንድ ቆሞስ( ከቅስና ማእረግ ከፍ ያለ፣ ከኤጲስ ቆጶስነት ማእረግ ደግሞ ዝቅ ያለ ለማእረገ ኤጲስ ቆጶስና የተዘጋጀ) የኤጲስ ቆጶስነትን ስልጣን ለመቀበል የምንኩስና ስርዓትን ከላይ በተገለፀው መሰረት ፈፅሞ ሰላሳ አመት በሞላቸው ምእመናን ደግሞ መመረጥ አለበት፡፡እድሜያቸው ሰላሳ አመት እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት ነገሮችን የሚያመዛዝን አእምሮ ደረጃ ላይ የሚደርሱበት እድሜ በመሆኑ ነው፡፡ በምርጫው ምእመናን እንዲሳተፉ የሚደረገው ሊያገለግላቸው፣ ሊመራቸው የሚችለውን ጳጳስ በአስተዳደር ብቃቱ፣ በጥሩ ስነምግባሩ በእውቀቱ ፣በህግ( ደንብ) ጠባቂነቱ መዝነው የሚበጃቸውን በመምረጥ ማቅረብ እንዲችሉ ነው፡፡ በስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔው ላይ ተገኝተው ሥልጣኑ የሚገባው ወይም የማይገባው መሆኑን መመስከር እንዲችሉ የስልጣን መስጪያው ቀን ሰዎች በሚሰበሰቡበት እሑድ እለት በስርአተ ቅዳሴ ላይ እንዲሆን በፍትሃ መንግስት አንቀጽ 5 እና በድስቅልያ አንቀጽ 27 ተወስኗል፡፡ ምርጫው የሚጠናቀቀው በምእመናን ብቻ ሳይሆን ጳጳሳት እና መንፈስ ቅዱስም እንዲመርጡ ይደረጋል፡፡ ጳጳሳት እንዲመርጡ ሲደረግ ለምሳሌ አስር ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ተፈልጎ ከሆነ ሃያ መነኮሳት ይቀርባሉ በኢትዮጵያ ያሉ ሁሉም ጳጳሳት ተሰብስበው ይመጡና ከሃያዎቹ መነኮሳት በተሰጣቸው ነጭ ወረቀት ላይ የመረጧቸውን አስር መነኮሳት ብቻ እንዲፅፉ ተደርጎ ወረቀቱ ይሰበሰባል፡፡ጳጳሳቱቆሞሳቱን ሲመርጡ የአስተዳደር ብቃታቸውን፣ስነምግባራቸውን፣ሐይማኖት ጠባቂነታቸውን፣እውቀታቸውን፣አስተማሪነታቸውን ሁሉ ከግምት በማስገባት ሰዎቹ ቢመረጡ ቤተክርስቲያንን እና ህዝቡን ምን ያህል መጠበቅ እንደሚችሉ በማረጋገጥ መሆኑን የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን ብፁእ አቡነ ጢሞቴዎስ ገልፀውኛል፡፡ለምርጫ የቀረቡት ቆሞሳት ለመጨረሻ ጊዜ ተመርጠው ሥልጣነ ክህነቱን የሚቀበሉት በመንፈስ ቅዱስ የተመረጡበትን ዕጣ ሲያገኙ ብቻ ነው፡፡ይህ ስርዓት የሚካሄደው የሚወጡት እጣዎች ሁሉ በመንበሩ ላይ ለሰባት ቀን ተቀምጠው እንዲጸለይባቸው እና እንዲቀደስባቸው ተደርጎ ነው፡፡(ለሰባት ቀናት የተወሰኑባቸውን ምክንያቶች በገጽ 94 ላይ ይመልከቱ ) ፡፡ ምንም እንኳ በህዝበ ክርስቲያን እና በጳጳሳት በኩል በአንደኛ ደረጃ ላይ የተመረጡ ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ ካልተጨመረበት ስልጣኑ እንደማይሰጣቸው ሊቀካህናት ክንፈገብርኤል አልታዬ ገልጸዋል፡፡ በዚህ መልኩ የተመረጡ

ቆሞሳት ቀን ተወስኖላቸው ህዝብ በተሰበሰበበት በእለተ እሑድ በቅዳሴ ስርዓት ላይ የኤጲስ ቆጶስነት ስልጣን ይሰጣቸዋል፡፡

የብፁእ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሰባተኛ አመት የሲመት በዓል በሚከበርበት እለት እሁድ ሐምሌ አምስትቀን 1991ዓ.ም. ለአስራ ስድስት ቆሞሳት የኤጲስ ቆጶስነት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በማኅበረ ቅዱሳን ኦዲዮ ቪዥዋል ክፍል በቪዲዮ ተቀርጾ ከተቀመጠ መረጃ የኤጲስ ቆጶስነት ስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ የሚከተለውን አይነት የስርዓተ አከዋወን ሂደት ነበረው፡፡

ስልጣነ ክህነቱን ለመስጠት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘ ኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘ አክሱም ወጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲል ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ደረሱ፡፡ በቦታው ሲደርሱ ሶስት ጊዜ ደወል ተደወለ፡፡ የእሳቸውን መምጣት ሲጠባበቁ የነበሩ ህዝበ ክርስቲያን፣ቀሳውስት፣ዲያቆናት ፣ሊቃውንት ቤተክርስቲያንና ሌሎች እንግዶች በታላቅ እልልታና ዝማሬ ተቀበሏቸው፡፡አብረዋቸው የመጡ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ፣ አቡነ ጢሞቲዎስ፣ አቡነ ገሪማ፣ አቡነ አትናቴዎስ፣ አቡነ ፊሊጶስ፣ አቡነ ጎርጎርዮስ፣ አቡነ መቃርዮስ፣ አቡነ ቀውስጦስ እና ሌሎችም ጳጳሳት ሲሆኑ ቁጥራቸውም አስራ ሰባት ነበር፡፡

ሁሉም ጳጳሳት ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰዋል፡፡ በዕለቱ ስልጣነ ክህነቱን የሚቀበሉ አስራ ስድስት ቆሞሳት በቤተ መቅደስ ውስጥ ገብተው መጀመሪያ በሚገኘው ቦታ ላይ ቆመው ሥርዓቱን ለመከታተል ዝግጁ ሆኑ፡፡ አቡነ ጳውሎስም ህዝቡን እየባረኩ ወደ ውስጥ በመዝለቅ ሶስት ጊዜ ተሳለሙ፡፡ ወዲያው ከየትኛውም ስርዓት ቀድሞ የሚፈፀመውን ኪዳን አድርሰው ወደ ስርዓተ ጵጵስናው ዘለቁ ፡፡ በእለቱ አቶ ዮሴፍ ወልደ መስቀል የአዲስ አበባ መስተዳድር፣የውጭ ዜጎች፣የማህበራዊ ቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና በአዲስ አበባ የሚገኙ ልዩ ልዩ የእምነት መሪዎች የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች ተገኝተዋል፡፡

የውጭ ዜጎችና የሃይማኖት መሪዎች ስርዓቱን ሲከታተሉ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በዕለቱ የለበሱት ልብሰ ተክህኖ ቀይ መደብ ያለው ሆኖ በወርቃማ ቀለም ያሸበረቀ ነው፡፡ በራሳቸው ላይ የደፉት አክሊል የካባው አይነት ቀለም ያለው ሲሆን

ከግንባራቸው ትይዩ ቅድስት ማርያም ከልጇ ጋር ሆና የሚያሳይ ስዕል አለበት፡፡ መሃሉ ላይም የመስቀል ቅርጽ አለው፡፡ በእጃቸው የያዙት በትረ (ብርት) አርዌ ወርቃማ ቀለም ያለው ሲሆን ጫፉ ላይ የእባብ ምስል አለው፡፡ የዚህ ተምሳሌት ሙሴ በበረሃ ላይ ሰቅሎ የታመሙ ሰዎች ሁሉ እሱን እያዩ እንዲፈወሱ እግዚአብሄር ያዘዘውን ትዕዛዝ የሚያስታውስ ነው፡፡ ይህ በሐዲስ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ይህም ሰዎች ይፈወሱ፣ ከሃጥያተቸውም ይድኑ ዘንድ በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንደሚገባ የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ አርዌ በትር ሙሴ ከአለት ውሃ ያፈለቀበት፣ የኤርትራን ባህር ለሁለት የከፈለበት እና ህዝቡን ከግብፅ ባርነት ያሻገረበት ምሳሌ ነው፡፡ በመሆኑም ምዕመናኑን የመጠበቂያ ምሳሌ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢየሱስ ጴጥሮስን በዮሐ (21÷15) ላይ ግልገሎቼን፣ በጎቼን፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ ብሎ የተናገረው ቃል ለእርሱ ብቻ ሆኖ የቀረ ሳይሆን የካህናትን ተግባር የሚያመለክት፣ ግልገሎች በጎችና ጠቦቶች የምዕመናን ምሳሌዎች ሲሆኑ በትሩ ምዕመናኑን በሚጠብቁበት ህግና ሥርዓት የሚመሰል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በስርዓቱ ላይ የተገኙት ጳጳሳት የለበሱት ልብስ ወደ ቢጫ ወርቃማና ነጭ ቀለም የሚያደላ ነው። ትልልቅ መስቀል አድርገው አርዌ በትራቸውንም ይዘዋል። የጳጳሳቱ አርዌ በትር ከፓትሪያርኩ በትር አጠር ያለ ሆኖ ጫፉ ላይ ድቡልቡል ቅርፅ ያለው ነው።

ስልጣኑን ከሚቀበሉት ከአስራ ስድስት ቆሞሳት አንዱ ሰማያዊ ሌላው ደግሞ ነጭ ከመልበሳቸው በስተቀር ሁሉም ጥቁር ቀሚስ ከነቆቡ አድርገዋል። ቆሞሳቱ ረጅም አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ጠረጴዛ ነጭ ልብስ ለብሶ በላዩ ላይም በብርጭቆ አበባ በተቀመጠበት ጠረጴዛ ዙርያ ከበው ሥርዓቱን ይከታተሉ ነበር። ጳጳሳት ደግሞ ዙርያቸውን ከበው የተቀመጡ ሲሆን ሌሎች ህዝበ ክርስቲያናት እና እንግዶች ከእነሱ ኂላ በመሆን ቆመዋል ። በዕለቱ ሥርዓተ ቅዳሴውን ያከናወኑ ጳጳሳት እና ቆሞሳት ናቸው እንጂ እንደ ዘወትር ቀናት ቀሳውስትና ዲያቆናት ብቻ አልቀደሱም ። ስርአቱን የሚፈጽሙ ጳጳሳትም አንድ ብቻ አለመሆናቸው የሥርዓተ ክዋኔውን ታላቅነት የሚጠቁም ነው።


ስልጣነ ክህነቱ የሚሰጠው የቅዳሴ ግማሽ ላይ በመሆኑ ሥርዓተ ቅዳሴው ግማሽ ላይ ሲደርስ ፓትርያርኩ በቀይ ቡኒ ብራና የተለበጠ የስልጣነ ክህነት መስጫ መፅሐፍ አውጥተው በግዕዝ አነበቡ። ሌሎችም ጳጳሳትም በሙሉ ተሰብስበው ሲመቱን በተመለከተ ተራ በተራ ከመጽሐፉ አነበቡ። ይህም ንባብ ክዋኔውን ለማስፈፀም የሚያስችል ስርዓት ነው።

ከዚያ በኂላ ሁሉም ጳጳሳት ቆባቸውን አውልቀው በጠረጴዛው ላይ አስቀመጡ። ካለአንድ ቆሞስ በስተቀር ሁሉም ፀጉራቸውን ተላጭተው ነበር ። የሚላጩትም በመኖኩሴ ነው። ጸጉራቸውን ከሚላጩበት ምክንያቶች አንዱ ወደ አዲስ ህይወት መግባታቸውን ለማመልከት ሲሆን ሌላው ደግሞ ጸጉር በየጊዜው ተቀርጦ የሚወድቅ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ በቋሚ አካል ላይ እንጂ በትርፍ አካል ላይ ስለማያድር ነው። ፓትርያርኩ ከዚህ ቀጥለው ፀሎቱን እየጸለዩ መስቀላቸውን በራሳቸው ላይ በማኖር (በማድረግ) ባረኳቸው።ሲባርኳቸውም እንደተመረጡበት ቅደምተከተል ከግራ ፣ከቀኝና ከመሃል እየለዩ ነው ።



*ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በመስቀላቸው ቡራኬ ሲሰጡ*


የዚህ ድርጊት ተምሳሌት ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን አንዱን ከአንዱ ሃገር ሌላውን ደግሞ ከሌላ ሃገር መምረጡን የሚያመለክት ነው፡፡በመስቀሉ ከባረኳቸው በኋላ ጸጋ እግዚአብሄር የሚያሰጠውን አንብሮተ ዕድ"አነ እነብር እደዊከ ሀበዝንቱ ገብር ኅሩይ ዘእግዚአብሄር በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ " በማለት ፈፅመዋል ፡፡ይህ ስርአት በሉቃስ 24 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደሰማይ ሲያርግ እጁን አንስቶ ባረካቸው የሚለውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ በሶስቱም የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ላይ ሲፈጸም ክህነቱን ፍጹም ለማድረግ ነው፡፡ይህም ከተጠናቀቀ በኋላ የእጅ መስቀል ይሰጣቸዋል፡፡



*ጳጳሳት አንብሮተ ዕድ ሲፈፀምላቸው*

ከዚህ ቀጥሎ በአንገታቸው ላይ አስኬማ ተደረገላቸው። ይህ አስኬማ የተዘጋጀው ከቆዳ ሲሆን አስራ ሶስት መስቀል አለበት። አስራ ሶስቱ መስቀሎች የአስራ ሶስቱ ህማማተ መስቀል ምሳሌዎችን የያዙ ናቸው። አስራ ሶስቱ ህማማተ መስቀል ኢየሱስ ከጸሎተ ሃሙስ ጀምሮ እስከ ስቅለት ድረስ የደረሰበትን መከራዎች እንደ ግርፋት፣ስቅላት፣በጥፊ መመታት፣በመስቀል ላይ መቸንከር ፣አክሊለ ሶክ ማድረግ እና ሌሎችም ናቸው። እንዲሁም ይህ አስኬማ ቅናተ ዮሃንስም ይባላል። በማቴ 3 ላይ በተገለጸው መሰረት ዮሃንስ ይኖር የነበረው በበረሃ የግመል ጠፍር ታጥቆ ነበር። ጳጳሳቱም የዮሃንስን ፈለግ በመከተል ፣ለእግዚአብሄር በመለየት ቅናተ ዮሃንስን በማድረግ የክርስቶስን መከራ በማሰብ ህዝቡን ከሃጥያት ለመመለስና ለማስተማር ይነሳሉ።

ከዚህ ሥርዓት በኋላ በስርዓቱ የተገኙት ጳጳሳት ከኋላቸው በመሆን እየዞሩ በቀኝ እጃቸው ትከሻቸውን ጫን ጫን በማድረግ ነኳቸው።ይህን ማድረጋቸውም የሚሰጣቸው ሃብት ብዙ በመሆኑ( ክህነትን መስጠት፣ሜሮን ማፍላትና መለወጥ፣ታቦትና ቤተክርስቲያንን መባረክ እንዲሁም ማስተዳደር) የእነሱ ጸጋና በረከት እንዲያድርባቸው ለማድረግ ነው።



*ጳጳሳት በአንድላይ በመሆን ኤጲስ ቆጾሳቱን ሲዳስሷቸው*

ከዚያም በኋላ ካባ እና አስኬማ ቆብ በጠረጴዛው ላይ በፊት ለፊታቸው ተቀመጠና ተፀለየበት። ፓትርያርኩ በቅድሚያ ቀሚሱን ከዚያም ሞጣይቱን (በአንገት የሚጠለቅ፣ በኋላ በኩል እስከ ጀርባ ፣ በፊት ለፊት በኩል ደግሞ እስከ እግር ጥፍር ድረስ የሚወርድ)



ቀጥሎም ካባውን አለበሷቸው፡፡ ይህ ሥርዓት እንደተጠናቀቀ አስኬማ ቆቡ ተደረገላቸው፡፡ ይህ ስርዓት እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ካህናት ይለብሱት ዘንድ የመረጠላቸውን የአልባሳት አይነት መሰረት ያደረገ ነው፡፡





*ለኤጲስ ቆጶሳቱ የተዘጋጁ ካባዎችና አስኬማ ቆቦች*


ስርአቱንም እግዚአብሄር ለሙሴ በዘሌ (8÷6 -21) ፣ ዘዳ( 28÷2) ላይ በዝርዝር ገልፆለታል፡፡ ሙሴም አሮንንና ልጆቹን በታዘዘው ስርዓት መሰረት ልብሶቹን ያለብስ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን የታዘዙት ስርዓቶች ሲወርድ ሲዋረድ ለዚህ ዘመን እየተላለፉ የደረሱ ትውፊቶች ናቸው፡፡ በዚያ ጊዜ ለአገልግሎት ስርአት እጀሰፊና እጀጠባብ ቀሚስ፣ዥንጉርጉር መደረቢያ፣መጠምጠሚያ፣ቆብ፣ዑሪምና ቱሚም የሚቀመጡበት የደረት ኪስ፣መታጠቂያ፣ኤፉድ እና የበፍታ ሱሪ ይለብሱ ዘንድ ያዝዝ ነበር፡፡ አሁን በከፊል የሚፈፀመው ስርዓት ያንን ለማድ የተከተለ ነው፡፡ ይህ ውስጣዊና ውጪያዊ ትርጉም ያለው ሲሆን ውስጣዊ ትርጉሙ እንደ የነፍስና የስጋን ንፅህና፣የእግዚአብሔርን ፀጋና ረድዔት ፣ቀሚሱ ሰፊ ነውና ታጋሽነትን ፣ቻይነትን የሚያመለክት ሲሆን ውጪያዊው እይታ ደግሞ ለስርአት፣ ለሞገስና ለክብር እንዲሁም ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ለመለየት ነው፡፡

ጳጳሳት ልብሰ ተክህኖ ሲለብሱ እና አስኬማ ቆብ ሲደረግላቸው፡፡

የለበሱት ቀሚስ ቀለም ከሃር የተሰራ ወርቃማ ( ወደ ቢጫ የሚያደላ) ቀለም ያለው ሲሆን ሞጣይቱ እና ከባው ቀይ ዥንጉርጉር ሲሆን አክሊለ ሶኩ( ቆቡ) ደግሞ ከሃር የተሰራ ጥቁር ቀለም ያለው ነው፡፡ ለጳጳሳት፣ለቀሳውስትም ሆነ ለመነኩሴዎች ቆብ ሲደፉ ተመሳሳይ ተምሳሌት አለው፡፡ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ በእለተ አርብ አይሁዳውያን ሲሰቅሉት የእሾህ አክሊል የደፉበትን እና ስለሰው ልጆች ብሎ የደረሰበትን መከራ በማሰብ ንስሃ እንዲገቡ፣ በመከራው በመዳናቸውም ምስጋና እንዲያቀርቡ ነው፡፡

ፓትርያርኩ ይህንን ሥርዓት ፈፅመው እንደጨረሱ የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣናቸውን በሚገባ መፈፀም እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ከአስራ ስድስቱ መካከል አንዱ ኤጲስ ቆጶስ ሁሉንም በመወከል ቃል ገቡ፡፡ የሚፈፅሙትን ተግባር ከወረቀት ላይ እያነበቡ ቃል ኪዳን የገቡ ሲሆን ከእነሱም ውስጥ በኒቅያ ጉባኤ ላይ በተደነገገው ሥርዓት (በፀሎተ ሃይማኖት) እንደሚያምኑ፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ፍፁም አንድ አካል መሆናቸውን፣ ወልድ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ መሆኑን፣ ማርያም የአምላክ እናት መሆኗን ፣እና ሌሎችም መሠረታዊ ነገሮችን አምነው እንደሚያስተምሩ የሚገልፁ ናቸው፡፡ የቃል ኪዳን ሥርዓቱ ከተፈጸመ በኋላ ፓትርያርኩ ስም አውጥተውላቸዋል፡፡ ይህ ስም ከዚያ ዕለት ጀምሮ የሚጠሩበት ሲሆን ስያሜውን ሲሰጡ የሚሰሩበትን ሃገረ ስብከት ጭምር በመግለፅ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ ወእስይመከ ብፁዕ አባ……" በማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ህዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ እያጨበጨቡ አሜን በማለት ፈቃዳቸውን ገልፀዋል፡፡



*ሁሉንም ጳጳሳት በመወከል ቃለ መሃላ ሲፈጸም*

ይህ ሥርዓት ከተጠናቀቀ በኂላ ወንጌል ተነበበ። ፓትርያርኩ እጃቸውን ታጥበው ወደ ቤተመቅደስ ሲገቡ የተሾሙት ጳጳሳትም ወደ ውስጥ ገቡ። ወደ ውስጥ የገቡበት ምክንያት በውስጥ ሆነው ሥጋ ወደሙን መቀበል ስለሚገባቸው ነው። በዚያ ውስጥም የሜሮን አቀባብ ስርዓት እንደሚፈፀም ገልፀውልኛል። የሚቀቡትም እራሳቸውን አምስት ቦታ ላይ ሲሆን የአምስቱ አዕማደ ምስጢራትን የሚወክል ነው። አምስቱ አእማደ ምስጢራት ምስጢረ ስላሴ፣ምስጢረ ስጋዌ፣ ምስጢረ ቁረባን፣ምስጢረ ጥምቀት እና ምስጢረ ትንሳኤ ሙታን ናቸው። እነዚህን ምሳሌ በማድረግ ሜሮኑን መቀባታቸው ምስጢራቱን አምነው በመቀበል ለህዝቡ ደግሞ በማስተማር ምስጢራቱን መግለጽ ይችሉ ዘንድ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉበት ሥርዓት ተፈፅሟል ይህንንም ለመፈጸም ኪርያላይሶ ተብሎ ከተፀለየ በኂላ ጳጳሳቱን ወደ እሳቸው ተራበተራ ቀረብ በማድረግ "ንሳ መንፈስ ቅዱስ" በማለት እፍ አሉባቸው። እነሱም ተቀበሉ።ምእመናኑም ይደልዎ፣ይደልዎ፣ ይደልዎ በማለትም ሥልጣነ ጵጵስናውን የሚገባቸው መሆኑን መስክረዋል።


የክህነት አሠጣጥ ሥርዓቱ ከተጠናቀቀ በኂላ ወደ ውጪ በመውጣት በአውደ ምህረቱ ላይ ተቀመጡ። በዚያም የፓትርያርኩን በዓለ ሲመት በተመለከተ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ቀረቡ።

ከቀረቡት ውስጥም ቅኔ፣ መዝሙር፣ ወረብ እና ትምህርት ይገኙበታል። የነዚህን ዝግጅቶች ይዘት ፓትሪያርኩንና ጳጳሳቱን የሚያወድሱ ናቸው። በዕለቱ የተሾሙትን ኤጲስ ቆጳሳት በተመለከተ


*በውስተ ሰባቱ በጉልቆ አስርቱ ቃላት ወበጉልቆ ቃላት ስድስቱ*

*ሁልቆ ሃሳበ ባህር አውጸአ ጳውሎስ ዘርእሰ አበው ውእቱ*

የሚል ቅኔም በዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ አዘጋጅ መጋቢ ምስጢር ወልደ ሩፋኤል ቀርቦ ነበር።



*ካህናት በአለ ሲመቱን በተመለከተ ያሬዳዊ ዜማ ሲያቀርቡ*



*መጋቤ ሚስጥር ወልደሩፋኤል ቅኔ ሲያቀርቡ*

### 5.3.3 ድህረ ስርዓተ ክዋኔ

የኤጲስ ቆጳስናን ሥልጣን ከተቀበሉ በኋላ ሶስት ሱባኤ ( ሶስት ሳምንታት ወይም ሃያ አንድ ቀናት) ይፆማሉ።ዘወትር ጤነኛ ይሆኑ ዘንድ እለት እለት ስጋወደሙን መቀበል አለባቸው። ጳጳሳት ደናግላን ናቸው። ከሴት ጋር ተገናኝተው እንዳይሳሳቱ ምግባቸውን አዘጋጅቶ የሚቀልብ ወንድ መነኩሴ ሲሆን የላመ የጣፈጠ መመገብ አልተፈቀደላቸውም። በሥርዓተ ክዋኔው ላይ የገቡትን ቃል ኪዳን አንድ በአንድ መፈፀም እና የተሰጣቸውን ጸጋ መጠበቅ ይገባቸዋል። እነሱ የህዝበ ክርስቲያን መሪ በመሆናቸው ሃይማኖት እንዳይጠፋ ህዝቡ

እንዳይሳሳት መልካም እረኛ በመሆን ቤተክርስቲያንን ይጠብቃሉ። ኤጲስ ቆጶስነት ሃብተ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ለዘመድ በውርስነት እንደማይሰጥ ፍትሃ ነገስት አንቀጽ 5 ቁጥር 164 ይገልጻል።

ስልጣናቸውን ከእግዚአብሔር የተቀበሉ እና በክርስቶስ መንበር የሚያስተምሩ በመሆናቸውም መጠሪያቸውም "ኖሎት " (ጠባቂ ነው)።አኗኗራቸው ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ መምሰል የለበትም። በመሆኑም ቤት፣ መሬት፣ ንብረት፣ ሚስት፣ ልጅ ፣ ርስት .....ሳይሉ በቤተክርስትያን መኖር እንዳለባቸው በፍትሃ ነገስት አንቀጽ 5 እና በድስቅልያ 38 ላይ ተገልጧል።ይህንን ስርአት ሃዋርያት የመሰረቱበት ምክንያት ጳጳሳቱ በሃገቱ እንደልብ ተዘዋውረው ማስተማር፣ በአንድ ልብ ሆነው እግዚአብሄርን ማገልገል እንዲችሉ ነው።

በሶስቱም የስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ ላይ ተደጋግመው በመምጣት ለመተርጎም የቻሉት ዋናዋና ሞቲፎች ቡራኬ፣ቁጥር ሶስት እና ሰባት፣አንብሮተ እድ ፣ድንግልና፣ቁርባን፣ቅዳሴ፣ልብስ፣ መስቀል እና ስነምግባር ናቸው። እነዚህ ሞቲፎች የስርአተ ክዋኔው ገጽታ ነባራዊውን ሁኔታ በመያዝ፣ ቀጣይነት እንዲኖረውና ትውፊታዊነቱን በማመልከት የክህነት አሰጣጡ በምን መልኩ የሃገረሰባዊ ልማድ ገጽታን እንዳመለከቱ ያሳዩ ናቸው። እነዚህ የአንድ ማህበረሰብ የእምነት ስርአትና የባህል እሴት የታየባቸው ሞቲፎች በእያንዳንዱ ክስተት ወይም ብቅ በሚሉበት ቦታ ላይ የሚኖራቸው ትርጓሜ የካህናትን፣ የማህበረሰቡንና የእምነት ስርአቱን በማሳየት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ናቸው።

# ምእራፍ ስድስት

## 6.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታውን ማሳየት ነው። ፎክሎራዊ ገጽታውን ለማሳየት በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደውን የሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ በመመልከት አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል።

አንድ ግለሰብ ለወግ ማዕረግ ለመብቃት ሦስት ደረጃዎችን ማለፍ እንዳለበት እነሱም መለየት (separation) ፣ ሽግግር (transition) ፣ እና መመለስ (reincorporation) መሆናቸው በጥናቱ ተጠቁሟል። በዚሁ መሰረት ሦስቱን ደረጃዎች ለማሳየት ይቻል ዘንድ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

መለየት (separation) የተለያዩ ግለሰቦች ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል ከማህበረሰቡ ተለይተው በመውጣት ለክህነት የሚያበቁ መስፈርቶችን የሚያሟሉበት ደረጃ ሲሆን ይህንን ለማመልከት ከብስራተ ገብርኤል እና በአታ ለማርያም ቅድስት ቤተክርስቲያን መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል።

ሽግግር (transition) ደግሞ ከማህበረሰቡ ተለይተው ለክህነት የሚያበቋቸውን መስፈርቶች ካሟሉ በኋላ ከነበሩበት ደረጃ ከፍ ወዳለው የሚሸጋገሩበት ነው። ይህንን አስመልክቶ የሚፈፀመው ስርአት ሥልጣነ ክህነትን የሚቀበሉበት የክዋኔ ሥርዓት ሲሆን መረጃዎቹም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም እና ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ተሰብስበዋል።

መመለስ (reincorporation) ሥልጣነ ክህነቱን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ማህበረሰቡ ተመልሰው በመምጣት ተልዕኳቸውን የሚፈጽሙበት፣ የክህነት ሥልጣን መቀበላቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን የሚከውኑበት ሲሆን ይህንን ገጽታ ለማመልከትም የተለያዩ ነባራዊ ገጽታዎችን በመመልከትና መረጃዎችን በመሠብሠብ ትንታኔ ቀርቧል። ይህንን ጥናት ለማካሄድ ስርአተ ክዋኔው እንዴት እንደሚፈጸም ፣ በማን እንደሚፈጸም፣ መቼ እንደሚፈጸም፣ ለምን እንደሚፈጸም ገልጾ ለማሳየት ገላጭ የምርምር ስልት እና የክዋኔ (performance) የቲዎሪ አቀጣጫ ወይም ዘዴ አገልግሎት ላይ

ውለዋል። በጥናቱ እነዚህ ዘዴዎች ጥቅም ላይ የዋሉት በዲቁና፣ በቅስና እና በኤጲስ ቆጶስና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ እና ክህነቱን ከመቀበላቸው በፊት እና በኋላ ባሉት ገጽታዎች ላይ ነው።

ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣርያ ሆነው ያገለገሉት ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና የቡድን ውይይት ናቸው። ስርዓተ ክዋኔው ለመተንተንና ለመተርጎም ይቻል ዘንድ ጳጳሳት፣ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ፣ቀሳውስት፣ዲያቆናት፣ የመንፈሳዊ ትምህርት መምህራንና የተለያዩ ምዕመናን ቃለመጠይቅ ተደርጎላቸዋል። እንዲሁም የዲቁናን ሥርዓተ ክዋኔ በተመለከተ ሥልጣነ ዲቁናውን ከተቀበሉት ስድስት ዲያቆናት ጋር የቡድን ውይይት በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

የተሰበሰቡት መረጃዎች በጥንቃቄ ተመርምረውና በአይነት በአይነታቸው ተከፋፍለው ተተንትነዋል ፣ ተተርጉመዋል። በመረጃ ትርጎማው ላይ የፎክሎር ገጽታዎች ተጠቁመው ተምሣሌታዊ ፋይዳቸው ሲገለጽም የሚከተሉት ነጥቦች የጥናቱ ግኝቶች ሆነው ቀርበዋል ።

## 6.2 የጥናቱ ግኝቶች

1. ስልጣነ ክህነትን መቀበል ከዝቅተኛው ማህበረሰባዊ ቦታ ወደ ከፍተኛው የሚያሸጋግር እና ስልጣኑን ለመቀበል ስርአት የተበጀለት በመሆኑ ወግ ማእረግ ነው። የስልጣነ ክህነቱ አሰጣጥ ትውፊታዊ መርሆዎችን የያዘ በመሆኑም ሃገረሰባዊ ልማድ ነው።
2. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የክህነት ስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ የሚፈጸመው ለዲቁና፣ቅስና እና ኤጲስ ቆጶስና ማእረግ ብቻ ነው።
3. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አሁን ያለው የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓት መመርያ ወይም መሰረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ክህነትን የሰጠበት ስርአት ነው ። ሥርዓቱ ሰዎች ምስጢራትንና አምልኮተ ቤተክርስቲያንን ለመፈጸም የሚችሉበትን ኃይል እንዲያገኙ የሚያስችል ሲሆን ቤተክርስቲያን የተባለውን ተቋም ለመመስረትም እነዚህ ካህናት የግድ መኖር አለባቸው።

4. የዲቁና የቅስና እና የኤጲስ ቆጶስና ሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ሲፈጸም እያንዳንዳቸው የሚመሳሰሉበት እና የሚለያዩበት ገጽታ አላቸው፡፡

## 4.1 ተመሳስሎ

- ሦስቱም ስልጣነ ክህነትን ከመቀበላቸው በፊት የሚፈጽሟቸው የተለያዩ ቅድመ ስርአቶች አሏቸው፡፡
- የሦስቱም ሥርዓተ ክዋኔ በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ይካሄዳል፡፡
- በሦስቱም ሥርዓተ ክዋኔ ላይ የአንብሮተ ዕድ (እጅ መጫን)ና የጸሎት ሥርዓት ይካሄዳል፡፡
- በሦስቱም ሥርዓተ ክዋኔ ላይ ሥልጣኑን የተቀበሉ ካህናት ለተከታታይ ቀናት እንዲቆርቡ ይደረጋል፡፡ ( የመቁረቢያው ቀን ቁጥር ቢለያይም)

## 4.2 ልዩነት

- በዲቁና እና በቅስና ሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ጊዜ ሥልጣን የሚሰጠው በአንድ ሊቀ ጳጳስ ነው፡፡ ለሥርዓቱ ህዝብ እንዲሰበሰብ አይደረግም፡፡ ፕሮግራምም አይወጣለትም፡፡ በሰጪውና በተቀባዩ ስምምነት ብቻ የመስጪያው ቀን ይወሰናል፡፡ በኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ጊዜ ግን ፕሮግራሙ ለህዝብ ይፋ ሆኖ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን፣ የመንግስት ባለሥልጣናትና የሃይማኖት መሪዎች በተገኙበት ይፈጸማል፡፡ሥርዓቱ የሚፈጸመው ከሁለት በላይ በሆኑ ሊቃነ ጳጳሳትና በፓትርያርክ ነው፡፡
- የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ከቅስና እና ዲቁና ሥልጣን አሠጣጥ ሥርዓት የሚለየው በአስኬማ፣ በልብሰ ተክህኖ አለባበስ፣ በአርዌ ብርት አሰጣጥ፣ በስም አወጣጥ፣ ቃል ኪዳን በመግባትና በቅዳሴ ሥርዓት የሚከናወን በመሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም የቅስና ስልጣን ከዲቁና ስልጣን አሰጣጥ ስርአት የሚለየው በንፍሃት፣ የቀሳውስት አንብሮተ ዕድ (ዳሰሳ) ሥርዓት የሚፈጸም በመሆኑ ነው፡፡
- ስልጣነ ክህነቱ ሲሰጥ ለሦስቱም የክህነት ደረጃዎች የሚጸለየው ጸሎት የተለያየ ነው፡፡ ሶስቱም አይነት ጸሎቶች የእያንዳንዱን ክህነት አይነት ለመስጠት የሚያስችል ይዘት እና ሊፈጽሙ የሚገባቸውን ተግባር የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

5. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የስልጣን ተዋረድ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ሲቀመጥ አፃዊ ሆህት ➔ መዘምር➔ አናጉንስጢስ➔ ንፍቀዲያቆን➔ዲያቆን➔ቄስ➔ኤጲስ ቆጶስ ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ ሥልጣነ ክህነት የሚባሉት ዲቁና፣ቅስና እና አጲስ ቆጶስና ናቸው። ሌሎች ግን ሹመት (በሰው መብትና ስልጣን የሚሰጡ ናቸው) የቤተክርስቲያን ስርዓት፣ አምልኮና ምስጢር የሚፈፀመው በእነዚህ የክህነት ተዋረድ ቅንጅት ነው።

6. የክህነትን ስልጣን ለመቀበል መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

ለዲቁና➔ ድንግልና፣ጥሩ ስነምግባር እና የክህነት ትምህርት

ለቅስና➔ የክህነት ትምህርት፣ሚስት ማግባት፣ጥሩ ስነምግባር

ለአጲስ ቆጶስና➔ የክህነት ትምህርት፣ድንግልና፣ ጥሩ ስነምግባር፣ የአስተዳደር ብቃት እና ምንኩስና ናቸው።

7. ካህናት ስልጣነ ክህነቱን ከተቀበሉ በኋላ በአለባበስ፣በአነጋገር፣በአኗኗር ዘይቤ፣በአስተሳሰብ ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ የአኗኗር ልማድ ያበጃሉ።እነዚህ የአኗኗር ልማዶቻቸው ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ገጽታዎችን የሚያንጸባርቁ ናቸው።

8. ካህናት በስርአተ ክዋኔው ላይ በተቀበሉት ስልጣን መንፈሳዊና ስጋዊ፣ማህበረሰባዊና ግለሰባዊ አገልግሎት ይሰጣሉ።( የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔው ካህናት አገልግሎትን መስጠት ይችሉ ዘንድ የሚያስችላቸውን ኃይል የሚሰጥ ነው።)

9. በሶስቱም የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ ላይ ተደጋግመው የሚመጡ የተለያዩ ሞቲፎች(motives)ቡራኬ፣ሶስትእናሰባትቁጥሮች፣ጸሎት፣ድንግልና፣ስነምግባር፣መስቀል፣አንብሮተ እድ ፣ቀሚስ መልበስ፣ቅዳሴ፣ ቁርባንና ቤተክርስቲያን ናቸው።

## 6.3 ከቀረቡት ግኝቶች በመነሳት በጥናቱ የተደረሰበት ማጠቃለያ (conclusion)

የሰዎችን የህይወት ገፅታ እና የአኗኗር ዘዴ የሚለውጡ ሁለት ነገሮች ተፈጥሮ እና ሃገረሰባዊ ልማድ ሲሆኑ የእነዚህ በአንድ ሰው ህይወት ላይ መከሰት ወይም ተግባራዊ መሆን ግለሰቡን ለወግ ማዕረግ በቃ ያሰኘዋል።

በተፈጥሮ የሚገኘው ሽግግር በማንኛውም ማህበረሰብ ላይ የሚከሰት ሲሆን መወለድ፣የዕድሜ እርከን እና ሞት ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ተፈጥሯዊ ሒደቶች ሲከሰቱ ማህበረሰቡ እንደ አኗኗር ልማዱ፣ እምነቱ፣ አመለካከቱ እና ህይወትን በሚተረጉምበት መንገድ ተመስርቶ ስርአቶችን በማበጀት ተፈጻሚነታቸውን ያረጋግጣል።

ሃገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ እንደ ንቃተህሊናው ፣አለምን እንደሚተረጉምበት አቅጣጫ፣እንደ አስተሳሰቡ፣ፍልስፍናው፣የአኗኗር ዘይቤው፣ዕውቀቱና በአጠቃላይ ልዕለ ተፈጥሮንና ልዕለ ሰብዕን ከሚመለከትበት እይታው ወይም ግንዛቤው ተነስቶ የህይወቱን አቅጣጫ የሚለውጥበት፣ከአንዱ የህይወት እርከን ወደ ሌላው የሚሸጋገርበትን መርህ የያዘ ነው። በሃገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ትውፊት የአኗኗር መርህ ነው።

የሰው ልጅ ወግ ማእረጉን ከሚያይባቸው ገጽታዎች መካከል፣ ከተሰማራበት የሙያ መስክ ወደ ሌላው የሚያደርገው ለውጥ፣ ወይም ከነበረበት የህይወት ገፅታ ወደ ተሻለው እና ወደከፍተኛው የሚያደርገው ሽግግር አንዱ ነው። ይህ ገፅታ ስልጣንን መቀበል ወይም ሹመት (Advancement to a higher class) ሲሆን ስልጣኑን ወይም ሹመቱን ለመስጠትም ሆነ ለመቀበል የሚፈፀም ስርዓተ ክዋኔ መኖር አለበት።እነዚህ ወግ ማእረጎች በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ተግባራዊ ሲሆኑ ማህበረሰቡ አሜን ብሎ የሚቀበላቸው የተለያዩ ስርአተ ክዋኔዎችን በመፈጸም ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔ አንድን ግለሰብ ከነበረበት የሙያ መስክ ከፍ ወዳለው ቦታ ለማሸጋገር የሚደረግ የማእረግ አሰጣጥ ስርዓት መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል ። ስርዓቱ የሚጀምረው ከዝቅተኛው ወደከፍተኛው (ከዲቁና ወደ ቅስና ከዚያም ወደ ኤጲስ ቆጶስና) ስልጣን በመሆኑ የቤተክርስቲያኗን የስልጣን መዋቅር ያመለክታል። ይህም የአንድን ማህበረሰብ የዕምነት ተቋም አደረጃጀት አውድ ገልፆ የሚያሳይ ነው። በስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔው ላይ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ካህናት

የተለያዩ አገልግሎቶችን ለመፈፀም የሚያስችላቸውን ኃይል የሚቀበሉበት እና የሚመሯቸውን ህዝበ ክርስቲያናት ሃማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶቻተውን ጠብቀው እንዲኖሩ አርአያ ለመሆን የሚወስኑበት ነው፡፡

ትውፊት ጥንት የነበረ አሁንም ያለ እና ወደፊትም ሊቀጥል የሚችል የአንድ ህዝብ ማንነት መገለጫ ነው፡፡ የስርዓተ ክዋኔው አፈፃፀም ስርዓትም ትውፊትን መሰረት ያደረገ ሲሆን አመጣጡም የሐዲስ ኪዳን መስራች ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ እስከ ሐዋርያት፣ ከሐዋርያት ደግሞ ሰባቱ ዲያቆናት ከሰባቱ ዲያቆናት እንዲሁ ሰባ አርድእት ከዚያም ሌሎች አባቶች ሲፈጽሙበት የነበረውን ስርዓት ተከትሎ ነው፡፡ በስርዓተ ክዋኔው ወቅት የሚፈፀሙ ድርጊቶች፣ለአገልግሎት የሚውሉ ቁሶች፣ንግግሮች፣ፀሎቶች ሁሉ ሃይማኖትን ትውፊትንና ልማድን የሚያንፀባርቁ ገፅታዎች ናቸው፡፡ ጥንት የሃይማኖቱ ተከታዮች ሲፈፅሙት የነበረው የክህነት አሰጣጥ ስርዓት የክርስትናን ምስጢር እንዲገልፁ ሆነው የተደነገጉ፣ ክርስቶስን ለመከተል የሚያስችሉ ገፅታዎችን በማንፀባረቅ ሲሆን ስርአቱ ትርጉም ይኖረው ዘንድ የማህበረሰቡን ልማድና እውቀት በመመርኮዝ መመርያዎችን ያወጣሉ፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት


ሄኖክ ሃይሌ :: ክብረ ክህነት :: አዲስ አበባ ፣ አስበ ሉሲ ማተሚያ ቤት፣ 1999::

ሉሌ መልአኩ:: የቤተክርስቲያን ታሪክ :: አዲስ አበባ ፣ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1986::

________ ::የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያ ታሪክ :: አዲስ አበባ ፣ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፣1997::

ሐየሎም በርሄ ::ሁለቱ ኪዳናት:: አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ድርጅት የሌለው ፣1995

ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች) :: የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ ፣ አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት ፣ 1990 ::

መልአኩ አስማማው :: ሀብታችንና ሥርዓቱ :: አዲስ አበባ ፣ 1993::

መንግስቱ ጎበዜ እና አሳምነው ካሳ:: የቤተክርስቲያን ታሪክ :: አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 2000::

ሙላው አለበል :: "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክህነት የሹመት ስሞች::" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 1981 ::

ሰሎሞን ዮሃንስ :: የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት:: አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት 2001 ::

ሰሙ ምትኩ እና ቸሬ አበበ :: የቤተክርስቲያን ታሪክ አዲስአበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 2000::

ሰይፈ ሥላሴ ዮሃንስ :: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት :: አዲስ አበባ፣ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፣1982::

ስርግው ገላው:: ክብረ ነገሥት ግዕዝና አማርኛ :: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1994

ብርሃኑ ጎበና:: መራሄ ድህነት::አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1990

ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች) ::የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ::

ታደሰ አይችሉህም :: "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ሥርዓት እና የገዳማውያን የዕለት ከእለት ህይወት ከትዕምርታዊነቱ አንፃር በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለኃይማኖት ገዳማት"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 1999 ::

ቴዎድሮስ ገብሬ :: በይነ - ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ:: አዲስ አበባ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 2001::

ማህበረ ቅዱሳን (አዘጋጅ):: ትምህርተ ሃይማኖት ርትእት:: ማተሚያ ቤት የሌለው ፣አዲስ አበባ፣ 1993 ዓ.ም::

አበራ በቀለ ::ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ህይወት::አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1996 ዓ.ም::

አቡነ ሳሙኤል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ/ም (2000) ::አዲስ አበባ፣ 2000::

አቡነ ኤጲፋንዮስ :: ፍኖተ ሃይማኖት፣ ሰባቱ ምስጢራትና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን:: አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማ.ቤ.ኃ.የተ.የግ.ማ.2002.::

አባ ገብርኤል ::ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት::አዲስ አበባ ፣ ማተሚያ ቤት የሌለው 1993 ::

አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)::የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ:: አዲስ አበባ፣ 1999ዓ.ም::

አክሊሉ ታደሰ::ክህነትና ካህን በቤቱ በዕስራ ምእት (2000ዓ.ም)::አዲስ አበባ ፣ 2000 ::

ከፍያለው መራሔ :: የቤተክርስቲያን አስተዋፅኦ ለኢትዮጵያ ስልጣኔ:: ማተሚያ ቤት የሌለው 1986::

ኪዳነወልድ ክፍሌ:: መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948::

ክንፈገብርዔል አልታየ :: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ (2000) ::አዲስ አበባ:2000 ::

ክንፈገብርዔል አልታየ እና ጌታቸው ደጀኔ :: ስርዓተ ቤተክርስቲያን አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ::

የኢትዮጵያ መፅሐፍ ቅዱስ ማህበር(አዘጋጆች) :: የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት::አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ::

_______ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይ እና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት :: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 2000 ::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናት ምርምር ማዕከል ( አዘጋጅ):: ኣማርኛ መዝገበ ቃላት ::አዲስ አበባ፣1993 ዓ.ም

ደስታ ተክለወልድ :: ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962::

ገ/ዮሐንስ ገ/ማርያም:: መፅሐፈ ቀሌሚንጦስ ዘሮም (በግዕዝና በአማርኛ):: አዲስ አበባ፣ማተሚያ ቤት የሌለው ፣2000 ዓ.ም::

ፊቃደ አዘዘ:: የሥነቃል መምሪያ:: አዲስ አበባ ፣ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣1991::

ፍሬህይወት ባዩ:: "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ"፣ 2000 :: ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 1999::

ፍትሃ ነገስት ስጋዊ ወመንፈሳዊ የህግ ምንጭ:: አዲስ አበባ ተስፋ ገብረ ስላሴ ማተሚያ ቤት 1993::

Arnold Van Gennep. The Rites of Passage. Chicago USA:The University of Chicago press,1960.

Aymro Wondimagengehu and Joachim Motovu. The Ethiopian orthodox Church .Addis Ababa:Berhanena selam ,HSI printing press, 1970.

Brown Radcliffe A.R. Structure and function in primitive society. Great Britain at the University press.1952.

Budge E.A Walls.The Queen of Sheba and her only son Menyilk.The kebra Nagast Newyork; Kegan Paul. 2001.

Chaillot ,Chiristain .The Ethiopian orthodox Tewahido Church Tradition.A Breaf Introduction to its Life and spirituality. Paris: 2002.

Dan Ben Amos." Context" in context ".Journal of American Folklore. Vol.52,No 2/4.9. 1993.P.209-226.

Dorson,Richard M.(ed).Folklore and folk life;An introduction. Chicago; USA . Chicago printing press;1972.

Dundes Alan. Essays in Folkloristics. Berkely;University of California press. 1978.

Epheram Isaac.``Social Structure of Ethiopian Church". Journal of Ethiopian Observer.Vol. XIV No 4. Published in Ethiopia and Britain,1971.

Goldstien Kenneth S .A guid for field workers in folklore. London,Herbvert Jenkins; 1964.

Kapchan Deborah A. "Performance ".Journal American Flklore. .Vol.108,No. 430 American folklore Society.1995.page 479.

Marcus Harold G. A history of Ethiopia . London ;University of California press.

Mary Hurfford ."Context".Journal of American Flklore. .Vol.108 ,No430. American folklore Society. 1995 Page 529.

Mattew P.K The Church of Ethiopia; A Panaroma of History and spiritual life ``The Hierarchy."_Addis Ababa : Publication of the Ethiopian orthodox church, 1970.

Brown Radcliffe A.R. Structure and function in primitive society. Great Britain at the University press.1952.

Rapport Ray A. Folklore, Culteral Performances, and Popular Entertaiments. Newyork; Oxford University press.1992.

Sergew Hable Selassie. The Church of Ethiopia; A Panaroma of History and spiritual life. Addis Ababa : Publication of the Ethiopian orthodox church, 1970.

Sims Martha and Stephens Martin. Living Folklore:An introduction to the study of People and their Tradition.Ohio;Utah state University press,2005.

Taddese Tamirat. Church and State in Ethiopia 1270-1527.Oxford : At the clarendon press,1972.

Titone Jeff Todd."Text" .The journal of American Folklore ,vol 108,No 430.p 432-445.1995.

Whitehead Alfered North. Symbolism. Its meaning and effect.New York,Fordham university press;1985.

Williams Toms Rhys. Field Methods in the study of Culture. New York; Stanford University press, 1967.

አባሪ አንድ

የመረጃ አቀባዮች አጭር መግለጫ

| የመረጃ ሰጪዎች ስም | ፆታ | እድሜ | ሥራ | መረጃው የተሰጠበት ቦታ | የመረጃው አይነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ | ወንድ | | - የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ፤የፓትርያርኩ ረዳት እና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል | በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን | - የዲቁና ስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ በተግባር ማሳየት |
| ብፁዕ አቡነ ጢሞቲዎስ | ወንድ | | - የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን | በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ | - ስለክህነት ስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ አፈጻጸም |
| መጋቢ. ጥበብ የማነብርሃን ጌታ | ወንድ | | - የቅድስት በአታለማርያም መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የዜማ መምህር | ቅድስት በአታለማርያም መንፈሳዊ ት/ቤት | -ስልጣነ ክህነትን ለመቀበል መሟላት ካለባቸው መስፈርቶች ውስጥ ስለአብነት ትምህርት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሊቀካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ | ወንድ | 75 | በአዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የሊቃውንት ጉባኤ አባል እና ሊቀ ካህናት | በአዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተክህነት | በስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ ውስጥ ስለሚገኙት ትእምርቶች ትርጓሜ |
| ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል | ወንድ | 35 | -የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህር | በአዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት | - ስልጣነ ክህነትን ለመቀበል መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች |
| መምህር ደጉ አለም ካሳ | ወንድ | | - የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህር | በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ | ስለክህነት ምንነት፣ደረጃዎች፣፣ መስፈርቶች፣ የአከዋወን ስርአት ፣ የካህናት አገልግሎት እና የትእምርቶች ተምሳሌት |
| መሪጌታ ጽጌ ዘሪሁን | ወንድ | 70 | -በጠቅላይ ቤተክህነት ሊቃውንት ክፍል ምክትል ጸሐፊ | በአዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተክህነት | ስለክህነት ምንነት፣ደረጃዎች፣፣ መስፈርቶች፣ የአከዋወን ስርአት ፣ የካህናት አገልግሎት እና የትእምርቶች ተምሳሌት |
| ሊቀጠበብት አዳሙ እምሩ | ወንድ | | -በአዲስ አበባ ሃገረስብከት ደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ የሐንስ እና መካነ ጎልጎታ ቤ/ያን የድጓ መምህር | አዲስ አበባ ወመዘክር ቤተ መፃህፍት ቅጥር ግቢ | ስለክህነት ምንነት፣ደረጃዎች፣፣ መስፈርቶች፣ የአከዋወን ስርአት ፣ የካህናት አገልግሎት እና የትእምርቶች ተምሳሌት |
| መምህር ኃይማኖት ኃይለማርያም | ወንድ | 48 | የሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ የዜና አበው መምህር | በሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ | -በስልጣን አሰጣጥ ስርአቱ ላይ ስለሚገኙ ትእምርቶች ተምሳሌት እና |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | መንፈሳዊ ኮሌጅ | ትርጓሜ |
| ዲያቆን ጽጌ ረዳኢ | ወንድ | 21 | የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ቤ/ያን ዲያቆን | በቅድስት ማርያም ቤ/ያን ቅጥር ግቢ | ዲቁናን ለመቀበል መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች፣ስለአገልግሎታቸው እና ስለአኗኗር ልማዳቸው |
| መጋቢ ጥበብ ቀሲስ አለምእሸት አብርሃም | ወንድ | | የቅድስት በአታ ለማርያም ቤ/ያን ቄስ እና የስብከተ ወንጌል ኃላፊ | በቅድስት በአታ ለማርያም ቤ/ያን ቅጥር ግቢ | ስለ ክህነት አሰጣጥ ቅድመ ክዋኔ ፣ስርአተ ክዋኔ እና ድህረ ክዋኔ ገጽታ |
| ዲያቆን ዮሐንስ ገ/ሚካኤል | ወንድ | | የብስራተ ገብርኤል ቤ/ያን ዲያቆን | በብስራተ ገብርኤል ቤ/ያን ቅጥር ግቢ | ዲቁናን ለመቀበል መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች፣ስለአገልግሎታቸው እና ስለአኗኗር ልማዳቸው |
| አብርሃም አለነ | ወንድ | | በሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ቤት የቲዎሎጂ ተማሪ | በሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ቤ/ያን ቅጥር ግቢ | ስለ ዲቁና ስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔ |
| አዲሱ ንብረት | ወንድ | 22 | ተማሪ | በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ | የዲቁናን ስልጣን ለመቀበል ስላሟላቸው መስፈርቶች፣በስርአተ ክዋኔው እለት ስለፈጸማቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና ስላሳለፈው የህይወት ልምድ |
| አለማየሁ ዘለቀ | ወንድ | 21 | ተማሪ | በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ | የዲቁናን ስልጣን ለመቀበል ስላሟላቸው መስፈርቶች፣በስርአተ ክዋኔው እለት ስለፈጸማቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና ስላሳለፈው የህይወት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| ተሾመ ደምለው | ወንድ | 22 | ተማሪ | በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ | የዲቁናን ስልጣን ለመቀበል ስላሟላቸው መስፈርቶች፣በስርአተ ክዋኔው እለት ስለፈጸማቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና ስላሳለፈው የህይወት ልምድ |
| ምስጋናው ካሱ | ወንድ | 22 | ተማሪ | በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ | ›› |
| አስቻለው ግርማ | ወንድ | 23 | ተማሪ | በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ | ›› |
| ሰለሞን ሞላልኝ | ወንድ | 21 | ተማሪ | በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ | ›› |

## አባሪ ሁለት

### ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርዓት ክዋኔን በተመለከተ ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

**ለመንፈሳዊ ትምህርት መምህራንና ለሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የቀረቡ ቃለመጠይቆች**

1. ክህነት ምን ማለት ነው?
2. ክህነት በኢትዮጵያ መቼ ተጀመረ?
3. የክህነት ደረጃዎች ስንት ናቸው?
4. ስልጣነ ክህነትን ለመቀበል የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ምን ምን ናቸው?
   4.1 በዲቁና
   4.2 በቅስና
   4.3 በኤጲስ ቆጶስና
5. ስልጣነ ክህነት መቼ መቼ ይሰጣል?
6. ስልጣነ ክህነትን ማን ይሰጣል? ለምን?
7. ክህነትን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ንዋያተ ቅድሳት ምን ምን ናቸው?
8. የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ቅደም ተከተል እንዴት ነው;
9. ከስልጣነ ክህነት በኋላ የካህናት ተግባር ምንድን ነው;
10. ካህናት በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ደረጃ ምንድን ነው; (ካህናት በማህበረሰቡ ውስጥ የተለየ ቦታና ደረጃ አላቸው;)
11. ክህነትን ደጋግሞ መውሰድ ይቻላል;
12. ካህናት ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች የተለየ የአኗኗር ልማድ አላቸው;
13. ከካህናት ህይወት ወይም ተግባር ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ወይም የሚተረኩ ስነቃሎች አሉ;
14. ሴት ስልጣነ ክህነትን መቀበል ትችላለች ;

ለ. ለጳጳሳት የቀረቡ ቃለመጠይቆች

1. ክህነት ምን ማለት ነው?
2. ክህነትን ማን መሰረተ?
3. በአሁን ሰዓት ያለው የክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ መሠረቱ ከየት ነው?
4. ክህነትን ማን ይሰጣል? ለምን?
5. የክህነት ደረጃዎች ስንት ናቸው?
6. ክህነትን ለመቀበል መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ምን ምን ናቸው?
7. የክህነት አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ እንዴት ይካሄዳል?
8. የክህነት ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ለመፈፀም ምን ምን አይነት ንዋያተ ቅድሳት ያስፈልጋሉ?
9. የክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ መፈጸም ለምን ይጠቅማል?
10. ካህናት ከማህበረሰቡ የተለየ የአኗኗር ልማድ አላቸው? ለምን?
11. ካህናት ስልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኋላ ምን ምን አይነት አገልግሎት ይሰጣሉ?

ሐ. ለቀሳውስት የቀረቡ ቃለመጠይቆች

1. ክህነት ምን ማለት ነው?
2. የክህነት አይነቶች ስንት ናቸው?
3. ቄስ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
4. ቄስ ለመሆን የፈለጉበት ምክንያት ምንድን ነው?
5. የቅስናን ስልጣን ለመቀበል ምን ምን መስፈርቶችን አሟልተው ነበር?
6. የቅስናን ስልጣን የሚሰጥ ማን ነው? ለምን? መቼስ ይሰጣል?
7. የቅስናን ስልጣን ከተቀበሉ በኋላ ምን ምን አይነት አገልግሎቶችን እየሰጡ ይገኛሉ?
8. የቅስናን ስልጣን ከተቀበሉ በኋላ ምን አይነት የአኗኗር ልማድ አለዎት?

መ. ለዲያቆናት የቀረቡ ቃለመጠይቆች

1. ዲያቆን ምን ማለት ነው?
2. የዲቁናን ስልጣን ለመቀበል ምን አነሳሳህ?
3. ዲያቆን ለመሆን ምን ምን መስፈርቶች መሟላት አለባቸው?
4. የዲቁናን ስልጣን እንዴት ተቀበልህ?
5. የዲቁናን ስልጣን በመቀበልህ ምን ጥቅም አገኘህ?
6. የዲቁናን ስልጣን ከተቀበልህ በኋላ ምን ምን አገልግሎቶችን ትሰጣለህ?
   6.1 በቤተ ክርስቲያን ውስጥ?
   6.2 በማህበረሰቡ ውስጥ?
7. የዲቁናን ስልጣን ከተቀበልህ በኋላ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለህ የአኗኗር ልማድ እንዴት ነው?

መ. በስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ለሚፈፀሙ ድርጊቶች ወይም ክዋኔዎች ተምሳሌታቸውን( ትርጉማቸውን) ለማግኘት ለካህናት፣ ለሊቃውንተ ቤተክርስቲያን እና ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ዲያቆናት የዲቁናን ስልጣን ለመቀበል አስራ ስምንት ሰዓት እንዲፆሙ የተደረገበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ስልጣነ ክህነት በጠዋት የሚሰጠው ለምንድን ነው?
3. ስርዓተ ክዋኔው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰጠው ለምንድን ነው?
4. የቀሳውስትና የጳጳሳት አልባሳት (ቆብ ፣ ቀሚስ ፣ የሚደርቡት ካባ ፣ ጥምጥም)አይነትና ቀለም ተምሳሌት ምንድን ነው?
5. በስልጣን አሰጣጥ ስርዓቱ ላይ የእጅና የመስቀል ቡራኬ ተምሳሌት ምንድን ነው?
6. ስልጣኑን ለሚቀበሉ ግለሰቦች በክርስትና ስማቸው ጸሎት የሚፀለየው ለምንድን ነው?
7. ስርዓተ ክዋኔው ሲፈፀም ፊትን ወደ ቤተመቅደስ ማዞር ምን ተምሳሌት አለው?
8. የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔ በፀሎትና በንባብ ለምን ይካሄዳል?
9. በስርዓተ ክዋኔው ላይ የስርዓቱን መጽሐፍ ሌላ ሰው ወደ ደረቱ አስጠግቶ ገልጦ እንዲይዝ የሚደረግበት ምክንያት ምንድን ነው?
10. በሚነበበው መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጽሑፎች በጥቁርና በቀይ ቀለማት የሚፃፉት ለምንድን ነው?

ABABA UNIVERSITY ... S LIBRARY

11. ስርዓተ ክዋኔው የሚፈፀምበት ቋንቋ ግዕዝ ለምን ሆነ?

12. በክህነት አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔው ጊዜ ተቀባዮች ወደ ቤተ መቅደስ እየዞሩ ሶስት ጊዜ የሚሰግዱበት ምክንያት ምንድን ነው?

13. በስርዓተ ክዋኔው ጊዜ ለሶስት ፣ ለአምስትና ለሰባት ጊዜ ጳጳሱ እና ዲያቆኑ የሚያደርጉት የቦታ ቅይይር (ዑደት) የምን ተምሳሌት ነው?

14. በስልጣን አሰጣጥ ስርዓተ ክዋኔው ላይ የእጅ መጫን (የአንብሮተ ዕድ) ተምሳሌት ምንድን ነው?

15. በስርዓተ ፀሎቱ ጊዜ እግዚኦ መሐረነ እና አቡነ ዘበሰማያት የሚፀለየው ለምንድን ነው? እግዚኦ መሐረነ 12 ጊዜ እንዲባል የተወሰነውስ ለምንድን ነው?

16. የቃለ ምዕዳን የሚፈጸመው ለምንድን ነው?

17. ዲያቆናቱ ለመቁረብ ሲዘጋጁ በካህኑ መስቀል የተባረኩት ለምንድን ነው?

18. ወንጌል ከተነበበ በኂላ ዲያቆናቱና ምዕመናን ወንጌሉን የተሳለሙት ለምንድን ነው?

19. ዲያቆናቱ ስርዓተ ክዋኔውን በተቀበሉበት ዕለት የዲያቆናትን ካባ እንዲለብሱ የተደረገው ለምንድን ነው?

20. ዲያቆናቱ ከቆረቡ በኂላ ጸበል እንዲጠጡና አፋቸውን እንዲሸፍኑ የተደረገበት ምክንያት ምንድን ነው ?

21. ቆርበው የቅዳሴው ስርዓት ከተጠናቀቀ በኂላ እህል (ፃዲቅ) እንዲቀምሱ የተደረገበት ምክንያት ምንድን ነው?

22. ቆርበው ወደ ቤታቸው ከሄዱ በኂላ የሚያደርጉት ጥንቃቄ ምንድን ነው? በጥንቃቄው የሚያገኙት ፋይዳስ ምንድን ነው?

23. ዲያቆናት ምስጢርን ቤተልሔም በተባለው ቦታ ውስጥ የሚያዩበት ምክንያት ምንድን ነው?

24. ዲያቆን ቄስ ለመሆን ከፈለገ ሚስት እንዲያገባ የሚደረገው ለምንድን ነው?

25. የቅስና ስልጣን ከሰላሳ ዓመት በኂላ ላሉት የሚሰጠው ለምንድን ነው?

26. ቄሶች ስልጣነ ክህነትን ተቀብለው አገልግሎት ሳይጀምሩ አርባ ቀን የሚፆሙት ለምንድን ነው?

27. ካህናት ምዕመናንን የሚባርኩበትን የዕጅ መስቀል ለአገልግሎት ከማዋላቸው በፊት ለሰባት ፣ ለአስራ አራት እና ለሃያ አንድ ቀናት በመንበር ላይ አስቀምጠው እንዲፀለይበት የሚያደርጉት ለምንድን ነው?

28. የካህናት የዕጅ መስቀል የሚሰራው ከምንድን ነው?

30. የኤጲስ ቆጶስነትን ስልጣን ለመቀበል ድንግል እና መነኩሴ መሆን ለምን አስፈለገ? ተምሳሌታቸውስ ምንድን ነው?

31. የኤጲስ ቆጶስነትን ስልጣን ለመስጠት ህዝበክርስቲያን እንዲሰባሰቡ የሚደረግበት ምክንያት ምንድን ነው?

32. የኤጲስ ቆጶስነትን ስልጣን ለመስጠት ምርጫ የሚካሔደው ለምንድን ነው?

33 . የኤጲስ ቆጶስና ስልጣን ለመቀበል ፀጉራቸውን የሚላጩት ለምንድን ነው?

34. በአንገታቸው ላይ ያጠለቁት ከቆዳ የተሰራ ነገር ምንድን ነው? የያዘው መስቀል ብዛትስ ስንት ነው? ተምሳሌቱስ ምንድን ነው?

35. ጳጳሳት አርዌ ብርት የሚሰጣቸው ለምንድን ነው?

36. የጳጳሳት የአለባበስ ስርዓት የተለየ ለምን ሆነ?

37. ጳጳሳት በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ተወስነው እንዲኖሩ እና የራሳቸው ሃብትና ንብረት እንዳይኖራቸው የተደረገበት ምክንያት ምንድን ነው?


## አባሪ ሶስት


## ፎቶግራፎች


1. መምህር የማነ ብርሃን ጌታ ስልጣነ ክህነትን መቀበል ለሚችሉ የአብነት ተማሪዎች በበአታ ለማርያም መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ውስጥ የቅዳሴ ትምህርት ሲያስተምሩ የሚያሳዩ ፎቶዎች



BABA UNIVERSITY
S LIBRARY















## 2. የዲቁና ስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች




ብጹእ አቡነ ቀውስጦስ የክህነት መስጪያ መጽሐፉን በማንበብ ሥርዓቱን ሲፈጽሙ



ሥርዓቱን በንባብ ከፈጸሙ በኋላ ቡራኬ ሲሰጡ

*የአንብሮተ ዕድ ሥርዓት ሲፈጸም*

*የዲቁና ስልጣን ከተቀበሉ በኋላ ቃለ ምእዳን ሲሰጥ*

3. ካህናት ስልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኂላ ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች ውስጥ ከፊሎቹን የሚያሳዩ ፎቶዎች






ሥርዓተ ጥምቀትን ይፈጽማሉ



ምዕመናን ሃይማኖታዊ ስርአቶችን ጠብቀው ጥሩ ስነምግባር ይኖራቸው ዘንድ ወንጌልን ያስተምራሉ






በምስጋና ፣በዝማሬ እና በአምልኮ ቤተክርስቲያንን ያገለግላሉ



ት ሃይማኖታዊ እሴቶችን በመጠበቅ የቤተክርስቲያንን ትውፊት ለምእመናን ያሳውቃሉ የነፍስ አባት
በመሆንም በጥሩ ስነምግባር ያንጻሉ

4. የጵጵስና ስልጣን አሰጣጥ ስርአተ ክዋኔን የሚያሳዩ ፎቶዎች





የኤጲስ ቆጶስናን ስልጣን ለሚቀበሉ ቆሞሳት ሥርዓተ ጸሎት ሲፈጸምላቸው




ብጹእ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መስቀላቸውን በጳጳሳቱ ራስ ላይ በማኖር ቡራኬ ሲሰጧቸው



ጳጳሳት በረከት እና ጸጋቸው በኤጲስ ቆጶሳቱ ላይ ያድርባቸው ዘንድ ሲዳስሷቸው



ብፁእ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ እጃቸውን በጳጳሳቱ ራስ ላይ በማስቀመጥ የአንድሮተ እድ ስርአት ሲፈጽሙ



ለኤጲስ ቆጶሳቱ ልብሰ ተክህኖ እና አክሊለ ሶክ( ቆብ) ሲደረግላቸው



ብጹእ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በጳጳሳቱ ማንባር ላይ እፍ በማለት መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ሲያደርጉ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸው ኢትዮጵያ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተማሪ የሆንኩ ይህ ጽሑፍ የእኔ ስራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በአግባቡ የተጠቀምኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም-----------------------------------------

ፊርማ -----------------------------------

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ሰኔ 2003 ዓ.ም